# አማርኛ እንደመጀመሪያ ቋንቋ

## ዘጠነኛ ክፍል

## የተማሪ መጽሐፍ

በአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ ተዘጋጅቶ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ ትምህርት ቢሮ ተስማምቶና ተሻሽሎ የቀረበ


### አስማምቶ አዘጋጆች

ታምሩ ገለታ (MEd)

ግሩም ጥበቡ (MA)

### አርታኢዎች

ታሪኩ ነገሰ (PhD)

በላይነሽ ደነቀ (PhD)

### ጥራት ተቆጣጣሪ

ይልፋሸዋ ጥላሁን (BEd)

### ግራፊክስ

ታደሰ ድንቁ

©ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2015/2023

ይህ መፅሐፍ በ2015 ዓ.ም. በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀ ነው። የመጽሐፉ ህጋዊ የቅጂ ባለቤት ©2015 ዓ.ም. የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ መብት በህግ የተጠበቀ ነው። የዚህን መጽሐፍ ክፍል በተለያዩ መሳሪያዎች ያለባለቤቱ የቅድሚያ ፈቃድ እንደገና ማሳተም፣ ማሰራጨት፣ ማከማቸትና መልሶ መጠቀም አይቻልም።

የቅጂ መብቶችን ለማክበር በተቻለን መጠን የሚፈለግብንን ጥረት ሁሉ አድርገናል። ሳናውቅ በስህተት ሳንጠቅሳቸው የተዘለሉ ካሉ በቅድሚያ ይቅርታ እየጠየቅን በሚቀጥሉት ህትመቶች አስፈላጊውን እውቅና እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን።

# ማውጫ


| ይዘት | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | iv |
| መግቢያ | v |
| ምእራፍ አንድ፡ ቋንቋ | 1 |
| ምእራፍ ሁለት፡ግብር | 22 |
| ምእራፍ ሦስት፡ ማእድን | 41 |
| ምእራፍ አራት፡ ልቦለድ | 58 |
| ምእራፍ አምስት፡ ቃላዊ ስነጽሑፍ | 75 |
| ምእራፍ ስድስት፡ ግጥም | 90 |
| ምእራፍ ሰባት፡ ኮሮና (ኮቪድ -19) | 111 |
| ምእራፍ ስምንት፡ ተውኔት | 126 |
| ምእራፍ ዘጠኝ፡ መገናኛ ብዙኃን | 144 |
| ሙዳየ ቃላት | 157 |
| ዋቢ ጽሁፎች | 161 |

# መቅድም

ትምህርት ሚኒስቴር "ጥራቱ የተጠበቀና እኩል ተደራሽነት ያለው ትምህርት ለሁሉም ማዳረስ" በሚል ትኩረት ሰጥቶ አዲስ ሥርዓተትምህርት ቀርጾ አቅርቧል። በዚህም መሠረት ቀድሞ በነበረው ሥርዓተትምህርት ላይ ታይተው የነበሩ ክፍተቶችን ለመሙላት ምርምር ተደርጓል። ከምርምሩም የተገኙ አቅጣጫዎች የተማሪዎቹን ደረጃ አለመመጠን፣ የትምህርቱ አንኳር ጽንሰሀሳቦች ግልጽ አለመሆን፣ ከይዘቱ መታጨቅ የተነሳ ለዓመቱ ከተመደበለት ክፍለጊዜ ጋር አለመመጣጠን እና ከተጓዳኝ ሥርዓተትምህርቶች አማራጭ ግብዓቶችን አለመጠቀም ናቸው። ስለሆነም ስርዓተትምህርቱ የቋንቋ ልህቀትን ለማሻሻል፣ በአውድ የተደገፈ ለማድረግ እና በተግባራዊ መማር ላይ የተመሠረተ የመማር ስኬታማነትን ለማረጋገጥ ተቀርጿል።

ሥርዓተትምህርቱን መሠረት በማድረግም የትምህርት መሣሪያዎች ተዘጋጅተዋል። ከእነዚህም ውስጥ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ አንዱ ነው። ስለሆነም ይህ መጽሐፍ በአዲስአበባ ትምህርት ቢሮ የተዘጋጀውን መጽሀፍ በኦሮሚያ አማርኛን እንደመጀመሪያ ቋንቋ ከሚማሩ ተማሪዎች ነባራዊ፣ ስነልቦናዊና የቋንቋ ችሎታ ሁኔታዎች አንጻር በማስማማትና በከፍተኛ ደረጃ በማሻሻል ተዘጋጅቷል። መጽሐፉም ተማሪዎች ቢያንስ መጎናጸፍ ያለባቸውን ብቃት (Minimum Learning Competency) እና የሚጠበቁ የመማር ውጤቶችን መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው።

## መግቢያ

ይህ መማሪያ መጽሐፍ ዘጠኝ ምእራፎችን ይዟል። እያንዳንዱ ምእራፍ ደግሞ በሥሩ ስድስት ንኡሳን የትምህርት ይዘቶችን አካቷል። እነርሱም ትምህርት አንድ ማዳመጥ፣ ትምህርት ሁለት መናገር፣ ትምህርት ሶስት ማንበብ፣ ትምህርት አራት መጻፍ፣ ትምህርት አምስት ቃላት እና ትምህርት ስድስት ሰዋስው ናቸው። እያንዳንዱ ትምህርት በመርሃትምህርቱ በተደለደለው መሠረት መመሪያዎችን፣ ትዕዛዛትን፣ መልመጃዎችን እና ተግባራትን አካቷል። ከዚህ አኳያ የቋንቋ ክሂሎች የተደራጁት በቅድመ ተግባር፣ በጊዜ ተግባር እና በድህረ ተግባር ሂደታዊ አቀራረብ ሲሆን የቋንቋ እውቀት ዘርፎች ደግሞ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር አቀራረብን ተከትለዋል። በተጨማሪም የቀረቡትን የትምህርት ይዘቶች የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ ተኮር እንዲሆን ጥረት ተደርጓል።

# ምእራፍ አንድ
# ቋንቋ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለቋንቋ ምንነትና ተግባራት የሚገልጽ ጽሁፍ ሲነበብ አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ።
- በውይይት ውስጥ በመሳተፍ ሀሳባችሁን ትገልጻላችሁ።
- የቃል ዘገባ ታቀርባላችሁ።
- የግል ማስታወሻ በመጠቀም አንቀጽ ትጽፋላችሁ።
- የምንባቡን ዋና ዋና ሃሳቦች ትጽፋላችሁ።
- አውድን በመጠቀም ለአንድ ቃል የተለያየ ትርጉም ትሰጣላችሁ።
- አርፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ።
- የተለያዩ የአረፍተነገር አይነቶችን ለተለያዩ ተግባራት ትጠቀማላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህራችሁ “የቋንቋ ምንነትና ተግባራት” በሚል ርእስ የቀረበ ጽሁፍን ሲያነቡላችሁ አዳምጡ። ከዚያም የቀረቡትን ጥያቄዎች በትእዛዛቸው መሠረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች በጥንድ በመሆን ስለቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ከተወያያችሁ በኋላ የተወያያችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

2. ተማሪዎች መምህራችሁ “የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት” በሚል ርእስ ጽሁፍ ያነቡላችኋል። ከርእሱ በመነሳት የጽሁፉን ርእስ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ።

3. የሚከተሉት ቃላት ከምታደምጡት ጽሁፍ የተወሰዱ ናቸው። የቃላቱን ፍች ግለጹ።

   ሀ. ተራ   ለ. ዘዬ   ሐ. ነጸብራቅ   መ. የሚሰርጸው

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት ጽሁፍ ምን ተገነዘባችሁ?

2. ቀጥሎ በምታዳምጡት የጽሁፉ ክፍልስ ምን ምን ጉዳዮች የሚተረክ ይመስላችኋል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ባዳመጣችሁት መሠረት ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. ቋንቋ ምንድን ነው?
2. ቋንቋ ከእንስሳት መግባቢያ በምን ይለያል?
3. ዋና ዋና የቋንቋ ተግባራት ምን ምን ናቸው?
4. የጽሁፉን አጠቃላይ መልእክት ግለጹ።

ለ. ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መነሻ በማድረግ የቋንቋ ዋና ዋና ተግባራት ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በሚከተለው ቻርት ላይ አስፍሩ።




## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ተግባራት እንዲሁም የውይይት ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ ማስታወሻ ቀርበውላችኋል። የቀረቡላችሁን ተግባራት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ፤ ማስታወሻውንም አጥኑ።

ተግባር አንድ

1. የውይይት ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ በመወያየት መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

2. የሰው ልጅ ቋንቋ ከእንስሳት መግባቢያ ጋር ያለውን ልዩነት በቡድን በመወያየት ዋና ዋና ነጥቦችን ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

## የውይይት ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ

ውይይት አላማ ያለው፣ በእቅድ የተዘጋጀና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ርእሰጉዳዮች ዙሪያ ሀሳብ የሚለዋወጡበትና ከጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት ተግባር ነው። ውይይት ራሱን የቻለ የዝግጅትና የአቀራረብ መመሪያ አለው። በውይይት ዝግጅት ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ ርእሱን በሚገባ ማስተዋል፣ ርእሱን በሚመለከት መረጃ መሰብሰብ፣ የተሰበሰቡት መረጃዎችለተሳታፊዎች የሚመጥኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ እና መረጃዎችን በቅደም ተከተል ማደራጀት የሚሉት ይገኙበታል።

በውይይት አቀራረብ ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ ደግሞ የውይይት አላማንና ርእስን ማስተዋወቅ፣ የውይይቱን ጭብጥ በቅደም ተከተል ለተደራሲያን ማቅረብ፣ ሀሳብን ባልተንዛዛ ሁኔታ በተመጠነ ድምጽ በመጠቀም ማቅረብ፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ መጠቀም እና በውይይቱ መጨረሻ ተሳታፊዎችንና ታዳሚዎችን ማመስገን ይገኙበታል።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት “የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት” የሚል ምንባብ እና ምንባቡን ከማንበባችሁ በፊት የቅድመማንበብ ጥያቄዎች፣ ምንባቡን እያነበባችሁ የምትመልሷቸው የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችና ምንባቡን አንብባችሁ ካጠናቀቃችሁ በኋላ የምትሰሯቸው ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል። በመሆኑም ጥያቄዎቹን በትእዛዛቸው መሠረት በትኩረት ስሩ።

## የቅድመ ማንበብ ጥያቄዎች

1. የቋንቋዎች መሠረታዊ ባህርያት ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
2. የሰው ልጅ ቋንቋን የሚለምደው እንዴት ይመስላችኋል?

# የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት

በአለማችን ላይ የሚነገሩ ቋንቋዎችን ከሌሎች መግባቢያዎች በተለየ እኳኋን አንድ የሚያደርጓቸው ብዛት ያላቸው የጋራ ባህርያት አሏቸው። እነሱም:- ማህበራዊነት፣ ሰብአዊነት፣ ዘፈቀዳዊነት፣ ስርአታዊነት፣ ረቂቅነት፣ ምሉእነት፣ መዋዋስ፣ በመልመድና በመማር መገኘት፣ መወለድ፣ ማደግ እና መሞት የተሰኙ ናቸው።

ቋንቋ ማህበራዊ የመግባቢያ መሳሪያ ነው። የሰዎች ማኅበራዊ ኑሮ ትርጉም ይኖረው ዘንድ ቋንቋ ያስፈልገዋል። የሰዎች ማኅበራዊነት ያለ ቋንቋ ሙሉ እንደማይሆን ሁሉ ቋንቋም ያለ ማኅበራዊነት ሙሉ አይሆንም። የቋንቋ ማኅበራዊነት ስንል፣ ቋንቋ ሰው ከመሰሉ ጋር የሚግባባበት መሆኑን ለማመልከት ብቻ ሳይሆን ቋንቋ "ሰው" የፈጠረው ከአካባቢው ጋር የሚለዋወጥ፣ የሚወለድ፣ የሚያድግና የሚሞት፣ የሰው መለያ የሆነ ምድራዊ ውጤት መሆኑንም ለማመልከት ነው። በዚህ መሠረት ቋንቋ የሚለመድ፣ የሚማሩት እንጂ የሚወለዱበት አይደለም።

ቋንቋ ለሰብአዊ ፍጡር ብቻ የሚያገለግል በመሆኑ የተነሳ ቋንቋን ሰብአዊ ነው ያሰኘዋል። ከሰው ልጅ በስተቀር ቋንቋ ያለው ሌላ ፍጡር የለም። በዚህም የተነሳ ቋንቋ ሰብአዊ ባህሪይ አለው ይባላል።

ቋንቋ የዘፈቀዳዊነት ባህሪይ አለው። ዘፈቀዳዊነት ሲባል በአንድ ቃል እና በሚወክለው ነገር መካከል የባሕርይ ግንኙነት የለም ማለት ነው። ለ ም ሳ ሌ "ውሻ" የሚለው በዚህ ስያሜ ለምንጠራው እንስሳ ሥጋው አይደለም። "ውሻ" በማለት ፈንታ "ላላ" ብንለው ውሻነቱ አይለወጥም።

ቋንቋ ሥርአት አለው። ይህም ሲባል ቋንቋ ሕግ አለው ማለት ነው። ይህንን በምሳሌ መመልከት ይበጃል። መጀመሪያ በሥርአተ ድምጹ በኩል ብናየው፣ "ረፈደ" የሚለውን ቃል እንውሰድና በውስጡ ያሉትን ድምጾች እንመልከት። ነገሩ በጣም ግራ እንዳያጋባን ልክ

በአማርኛ እንደተጻፈው እንውሰደውና ረ-ፈ-ደ ጊዜው እንደማለፍ ብኋል ማለት ነው። ፊደላቱ ያሉበትን ቦታ ብንቀያይር "ደፈረ"ን፣ "ፈረደ"ን እናገኛለን። ፊደላቱ ወይም ትእምርቶቹ አንዱ የሌላውን ስፍራ ሲወስድ ትርጉሙ ይለወጣል።

ቋንቋ ረቂቅ ነው። በንግግር ወቅት መልእክት የሚተላለፈው በድምጽ ነው። ድምጹ እና ድምጹ የሚወክለው ነገር ወይም ሁኔታ ግን የግድ አንድ ላይ ላይገኙ ይችላሉ። ይህም ማለት አንድ ሰው አንድ ቃል ከወካዩ ግኡዝ ነገር፣ ሁኔታ ነጥሎ ጽንሰሀሳቡን ብቻ በመቅረጽ ነገሩ ወይም ሁኔታው ከነበረበት የቦታና የጊዜ ክልል ውጪ ሊናገረው ይችላል። ለራሱ ሲነገረውም አዳምጦ መረዳት አይቸግረውም። ለምሳሌ "ነብር" የሚለው ቃል አውሬው በሌለበት ቦታ እና ጊዜም ቢነገር ወይም ድምጹ ቢሰማ ነብሩ በሐሳባችን ይቀረጻል። ይህም መልእክቱን በተለየና በላቀ ደረጃ የማስተላለፍ ባህርይው ቋንቋን ረቂቅ ነው ያሰኘዋል።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካነበባችሁት ጽሑፍ ምን ተገነዘባችሁ?
2. የቋንቋ የሰብአዊነት እና የሥርአታዊነት ባህርይ ምንን ይገልጻሉ?

ለአንድ ለተወሰ ሕዝብ ቋንቋው በራሱ ምሉእ ነው። የቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ አካባቢውን ተገንዝቦ፣ የተገነዘበውን ለመሰሉ ለማስተላለፍ የሚያስችለው በቂ መድበለ ቃላት፣ ሙሉ የቋንቋ ሥርአት አለው። የማወቅ ክበቡ በሰፋ ቁጥር ቋንቋውም ይሰፋል። የማያውቀውን አለመግለጹ ቋንቋውን ጎዶሎ ወይም ዝቅተኛ አያደርገውም። ስለዚህ ቋንቋዎች ሁሉ ለራሳቸው ባህል ምሉእ በመሆን አንድ አይነት ባህርይን ይጋራሉ።

የተለያዩ ሕዝቦች በልዩ ልዩ ምክንያት ተገናኝተው ልዩ ልዩ የባህል ቅርሶችን መለዋወጣቸው የታወቀ ነው። ቋንቋዎችም እንደዚሁ

ይለዋወጣሉ። በንግድ፣ በሃይማኖት፣ በቴክኖሎጂ፣ ወዘተ. ምክንያት አንዱ ቋንቋ ከሌላው ይገናኛል፤ ያለውን ያውሳል፤ የሌለውን ይዋሳል። መዋዋስ የቋንቋና የማኅበራዊ ኑሮ ሥርአት የሚጠይቀው ግዴታ ነው። በዚህ አንጻር ስናየው አንድም ቋንቋ ራሱን ችሎ፣ ንጽሕናውን ጠብቆ" የአለሙን ሁኔታ ሁሉ መግለጽ አይቻለውም። አንድ ቋንቋ ከሌላው ቋንቋ ድምጽን፣ ቃልን፣ አገላለጽን፣ ወዘተ. ሊዋስ ይችላል።

አንድ ሰው የጠቅላላ አካላቱን ቅርጽና ዓይነት ከእናት ከአባቱ ወይም ከሥጋ ዘመዶቹ ይወርሳል። ቋንቋ መናገር የሚችለው ግን በመማርና በመለማመድ እንጂ በተፈጥሮ ከእናት ከአባት በመውረስ አይደለም። አንድ ህጻን ሲወለድ ይዞት የሚወለደው ቋንቋን ሳይሆን ቋንቋን ለመልመድ የሚያበቃውን ሰብዓዊ ችሎታ ነው። በሚያድግበት አካባቢ ካለው ማኅበረሰብ ጋራ በሚኖረው መስተጋብር ባካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በማዳመጥ በምላሹም ለመናገር በመሞከር ቋንቋን ይለምዳል። ከዚህ ባለፈም ትምህርት ቤት በመግባትና፣ ከሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሌላ ተጨማሪ ቋንቋ ሊማር ይችላል። ቋንቋ ሰዎች ከተወለዱ በኋላ የሚለምዱት ወይም የሚማሩት እንጂ በተፈጥሮ የሚያገኙት አይደለም።

ቋንቋ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል። ይህ ሌላው የቋንቋ ጠባይ ነው። የአንድ ቋንቋ ዘዬዎች የተለያዩ ቋንቋዎች ከመሆን ደረጃ ሲደርሱ ቋንቋ ተወለደ ይባላል። የቋንቋው ተናጋሪ ኅብረተሰብ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በባህልና በአኗኗር ስልቱ ሲያድግ፣ እውቀቱ ሲሰፋ ወይም ርእዮተአለሙ ሲለወጥ ቋንቋውም በዚያው መጠን አዳዲስ ቃላትን በመፍጠር፣ ያሉትንም ቃላት ትርጉም በማስፋትና ከሌሎች በመዋስ አብሮ እየተሻሻለ፣ እያደገና እየበለጸገ ሲመጣ ቋንቋ አደገ እንላለን። ቋንቋው ቀስ በቀስ ወደሌላ ቋንቋ ሲለወጥ፣ በሌላ ቋንቋ ሲዋጥ፣ ተናጋሪ ሲያጣ ደግሞ ቋንቋ ሞተ ይባላል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት በሁሉም ቋንቋዎች ላይ የሚታዩ የጋራ ባህርያት ናቸው። ሆኖም ግን እያንዳንዱ ቋንቋ የራሱ የሆኑ

መለያ ባህርይ ያለው መሆኑ ሊዘነጋ የማይገባ ነው።

(ምንጭ፡ ዮሐንስ አድማሱ (1966) "አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ" ከሚለው ተሻሽሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ተገቢውን መልስ በቃልግለጹ። መልሶቻችሁንም ከሌሎች ቡድን ተማሪዎች ጋር አወዳድሩ።

1. ከቋንቋዎች መሠታዊ ባህርያት ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ።
2. "… ቋንቋዎችን ከሌሎች መግባቢያዎች …" የሚለው ሐረግ ምንን ያመለክታል? ከቋንቋ ውጭ የሆኑት ሌሎች መግባቢያዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
3. "… ቋንቋ የሚለመድ፣ የሚማሩት እንጂ የሚወለዱበት አይደለም። " ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. "ቋንቋ ዘፈቀዳዊ ነው" የሚለውን አገላለጽ አብራሩ።
5. አንድ ቋንቋ ከሌላ ቋንቋ ምን ምን ነገሮችን ሊዋስ ይችላል?
6. ቋንቋ ሞተ የሚባለው ምን ሲሆን ነው?
7. የምንባቡን ዋና ሀሳብ በአጭሩ ግለጹ።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።

1. የቋንቋ ማኅበራዊነት የሰው ልጅ ቋንቋን ከመሰሉ ጋር ለተግባቦት አገልግሎት ብቻ የሚያውለው መሳሪያ መሆኑን ያመለክታል።
2. ማንኛውም ቋንቋ በራሱ ምሉእ ነው።

3. በአንድ ቃል እና ቃሉ በሚወክለው አካል መካከል ያለው ግንኙነት ተፈጥሯዊ ነው።

4. ንግድ፣ ሃይማኖት፣ ቴክኖሎጂ በቋንቋዎች መ ካ ከ ል ለሚካሄደው ውሰት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

5. የቋንቋ የዘፈቀዳዊነት ባህርይ ከቋንቋ የሥርዓታዊነት ባህርይ ጋር ይቃረናል።

## ሐ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተገቢውን መልስ ምረጡ።

1. "የሰው ልጅ ድምጾችን ወይም ቃላትን ለአንድ ነገር ወኪል እንዲሆኑ የሚሰይማቸው በውክልና ከቆሙለት ነገር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ ተመስርቶ አይደለም።" የሚለው አገላለጽ ከቋንቋ ባህርያት ውስጥ የትኛውን ያመለክታል?

   ሀ. ሰብዓዊነቱን ለ. ሥርዓታዊነቱን

   ሐ. ዘፈቀዳዊነቱን መ. ረቂቅነቱን

2. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የቋንቋ የተዋዋሽነት ባህርይን አስመልክቶ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ለቋንቋ መጥፋት ምክንያት መሆኑን ያመለክታል።

   ለ. አንድ ቋንቋ በራሱ ምሉእ አለመሆኑን ያሳያል።

   ሐ. የቋንቋ ስርአት የሚጠይቀው ግዴታ መሆኑን ያመለክታል።

   መ. ቋንቋው ሙሉ በሙሉ ራሱን አለመቻሉንያመለክታል።

3. አንድ ህጻን አንድን ቋንቋ የሚ ናገረው

   ሀ. ከተፈጥሮ በማግኘት ነው። ለ. ከአካባቢው በመልመድ ነው።

   ሐ. ከአያቶቹ በመውረስ ነው። መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

4. በምንባቡ መሠረት ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በስምና በተሰያሚ መካከል ተፈጥሯዊ ግንኙነት አለ።

ለ. ማንኛውም ነገር ፍጹም ተገቢ የሆነ መጠሪያ የለውም።

ሐ. ማንኛውም ሰው ባሻው ጊዜ የቋንቋ ሥርዓት መቀየር ይችላል።

መ. ማንኛውም ፍጡር የሚግባባው በቋንቋ አማካይነት ነው።

5. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ለቋንቋ ማደግ በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችለውን ነገር የሚያመለክተው የትኛው ነው?

ሀ. የቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ በቴክኖሎጂ መበልጸግ፣

ለ. የቋንቋው ተናጋሪ ርእዮተ ዓለም መለወጥ፣

ሐ. የቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ እውቀት መስፋት፣

መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ።

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

ቀጥሎ "የቋንቋ መሰረታዊ ባህርያት" የሚለውን ምንባብ በድጋሚ በማንበብ የራሳችሁን ማስታወሻ ያዙ። በማስታወሻችሁ ላይ የራሳችሁ ልምድና ሌሎች ሰዎችን በመጠየቅ የምታገኙትን መረጃ አክላችሁበት ካደራጃችሁት በኋላ የተሟላ አንቀጽ አድርጋችሁ ጻፉ።

## ተግባር ሁለት

1. በምንባቡ ውስጥ ከቀረቡት የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት ውስጥ አንዱን በመውሰድ በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

2. “የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት” የሚለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች መነሻ በማድረግ አጭር ጽሁፍ ጻፉ።

ሀ. የምትማሩትን የቋንቋ አይነት ግለጹ።

ለ. የምትማሩትን ቋንቋ ከቋንቋ ባህርያት አኳያ የሚታይበትን ባህሪይ ዘርዝሩ።

ሐ. የዘረዘራችሁትን የቋንቋ ባህሪይ መነሻ በማድረግ አንድ የተሟላ አንቀጽ ጻፉ።

## ተግባር ሦስት

የማስታወሻ አያያዝ ስርአትን በተመለከተ ወደቤተመጻህፍት ጎራ ብላችሁ በማንበብ በማስታወሻ ደብተራችሁ ሀሳቡን በአንድ አንቀጽ አደራጅታችሁ ጻፉ። ከዚያም የጻፋችሁትን አንቀጽ ለጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ከዚህ ቀጥሎ የቃላትን አውዳዊ ፍቺ እንድትሰጡ የሚያስችል መልመጃ ስለቀረበላችሁ በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

### መልመጃ ሦስት

ሀ. በሚከተሉት ጥንድ ጥንድ አረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አውዳዊ ፍቺ በምሳሌው መሰረት ግለጹ።

ምሳሌ፡-

ሀ. ሀገራችን ለችግሮቿ <u>ቋሚ</u> መፍትሄ አገኘች። (አውዳዊ ፍቺ

- ዘላቂ)

ለ. እሷ ለወንድሟ ሰርግ <u>ቋሚ</u> ነበረች። (አውዳዊ ፍቺ - አሳላፊ፣

አስተናጋጅ)

1. ሀ. የምንጭ ውሃን ለመጠጥ ከመጠቀማችን በፊት ማጣራት ያስፈልጋል፡
   ለ. አንድ ነጋዴ አዳዲስ ምርቶችን ወደ መጋዘን ከማስገባቱ በፊት የነበሩትን ማጣራት አለበት።
2. ሀ. የሀገር ሽማግሌዎች ያቀረቡት የሰላም ጥሪ ድጋፍ አገኘ።
   ለ. ልጁ የቤተሰቡን ድጋፍ ፈለገ።
3. ሀ. ወጣቱ ትውልድ ከድህነት ለመውጣት እና ሀገሩን ለማልማት በጋራ ተነሳ።
   ለ. ተማሪው ለፈተና ዝግጅት በለሊት ከእንቅልፉ ተነሳ።
4. ሀ. መሐንዲሱ ለህንጻው ሥራ የሚያስፈልገውን በቂ ገንዘብ መደበ።
   ለ. የሥጋ ቤቱ ባለሙያ ሥጋውን ባይነት ባይነቱ መደበ።
5. ሀ. በጣለው ኃይለኛ ዝናብ ምክንያት ወንዙ ደፈረሰ።
   ለ. ጓደኛዬ ለሊቱን ሙሉ ትምህርቱን ሲያጠና በማደሩ ዐይኑ ደፈረሰ።

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት ሊያስገኙ የሚችሉትን የተለያየ አውዳዊ ፍች የሚያመለክቱ አረፍተነገሮች ከጻፉችሁ በኋላ አውዳዊ ፍቻቸውን ግለጹ።**

ምሳሌ፡-

ቃል -- ቆረጠ

ሀ. የሂሳብ ባለሙያዋ ከሠራተኞች ደሞዝ ላይ የጡረታ ተቀማጭ ገንዘብ ቆረጠች።

አውዳዊ ፍች፡ ቀነሰች (ቀንሳ ወሰደች)

ለ. ፀጉር አስተካካይዋ የደንበኛውን ፀጉር ቆረጠች።

አውዳዊ ፍች፡ አሳጠረች፣ አስተካከለች፣ ከረከመች

ሐ. ተማሪዋ በፈተና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ቆረጠች።

አውዳዊ ፍች፡ ወሰነች

1. መዋል
2. ምንጭ
3. ሳለ
4. ቀሸረ
5. በራሪ

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ቀጥሎ ስለአረፍተነገር አይነቶችና ስልቶች ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። መምህራችሁ የሚያደርጉላችሁን ማብራሪያና ምሳሌ መሠረት አድርጋችሁ የቀረቡትን መልመጃዎች ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## የአረፍተነገር አይነቶች

አረፍተነገር በስርዓት ተቀነባብሮ ሙሉ ሀሳብን ማስተላለፍ የሚችል የቃላት ወይም የሀረጎች ስብስብ ነው።

አረፍተነገርን የሚያስገኙት መሰረታዊ ተዋቃሪዎች ስማዊ ሀረግ እና ግሳዊ ሀረግ ናቸው። እነዚህ ተዋቃሪዎች በሁሉም ረገድ የተስማሙ ሆነው መገኘት አለባቸው።

በአረፍተነገሩ ውስጥ የገቡት ሀረጎች ከሚይዟቸው የግስ ብዛት አንጻር ነጠላ እና ውስብስብ አረፍተነገር ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ነጠላ አረፍተነገር፡ በውስጡ አንድ ግስን የሚይዝ፣ ከአንድ ነጠላ ስማዊ ሀረግና ከአንድ ነጠላ ግሳዊ ሀረግ የሚመሰረት የአረፍተነገር ዓይነት ነው።

ምሳሌ፡ አውሮፕላኑ በሰዓቱ ደረሰ።

ስማዊ ሀረግ፡ አውሮፕላኑ

ግሳዊ ሀረግ፡ በሰዓቱ ደረሰ

በምሳሌው ላይ እንደሚታየው "አውሮፕላኑ" ነጠላ ስማዊ ሀረግ፣ "በሰዓቱ ደረሰ" ነጠላ ግሳዊ ሀረግ በመሆናቸው የተነሳ አረፍተነገሩን ነጠላ ያሰኘዋል። በአረፍተ ነገሩ ውስጥም የሚገኘው የግስ ብዛት አንድ ብቻ ነው። ውስብስብ አረፍተነገር፡ ከአንድ በላይ ግስን የሚይዝ ወይም በውስጡ ሌላ ያላሰረ አረፍተነገርን የሚይዝ የአረፍተነገር ዓይነት ነው።

ምሳሌ፡ ትላንት የተሸለሙት ተማሪዎች ስለተደሰቱ ወደመዝናኛቦታ

ሄዱ።

ስማዊ ሀረግ፡ ትላንት የተሸለሙት ተማሪዎች

ግሳዊ ሀረግ፡ ስለተደሰቱ ወደመዝናኛ ቦታ ሄዱ

ምሳሌው ላይ የሚገኘው ስማዊ ሀረግ በውስጡ "ትናንት የተሸለሙት" የሚለውን ያላሰረ አረፍተነገር ይዟል። ግሳዊ ሀረጉም "ስለተደሰቱ" የሚለውን ጥገኛ አረፍተነገር ይዟል። በዚህም ምክንያት በአረፍተ ነገሩ ውስጥ ሦስት ግሶች በመገኘታቸው አረፍተነገሩን ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል።

## መልመጃ አራት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ አረፍተነገር በማለት ለዩ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።**

1. ሀገር መከበሪያ ናት።
2. ወርቃዊ ገቢው ስለጨመረ የቤተሰቡ ኑሮ ተሻሻለ።
3. ሰዎች ለሁላችንም በአንድ ወይም በሌላ መንገድ አንድ ውለታ ውለውልናል።
4. የሥራ ፍቅር ያለው የትም ቢቆፍር ወርቅ ያገኛል።
5. ሰዓቱ ስለደረሰ ወደየቤታችን እንሂድ።

ለ. ከዚህ በታች በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ነጠላ እና ውስብስብ አረፍተነገሮች ለይታችሁ አውጡ።

አንድ ገበሬ በጣም የሚወደው ፈረስ ነበረው። ፈረሱ ገበሬውን ለብዙ ዓመታት አገልግሏል። ፈረሱ ለቤተሰቡ ብቸኛው መተዳደሪያቸው ነበር። አንድ ቀን ፈረሱ ሜዳ ላይ ሳር እየጋጠ ሳያስበው የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ወደቀ። ከጉድጓዱ ለመውጣት ብዙ ታገለ፤ ግን ደግሞ መውጣት አልቻለም። ትንሽ ቆይቶ ፈረሱ ውሃው ጉድጓድ ውስጥ መውደቁን ገበሬው ሰምቶ በከፍተኛ ሀዘን ውስጥ ሆኖ ወደ ጉድጓዱ ቀረበ። ከጉድጓዱ ጫፍ ቆሞ በጭንቀት ሲያየው ፈረሱ ቀና ብሎ ተመለከተ። ፈረሱ የገበሬውን ማዘን ሲያይ ከጉድጓዱ ሊያወጣው እንደሚችል ተስፋ አደረገ። …

1. ነጠላ አረፍተነገር

ሀ. ________________

ለ. ________________

ሐ. ________________

2. ውስብስብ አረፍተነገር

ሀ. ________________

ለ. ________________

ሐ. ________________

## የአረፍተነገር ስልቶች

አረፍተነገሮች በተነገሩበት ስልት መሠረት ከሚኖራቸው ተግባራት አንጻር አታች (ሀተታዊ)፣ መጠይቃዊ፣ ትእዛዛዊ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡

1. ሐተታዊ አረፍተነገር፡ ስለአንድ ድርጊት ወይም ሁነት አሉታዊ ወይም አዎንታዊ የሆነ አስተያየት የሚሰጥ የአረፍተነገር አይነት ነው።

1.1. አዎንታዊ አረፍተነገር፡ አንድ ድርጊት በተወሰነ ቦታ እና ጊዜ፣ በተወሰነ ምክንያት የተፈጸመ ወይም የተከሰተ መሆኑን ያትታል፤ ይገልጻል። ምሳሌ፡ የአካባቢያችን ነዋሪዎች በነቂስ ወጥተው አካባቢውን አጸዱ።

1.2. አሉታዊ አረፍተነገር፡ የአዎንታዊ አረፍተነገር ተቃራኒ ነው። ይህም ማለት በአዎንታዊ መንገድ የቀረበን ሀሳብ የሚያፈርስ ወይም የሚቃረን አረፍተነገር ነው።

ምሳሌ፡

የአካባቢያችን ነዋሪዎች በነቂስ ወጥተው አካባቢውን አላጸዱም።

2. መጠይቃዊ አረፍተነገር፡ በአንድ ሀተታዊ አረፍተነገር ስለተገለጸ ድርጊት ወይም ሁነት ጥያቄ የሚሰነዝር የአረፍተነገር ዓይነት ነው። የሚሰነዘረው ጥያቄ በሁለት አይነት መልኩ ሊሆን ይችላል። አንደኛው ያልታወቀ ነገርን ለማወቅ፣ ሁለተኛው ደግሞ የታወቀ ነገርን ለማረጋገጥ ሲፈለግ የሚቀርብ ጥያቄ ነው።

ምሳሌ፡ ሀ. ማን አካባቢውን አጸዳ? (ያልታወቀ ነገርን ለማወቅ)

ለ. የከተማው ነዋሪ በነቂስ ወጥቶ አካባቢውን አጸዳ እንዴ?

(የታወቀ ነገርን ለማረጋገጥ)

1. ትእዛዛዊ አረፍተነገር፡ አንድ ሰው አንድ ተግባር እንዲፈጽም ሲፈለግ ትዕዛዝ የሚሰጥበት የአረፍተነገር ስልት ነው። ይህ አረፍተነገር በሁለት አይነት መንገድ ሊቀርብ ይችላል። አንደኛው ቀጥተኛ (ርቱእ) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ኢቀጥተኛ (ኢ-ርቱእ) አቀራረብ ነው።

ምሳሌ፡ ሀ. ወደክፍል ግቡ (ቀጥተኛ ትእዛዛዊ አረፍተነገር)

ለ. ወደክፍል ይግቡ (ኢቀጥተኛ ትእዛዛዊ አረፍተነገር)

## መልመጃ አምስት

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን አረፍተነገሮች ስልታቸውን ለዩ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።

1. የመኪናውን ፍጥነት ቀንሺ።
2. የህጻሴው ግድብ የውሃ ሙሌት ደረጃ በደረጃ ተጠናቀቀ።
3. የተዋስከውን መጽሐፍ መልስ።
4. ትልቅ ሥራ ለመስራት እድሜ አይገድበውም።
5. የስኬት መሰረት የሆነው ምንድን ነው?

ለ. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ከእያንዳንዳቸው የአረፍተነገር ስልት አይነቶች ሦስት ሦስት አረፍተነገሮችን መስርቱ።

1. ሐተታዊ አረፍተነገር

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

2. መጠይቃዊ አረፍተነገር

ሀ. ______________________

ለ. ______________________

ሐ. ______________________

3. ትእዛዛዊ አረፍተነገር

ሀ. ______________________

ለ. ______________________

ሐ. ______________________

ሐ. በሚከተለው ሠንጠረዥ በተ.ቁ. 1 ላይ በቀረበው መሠረት የተጓደሉትን የአረፍተነገር ስልቶች አሟልታችሁ ጻፉ።

| ተ.ቁ | ሐተታዊ አረፍተነገር | መጠይቃዊ አረፍተነገር | ትእዛዛዊ አረፍተነገር |
|---|---|---|---|
| 1 | በሕክምና ሙያ ሰለጠኑ። | በምን ሙያ ሰለጠኑ? | በሕክምና ሙያ ይሰልጥኑ። |
| 2 | | ትምህርት ቤቱ መቼ ተዘጋ? | |
| 3 | | | ሁሌም ፈተና ስለሚኖር ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ። |
| 4 | ሥራ አስኪያጁ ወደ አዳራሹ ገቡ። | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 5 | | | በቂ መረጃ ሳይኖራችሁ አስተያየት ከመስጠት ተቆጠቡ። |
| 6 | ጊዜያችሁን በአግባቡ ተጠቅማችኋል። | | |

## የምእራፉ ማጠቃለያ

በምእራፍ አንድ የቋንቋ ምንነትና ተግባራትን በማዳመጥ ክፍል ውስጥ ተምራችኋል። በክፍል ሁለትም ዘገባ በቃልና በጽሑፍ ሊቀርብ እንደሚችል ተምራችኋል። በክፍል ሦስት የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያትን ተምራችኋል። በምንባብ መሠረትም ቋንቋዎች በዘፈቀዳዊነት፣ በስርአታዊነት፣ በምሉእነት፣ ወዘተ. ባህርያት ሊመሳሰሉ እንደሚችሉ አንብባችኋል።

ቃላት በአረፍተነገር ውስጥ የሚሰጡት ፍቺ አውዳዊ ፍቺ ተብሎ ይጠራል። የቃላትን አውዳዊ ፍቺ በሚመለከት በክፍል አምስት በቀረበላችሁ መልመጃ አማካይነት ተለማምዳችኋል። በሰዋስው ክፍል የአረፍተነገር አይነቶችንና ስልቶችን በሚመለከት ተምራችኋል። በዚህም ውስጥ በአረፍተነገሩ ውስጥ የሚገኘውን የግስ ብዛት (መጠን) መሠረት በማድረግ ነጠላ እና ውስብስብ ተብለው ሊከፈሉ እንደሚችሉ ተምራችኋል። አረፍተነገሮች ከሚኖራቸው ተግባር አንፃርም ሐተታዊ፣ መጠይቃዊ እና ትእዛዛዊ ተብለው ሊከፈሉ እንደሚችሉ ተመልክታችኋል።

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቋንቋን ምንነትና አገልግሎት ግለጹ።
2. ከቋንቋዎች መሠረታዊ ባህርያት ውስጥ ሦስቱን በመጥቀስ አብራሩ።
3. ሁለት ቃላትን በመጠቀም አውዳዊ ፍቺያቸውን በአረፍተነገር ውስጥ አመልክቱ።
4. የአረፍተነገር ዓይነቶችን በምሳሌ አብራሩ።
5. የአረፍተነገር ስልቶችን የሚያመለክቱ አረፍተነገሮችን ጻፉ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምእራፍ አንድ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች መልሳችሁ አንብቡ።

| | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የተነበበውን ምንባብ አድምጬ ተረድቻለሁ | | | |
| 2 | የቋንቋን ምንነትና ተግባራት ተረድቻለሁ | | | |
| 3 | የዘገባን አቀራረብ መንገዶች መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 4 | የቀረበውን ምንባብ አንብቤ ተረድቻለሁ | | | |
| 5 | የቋንቋን መሠረታዊ ባህርያት መዘርዘር ችያለሁ | | | |
| 6 | ለቃላት ዐውዳዊ ፍቺ መስጠት ችያለሁ | | | |
| 7 | የአረፍተነገር አይነቶችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 8 | የአረፍተነገር ስልቶችን መመስረት ችያለሁ | | | |

# ምእራፍ ሁለት

# ግብር

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ጠቃሚና እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ መረጃዎችን ትለያላችሁ።
- ሀሳባችሁን በራስ መተማመን ትገልጻላችሁ።
- ከጽሑፉ ውስጥ ጠቃሚ መልእክትን አንብባችሁ ትመዝናላችሁ።
- መረጃዎችን ትተረጉማላችሁ።
- የፌደል አሰዳደርን ለማረጋገጥ መዝገበ ቃላትን ትጠቀማላችሁ።
- አንቀጽ ትጽፋላችሁ።
- የተለያዩ የጊዜ አመልካች ግሶችን ለንግግርና ለጽሕፈት ትጠቀማላችሁ።

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት "የግብር ጠቀሜታና አጀማመር" በሚል ርእስ የቀረበ ጽሁፍ መምህራችሁ ያነቡላችኋል። እናንተም አዳምጣችሁ የቀረቡትን ጥያቄዎች በተገቢው መንገድ ስሩ።

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩባቸው፤ የውይይታችሁንም ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

   ሀ. ግብር ምንድን ነው?

   ለ. ግብር መክፈል ለምን ይጠቅማል?

2. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ።

   ሀ. ግብር ለ. ማነቃቃት ሐ. መገባደጃ መ. አዋጅ

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ግብር መክፈል የተጀመረው መቼ ነው?
2. ለዘመናዊ የግብር ሥርአት ብቅ ብቅ ማለት በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀሰው አገር ማን ናት?
3. በኢትዮጵያ ግብር መክፈል የተጀመረው መቼ ይመስላችኋል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ባዳመጣችሁት መሠረት የሚከተሉትን ሀሳቦች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሀሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. ግብር በግዴታና በውዴታ ለመንግስት የሚከፈል መዋጮ ነው።
2. የታዳጊ ሃገር ዜጎች ግብር መክፈል አይጠበቅባቸውም።

3. ግብር መክፈል ከመንግስት መቋቋም ጋር እንደተጀመር ይታመናል።

4. በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የግብር አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣው እ.ኤ.አ በ1942 ዓ.ም ነው።

ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡትን ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ጽሁፍ መሠረት በማድረግ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. ግብር መክፈል ለአንድ ሀገር ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ሀ. ኢንቨስትመንትን ያበረታታል።

ለ. ማህበራዊ አገልግሎትን ለማስፋፋት ያስችላል።

ሐ.. የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ያስችላል።

መ. ሁለም ጠቀሜታዎች ናቸው።

2. በጥንታውያን ግሪክ፣ ሮማ፣ ፐርሺያና ግብፅ ይከፈሉ ከነበሩት የግብር ዓይነቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

ሀ. ጥንታዊ ሳንቲሞች　　　　ለ. የከበሩ ማእድናት

ሐ. የጋማ ከብቶች　　　　መ. ልጆቻቸው

3. በጥንት ዘመን ግብር መክፈል እንደተጀመረ በማስረጃነት የሚቀርበው ምንድን ነው?

ሀ. ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች

ለ. የታሪክ ድርሳናት

ሐ. የዋሻ ላይ ስእሎች

መ. በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትመው የወጡ አዋጆች

4. በሀገራችን የስራ ላይ ግብር የዋለው በስንት ዓመተምህረት ነው?

ሀ. በ1941　　　　ለ. በ1943

ሐ. በ1942　　　　መ. በ1944

**ሐ. ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሠረት ለርእሱ ጠቃሚና እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ ሀሳቦችን በመለየት ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ አስፍሩ።**

| ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦች | እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ ሀሳቦች |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት የዘገባና የክርክር ማስታወሻ እንዲሁም ተግባራት ቀርቦላችኋል። ተግባራቱን በትእዛዛቸው መሰረት ስሩ፤ ማስታወሻውንም በትኩረት አጥኑ።

## ተግባር አንድ

ግብርን በሚመለከት ከመገናኛ ብዙኃን (ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥን፣ ወዘተ.) ወይም ከተለያዩ ጽሑፎች ያነበባችሁትን መረጃ መነሻ በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ቃላዊ ዘገባ አቅርቡ።

## ዘገባ

ዘገባ አንድን ክንውን ወይም ሂደት በሚመለከት ለሌላ ወገን ክንውኑን ወይም ሂደቱን አስመልክቶ በቃል ወይም በጽሁፍ የሚያቀርብ ኢ-ልቦለድ ድርሰት ነው። ዘገባ ሀቅን ወይም እውነትን መሰረት በማድረግ የሚቀናበር እንጂ ፈጠራ አይደለም። ለምሳሌ ጉዞን፣ አደጋን፣ ልማትን በልዩ ልዩ ርእሶች ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶችን እና ሌሎች ጉዳዮች ሊዳስስ ይችላል። ዘገባ እንዳስፈላጊነቱ በቃል ወይም በጽሁፍ ሊቀርብ ይችላል። ከሁለቱ የአቀራረብ መንገዶች ውስጥ አንዱን ለመምረጥ ከሚያስገድዱን ሁኔታዎች ውስጥ ዋነኛው የዘገባው አይነትና ባህርይ፣ ዘገባው የሚቀርብበት ምክንያት፣ ዘገባው የሚቀርብላቸው ሰዎች ማንነት ይጠቀሳሉ። አብዛኛውን ጊዜ ግን የሚቀርበው በጽሁፍ ነው። ቃላዊ ዘገባ አንድን ክንውን ወይም ሂደት በሚመለከት በጽሑፍ ሳይሆን በቃል ድርጊቱን ወይም ሁኔታውን በሚመለከት ይቀርባል።

## ተግባር ሁለት

በቡድን በመሆን ከዚህ በታች ከቀረቡት ርእሶች አንዱን በመምረጥ የክርክር አቀራረብ ሂደትን በመከተል ክርክር አካሂዱ።

ሀ. በግብር መክፈል ጥቅምና ጉዳት ላይ ክርክር አድርጉ።

ለ. ግብር ከፋዮች በአግባቡ ግብር ቢከፍሉ ተጠቃሚ የሚሆነው ህብረተሰብ ነው ወይስ ግለሰብ።

## የክርክር ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ

ክርክር በአንድ ርእሰ ጉዳይ ላይ ሁለት ተቃራኒ አመለካከት ባላቸው ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል ለማሸነፍ፣ ተናግሮ ለማሳመን የሚካሄድ ስርዓታዊ ሙግት ነው። በሙግቱ ሂደትም የተሟጋቾችን (የተከራካሪዎቹን) ሀሳብ መዝነው ፍርድ የሚሰጡ ዳኞች ይኖራሉ።

ለክርክሩም ሁለቱ ተቃራኒ እይታ ያላቸው ወገኖች በቂ ዝግጅት ማድረግና የክርክር አቀራረብ ስልትን ማወቅ፣ መከተል ይኖርባቸዋል።

ተከራካሪ ወገኖች በክርክር የቅድመዝግጅት ወቅት ማከናወን ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ በርእሱ ዙሪያ ከመረጃ ምንጮች መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ ለክርክሩ ጠቃሚ የሆኑትን መምረጥና በቅደም ተከተል ማደረጀት፣ ልምምድ ማድረግ፣ ወዘተ. ይጠቀሳሉ።

ተከራካሪ ወገኖች ክርክር በሚያቀርቡበት ወቅት ደግሞ በመደገፍ ወይም በመቃወም የሚከራከሩበትን የክርክር ርእስ ለአድማጭ ማስተዋወቅ፣ በልበ ሙሉነት የመከራከሪያ ሀሳቦችን በመረጃ በማስደገፍ በቅደም ተከተል ማቅረብ፣ ሀሳብን በተገቢው የአካል እንቅስቃሴ ማቅረብ፣ በተቃዋሚዎች የሚነሱትን ሀሳቦች በትክክል መመዝገብና የተቃውሞ ሀሳብን ማዘጋጀት፣ ለክርክሩ የተሰጠን ጊዜ በአግባቡ መጠቀም፣ ሲጨርሱ በምስጋና ማጠቃለል፣ ውጤትን በጸጋ መቀበል፣ ወዘተ፣ ይጠቀሳሉ።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት "ግብር እና አይነቶቹ" የሚል ምንባብ ቀርበላችኋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የቀረበላችሁን የቅድመማንበብ፣ የአንብቦ መረዳት እና የድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ስሩ።

## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ ወይም በቡድን ተወያዩ።

1. የአንድ ሀገር ዜጎች ግብር የሚከፍሉት ለምን ይመስላችኋል?
2. ነጋዴዎች ግብር ባይከፍሉ ምን የሚገጥማቸው ይመስላችኋል?
3. የምታውቋቸውን የግብር ዓይነቶች ዘርዝሩ።

4. የሚከተሉትን ቃላት የመዝገበቃላዊ ፍቺ ስጡ።

ሀ. ካፒታል ሐ. ቀረጥ

ለ. በጀት መ. ቴምብር ሠ. ጉሙሩክ

# ግብር እና አይነቶቹ

ግብር መንግስት የልማት እና የመልካም አስተዳደር አላማውን እንዲያሳካ ለመደገፍ ከግብር ከፋዮች የሚሰበስበው ገቢ ነው። በህግ መሠረት ግብር ሊከፈለበት የሚገባ ገቢ የሚያገኝ ማንኛውም ለምርትና አገልግሎት ወጪ የሚፈጽም ሰው ወይም ድርጅት ግብር ከፋይ ተብሎ ይታወቃል።

ግብር የውዴታ ግዴታ መዋጮ ሆኖ የሚሰበሰበው ለጋራ ጥቅም ነው። መንግስት ከነዋሪው የሚሰበስበውን ግብር እያንዳንዱ ግለሰብ ምን ያህል እንደሚከፍል ግምት ውስጥ ሳያስገባ ሁሉንም እኩል ተጠቃሚ ሊያደርጉ በሚችሉ ተግባራት ላይ እንዲውል ያደርጋል። ግብር የሚጣለው በተገኘ ጥቅም ላይ ነው። ምንም እንኳን ግብር የግዴታ መዋጮ ቢሆንም የትኛውንም ሰው ግብር የሚያስከፍል ገቢ (ጥቅም) ካላገኘ በስተቀር እንዲከፍል አይገደድም።

መንግስት ግብር የሚጥለውና የሚሰበስበው የተለያዩ አላማዎች ለማሳካት ነው። ከአላማዎቹ ውስጥም ገቢን በመሰብሰብ ለሚያከናውነው የልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎች እንዲውል ለማስቻል፣ የሀብት ክፍፍልን ለማመጣጠን፣ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት፣ ለህብረተሰቡ ጠንቅ የሆኑ ፍጆታዎች እንዳይበረታቱ ለማድረግ፣ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ወይም ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ የካፒታል ግንባታንና ክምችትን ለማፋጠን፣ የክልሎችን እድገት ለማመጣጠን፣ ውስን የሆነውን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም፣ የወጪ ንግድ ለማበረታታት፣ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ወይም የስራ እድልን ለመፍጠር፣ የህብረተሰቡን የገቢ አቅም ለማሳደግ፣ ወዘተ. ይጠቀሳሉ።

ግብር ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ይሰበሰባል። ገቢ ማለት ማንኛውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን፣ በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማንኛውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይንም በአይነት በማንኛውም መልክ ለግብር ከፋዩ የተከፈለውን፣ በስሙ የተያዘውን፣ ወይንም የተቀበለውን ጥቅም ሁሉ ይጨምራል። የገቢ ምንጮች የሚባሉት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣ መኖሪያ ቤትን ወይንም ድርጅትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣ ከንግድ ስራ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ፣ የማዝናናት ሥራ ከሚሰራ ሙዚቀኛ ወይንም ስፖርተኛ በግል ካከናወነው ሥራ የሚያስገኘው ገቢ፣ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልሆነ ሰው በቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት አማካይነት ከሚያከናውነውየንግድ ሥራ የሚያስገኘው ገቢ፣ ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የሚገኘ ገቢ፣ ከከብት እርባታ ከግብርና እና ከደን የሚገኝ ገቢ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ ቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሸጥ የሚገኝ ገቢ፣ ወዘተ. ናቸው። በተለያዩ ጊዜያት በኢኮኖሚው ውስጥ በሚደረጉት ለውጦችና መሻሻል መነሻ ተጨማሪ የገቢ ምንጮች ሊፈጠሩ ወይንም የነበሩት ሊቀሩ ይችላሉ።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. መንግስት ግብር የሚሰበስበው ለምንድን ነው?
2. ግብር ከሚሰበሰብባቸው የገቢ ምንጮች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ።
3. የምታውቋቸው የግብር አይነቶች ካሉ ጥቀሱ።

የግብር ገቢ በሁለት ዋና ዋና መደቦች ይፈረጃሉ። አንደኛው ቀጥተኛ ግብር ሲሆን፣ ማንኛውም ግለሰብ ወይንም ድርጅት ከሚያገኘው ገቢ ላይ እራሱ በቀጥታ የሚከፍለው የግብር ዓይነት ነው። በዚህ ውስጥም ከመቀጠር፣ ከቤት ኪራይ፣ ከንግድ ሥራዎች እና ከሌሎች ገቢዎች የሚገኙ የገቢ ግብሮች ይካተታሉ። ሌሎች ገቢዎች በመባል የሚጠቀሱት ከእድል ሙከራ አሸናፊነት፣ የፈጠራ

መብትን በማከራየት፣ ከካፒታል ዋጋ እድገት፣ ከወለድ፣ ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚሰጥ አገልግሎት፣ ከአክሲዮን የትርፍ ድርሻ፣ ቋሚ ባልሆነ ሁኔታ ከንብረትና ኪራይ የሚገኙ ገቢዎች ናቸው።

የደመወዝ ገቢ ግብር ማንኛውም ሰው ቀጥሮ ከሚያሰራቸው ሠራተኞች ላይ የሥራ ግብር ይቀንሳል። በየወሩ ከሠራተኞች ደመወዝ ተቀንሶ የሚሰበሰበውን የስራ ግብር ቀጣሪው ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለግብር ባለሥልጣን ይከፍላል። የዲፕሎማቲክ መብት ባላቸው ድርጅቶች የሚሠሩና ከአንድ በላይ ለሆኑ ቀጣሪዎች የሚሠሩ ሠራተኞች እራሳቸው አስታውቀው ይከፍላሉ።

የቤት ኪራይ ግብር ቤትና ከቤት ጋር የተያያዙ ንብረቶችን በማከራየት የሚገኝ ገቢ ነው። ገቢውን የሚያገኘው ሰው በግብር ከፋዩ ደረጃ ላይ ተመስርቶ ከበጀት ወይም ከሂሣብ አመቱ ማለቂያ ጀምሮ ከአንድ እስከ አራት ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ አስታውቆ ይከፍላል። የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ደግሞ ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በተገኘ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ነው። የገቢ ማስታወቂያ የሚቀርበው በግብር ከፋዮች ደረጃ ላይ ተመስርቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ ከአንድ እስከ አራት ወራት ውስጥ ነው።

ሁለተኛው የግብር አይነት ቀጥታ ያልሆነ ግብር ነው። ቀጥታ ያልሆነ ግብር በማምረት፣ በአገልግሎትና ምርት ሽያጭ አማካይነት ከተጠቃሚው የሚሰበሰብ ነው። የግብሩ መሠረት ለምርትና አገልግሎት የሚከፈል ወጪ ሲሆን ግብሩም የምርት ወይም የወጪ ግብር ይባላል። በአገራችን የሚታወቁት ዋና ዋና ቀጥታ ያልሆኑ የግብር አይነቶች የሚባሉት የኤክሳይዝ ታክስ፣ የተርን ኦቨር ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የቴምብር ቀረጥ እና የጉምሩክ ቀረጥ ናቸው።

የኤክሳይዝ ታክስ በአገር ውስጥ ሲመረቱም ሆነ ከውጪ ሲገቡ

በተመሳሳይ ተመን የሚከፈል ግብር ነው። ማህበራዊ ጠቀሜታ ከሌላቸው፣ መሠረታዊ እና የቅንጦት ከሆኑ ምርቶች ግብሩ ይሰበሰባል። የግብሩ መሠረት ለአገር ውስጥ ምርቶች የማምረቻ ዋጋ ሲሆን፣ ከውጪ ለሚገቡት ግን የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ነው።

ተርን ኦቨር ታክስ በእቃ ወይም በአገልግሎት ሽያጭ ላይ የሚከፈል ግብር ነው። የግብር ማስከፈያ መሠረት የመሸጫ ዋጋው ነው። ግብሩን የሚሰበስቡት በዓመት ከብር 500000 በታች ገቢ ያላቸው ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ የማይጠበቅባቸው ግብር ከፋዮች ናቸው።

የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈለው በእቃ ወይም በአገልግሎት ማምረት ወይም በንግድ ግብይት ሂደት በሁሉም ደረጃ በሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት ላይ ነው። የግብሩ መክፈያ ጊዜው ወርሃዊ ሆኖ የሚቀጥለው ወር ከማለቁ በፊት ይከፈላል። የግብር ተደራራቢነትን ለማስቀረት በግብአት ላይ የተከፈለው ግብር ከመጨረሻ ምርት ግብር ላይ ይቀናነሳል። ይህም በአንድ ምርት ላይ ተደጋጋሚ ግብር እንዳይከፈል ያደርጋል። የግብር ተደጋጋሚነት በማስቀረትም የግብር ፍትሃዊነትን ይፈጥራል።

የቁርጥ ታክስ ስርዓት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረትና እቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ ስለሚከፈል ግብሩ የቁርጥ ግብር አስተዳደር አንዱ አካል ነው። ስርአቱም የግብር አሰባሰብን ለማቀላጠፍ የሚያገለግል ነው። ከመደበኛየግብር አስተደደር ተግባሮች የሚያመልጡትን ግብይቶች ከምንጩ ለመያዝ ያግዛል።

የቴምብር ቀረጥና ሽያጭ የሚፈፀመው መብት ወይም ግዴታ የተመሠረተበት፣ የተመዘገበበት፣ የተላለፈበት ማንኛውም ሰነድ ላይ ነው። የቀረጡ አከፋፈል በቁርጥ እና በዋጋ ላይ በመቶኛ ሆኖ እንደሰነዱ ይዘትና ዋጋ ይለያያል። የቴምብር ቀረጡ ከብር 50

በላይ የሚያስከፍል ሰነድ ሲያጋጥም ገንዘቡ ከተከፈለ በኋላ በሰነዶቹ ላይ ቀረጡ ስለመከፈሉ በማህተም ይረጋገጣል። ሰነዱ የያዘው ጉዳይ ከብር 50 በታች የሚያስከፍል ሲሆን የቴምብር ቀረጡ ከ0.10 ሣንቲም ጀምሮ እስከ 20 ብር ያለውን ቴምብር በመለጠፍ ይፈፀማል።

(ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን (2002) ስለግብር/ታክስ አስተዳደር አስመልክቶ ከተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ ማብራሪያ ላይ ተሸሽሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንድ ወይም በቡድን በመወያየት በቃል መልሱ።

1. የቀጥተኛ ታክስ አይነቶችን የሚገልፁ አንቀጾች የትኞቹ ናቸው?
2. የኢ-ቀጥተኛ ታክስ አይነቶችን የሚገልጹ አንቀጾች የትኞቹ ናቸው?
3. በምንባቡ ውስጥ ደምቀው የተጻፉ ቃላትና ሀረጋት ያላቸውን ፍቺ በቡድናችሁ ተወያይታችሁበት ለክፍል ተማሪዎች አብራሩ።
4. የምንባቡን አንደኛ አንቀጽ ሀሳብ በራሳችሁ አገላለጽ ለቡድን አባላት አቅርቡ።
5. የምንባቡን ሀሳብ አጠቃላችሁ ለቡድን አባላት አቅርቡ።

ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ትክክል ለሆኑት “እውነት”፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ “ሐሰት” በማለት በቃል መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።

1. ግብር የግዴታ መዋጮ ነው ።
2. ማንኛውም ሰው ግብር የሚያስከፍል ገቢ እስካላገኘ ድረስ እንዲከፍል አይገደድም።
3. ቀጥተኛ ግብር በማምረት፣ በአገልግሎትና በምርት ሽያጭ ከሚያገኙት ተጠቃሚዎች ላይ የሚሰበሰብ ነው።

4. የቁርጥ ታክስ ስርዓት ከመደበኛ የግብር አስተዳደር ተግባራት የሚያመልጡትን ግብይቶች ከምንጩ ለመያዝ ያስችላል።
5. ግብር የሚሰበሰበው የመንግስትን የገቢ መጠን ለመጨመር ብቻ ነው።

**ሐ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በምረጥ መልሱ።**

1. ከቀጥተኛ የግብር ዓይነቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

   ሀ. የጉምሩክ ቀረጥ  ለ. የንግድ ስራ ግብር

   ሐ. የደመወዝ ገቢ ግብር  መ. የቤት ኪራይ ገቢ ግብር

2. ስለግብር ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ግብር የሚሰበሰበው ለጋራ ጥቅም ነው።

   ለ. ግብር የውዴታ ግዴታ መዋጮ ነው።

   ሐ. ግብር የሚጣለው በተገኘ ጥቅም ላይ ነው።

   መ. ግብር የሚከፈል ስራ አጥነትን ለማሳደግ ነው።

3. ማህበራዊ ጠቀሜታ ከሌላቸው፣ መሠረታዊ እና የቅንጦት ከሆኑ ምርቶች የሚከፈል ግብር ምን ይባላል?

   ሀ. ተርን ኦቨር ታክስ  ለ. ኤክሳይዝ ታክስ

   ሐ. የተጨማሪ እሴት ታክስ  መ. የንገድ ስራ ግብር

4. “መንግስት ግብር ከሚሰበስብባቸው ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የሀብት ክፍፍልን ለማመጣጠን ነው።” የሚለው ምንን ይገልጻል?

   ሀ. ሀብታም እና ድሃ እኩል እንዲሆኑ ለማድረግ

   ለ. የሀገሪቱን ሃብት እኩል ለዜጎች የየድርሻቸውን ለማከፋፈል

   ሐ. የዜጎችን ፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ

   መ. ዜጎች ተመሳሳይ የሆነ ገቢ እንዲኖራቸው ለማድረግ

5. መንግስት ግብር ከሚሰበስብባቸው ምክንያቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው?

ሀ. ኢኮኖሚን ለማረጋጋት

ለ. የውጭ ንግድን ለማበረታታት

ሐ. የክልሎችን እድገት ለማመጣጠን

መ. ጎጂ የሆኑ እሴቶችን ለማበረታታት

# ትምህርት አራት፡ መፃፍ

ከዚህ በታች አንቀጽ እንድትጽፉ የሚያደርጉ መልመጃ ቀርቦላችኋል። ስለአንቀጽ የቀረበላችሁን ማስታወሻ እና መምህራችሁ የሚሰጧችሁን ማብራሪያ መሠረት አድርጋችሁ አንቀጽ ጻፉ።

## አንቀጽ

አንቀጽ በሐሳብ ተዛምዶ የተሰናሰሉ አረፍተነገሮች የሰፈሩበት፣ በአንድ ድርሰት ውስጥ ተካተው ሊቀርቡ የሚገባቸውን ነጥቦች በተመጠነና ራሱን በቻለ ሁኔታ የሚያራምድ የጽሑፍ አካል ነው። ባጭር አገላለጽ ስለአንድ ዋና ጉዳይ የሚያወራ የአንድ ጽሑፍ ንዑስ ክፍል ነው። ሌላ የተለየ ሀሳብ መግለጽ ቢያስፈልግ ሌላ ሁለተኛ አንቀጽ ሊኖር ግድ ይላል።

“ስፖርት” በሚል ርዕስ አንድ አጭር ጽሁፍ ለመጻፍ የፈለገ ሰው የስፖርትን ጥቅምና ዓይነት የሚዳስስ ቢሆን፣ ሁለቱም ጉዳዮች በተለያየ አንቀጽ ራሳቸውን ችለው እንዲሰፍሩ ይደረጋል።

ምሳሌ፡

ትምህርት እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው። ሰዎች የሚያውቁትን የዚህን ዓለም ምስጢር መረዳት እና መጠቀም የሚችሉት በትምህርት ሃይል ነው። የራስን ኑሮ ማሻሻል፣ ሕዝብን መምራት እና ኑሮን መለወጥ የሚቻለው በትምህርት ነው። ትምህርት የሰዎችን አስተሳሰብ የሚያሻሽል፣ እንዲሁም መጥፎ ድርጊትን እና ባህርይን ለመከላከል እና ለማስወገድ የሚያስችል መሳሪያ ነው።

በአንቀጽ ውስጥ የሚገኙ አረፍተ ነገሮች ኃይለ ቃልና መዘርዝር አረፍተነገር ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ኃይለቃል በአንቀጹ ውስጥ የሚገኘውን ዋና ሐሳብ አጠቃሎ የሚይዝ ሲሆን፣ መዘርዝር አረፍተነገር ደግሞ ኃይለቃሉ የያዘውን ሀሳብ የሚያብራራ ነው።

ከላይ በቀረበው ምሳሌ ላይ የመጀመሪያው አረፍተነገር ማለትም "ትምህርት እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው።" የሚለው የአንቀጹ ኃይለቃል ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ደግሞ መዘረዝር አረፍተነገሮች ናቸው። በአንቀጹ ውስጥ ኃይለቃሉ ከሚገኝበት ቦታ አኳያ አንቀጽ አራት አይነት ቅርጽን ሊይዝ ይችላል። እነሱም፡

ሀ. ኃይለ ቃሉ በአንቀጹ መነሻ ላይ ሲገኝ ለ. ኃይለ ቃሉ በአንቀጹ መጨረሻ ላይ ሲገኝ

ሐ. ኃይለ ቃሉ በአንቀጹ መካከል ላይ ሲገኝ

መ. ኃይለ ቃሉ በአንቀጹ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ሲገኝ

## መልመጃ ሦስት

ሀ. ከዚህ በታች አንድ አንቀጽ የሚሆኑ የተለያዩ አረፍተነገሮች ተዘበራርቀው ቀርበዋል። እናንተ የአረፍተነገሮችን ቅደም ተከተል ካስተካከላችሁ በኋላ የተሟላ አንቀጽ አድርጋችሁ ጻፉ፤ የአንቀጹንም ኃይለቃል ለዩ።

1. በጥቅሉ ያለሰላም ወጥቶ መግባት፣ ነግዶ ማትረፍ፣ ወልዶ መሳም፣ ተምሮ መመረቅ ስለማይቻል ትልቅ ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል።

2. መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት እንዲሁም ሰዉ ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲኖር ሰላም አስፈላጊ ነው።

3. ሰላም ለሰዉ ልጆች በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ እና ወሳኙ ነው።

4. ሰላም የሰዎችን ደህንነት ለማስጠበቅና ለቀጣዩ ትውልድ የተሻለ ህይወትን ለመፍጠር ያስችላል።

ለ. ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ከደሞዝ ገቢ የሚከፈልን የግብር መጠን በቅደም ተከተል የሚመለከት መረጃ በመቶኛ ተገልጿል። የቀረበውን ቁጥራዊ መረጃ ወደአንቀጽ ቀይራችሁ ጻፉ። አንቀጻችሁ አንድ ኃይለቃልና ሰባት ዝርዝር አረፍተነገሮች እንዲኖሩት ይጠበቃል።

| በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በብር | ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን |
|---|---|
| 0 - 600 | 0% |
| 601 - 1,650 | 10% |
| 1,651 - 3,200 | 15% |
| 3,201 - 5,250 | 20% |
| 5,251 - 7,800 | 25% |
| 7,801 - 10,900 | 30% |
| 10,900 በላይ | 35% |

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት የቃላትን የመዝገበ ቃላትና አውዳዊ ፍችን የመለየት መልመጃ ስለቀረበላችሁ መልመጃውን በትእዛዙ መሠረት ስሩ።

## መልመጃ አራት

ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት በጥንድ በመሆን በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ካስተካከላችሁ በኋላ ፍቺያቸውን ከመዝገበ ቃላት በመፈለግ ጻፉ።

| | | |
|---|---|---|
| 1. ጨዋ | 4. ብራ | 7. አርማ |
| 2. የብስ | 5. ጠበቃ | 8. ዙፋን |
| 3. ገራገር | 6. ደባ | 9. ነጠፈች |

ለ. ከላይ በ“ሀ” ስር የቀረቡትን ቃላት አውዳዊ ፍች የሚያመለክቱ አረፍተነገሮች መስርቱ።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ቀጥሎ ስለሰዋስው ጊዜ የሚያብራራ ማስታወሻ ቀርቦላችኋል። መምህራችሁም የቀረበውን ማስታወሻ ያብራሩላችኋል። የቀረቡትን መልመጃዎች በትእዛዛቸው መሠረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## ጊዜ

እየተፈጸመ ያለን፣ የተፈጸመን እና የሚፈጸምን ድርጊት መሠረት በማድረግ በግሶች ላይ የሚታየውን የጊዜ ሁኔታ የአሁን ጊዜ፣ ሃላፊ ጊዜ እና የትንቢት ጊዜ በማለት መክፈል ይቻላል።

1. የአሁን ጊዜ፡ አንድ በአሁኑ ጊዜ በመፈጸም ላይ ያለ ድርጊትን ወይም ሁኔትን የሚገልጽ የጊዜ አይነት ነው። የአሁን ጊዜ ግስ "እየ- " የሚል ምእላድ ሊያስቀድም እና "ነው" የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል።

ምሳሌ፡

ሀ. ልጁ እየ-አጠና ነው።

3. 2. የሃላፊ ጊዜ፡ አንድ ድርጊት ከአሁን በፊት ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን የሚገልጽ የጊዜ ዓይነት ነው። ሃላፊ ጊዜ የዋህ ሃላፊ፣ የቅርብ ሃላፊና የሩቅ ሃላፊ ጊዜያት አሉት።

ሀ. የዋህ ሃላፊ ጊዜ፡ ጊዜውን በውል ማሳየት የማይችል፣ አንድ ድርጊት ባለፈ ጊዜ ተፈጽሞ ያለቀ መሆኑን ብቻ ያመለክታል።

ምሳሌ፡ ድርሰቷን ጽፋ ጨረሰች።

ለ. የቅርብ ሃላፊ ጊዜ፡ አንድ ድርጊት ከቅርብ ጊዜ በፊት የተፈጸመ ወይም ድርጊቱ ከተፈጸመ ብዙ ጊዜ ያልቆየ መሆኑን ያመለክታል።

ምሳሌ፡ መጽሐፉን ወስዷል።

ሐ. የሩቅ ሃላፊ ጊዜ፡ አንድ ድርጊት የተፈጸመበት ከሚነገርበት ጊዜ አንጻር ሩቅ መሆኑን ያመለክታል።

ምሳሌ፡ መጽሐፉን ወስዶ ነበር።

3. የትንቢት ጊዜ፡ አንድ ድርጊት ገና ያልተፈጸመ እና ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን ያመለክታል።

ምሳሌ፡ መጽሐፉን ይወስዳል።

(ምንጭ፡ ባየ ይማም (2000) "የአማርኛ ሰዋስው" ላይ ተሻሽሎ የተወሰደ)

## መልመጃ አምስት

### ሀ. ቀጥሎ የቀረቡት አረፍተነገሮች በየትኛው የጊዜ አይነት እንደቀረቡ ግለፁ።

1. የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት የስራ አመራሮች ቀጣይ ሳምንት ስብሰባ ያደርጋሉ።

2. ባለፈው ክረምት በአብዛኛው የሃገራችን ክፍል ከፍተኛ ዝናብ ነበር።
3. በብሔራዊ ቲያትር የስነጽሁፍ ውድድር ይካሄዳል።
4. መምህሩ ለተማሪዎቹ የፈተና ወረቀት እየመለሰ ነው።
5. ነጋዴው ህብረተሰብ ግብሩን በወቅቱ ከፍሏል።
6. ሀኪሙ ታማሚውን እየመረመረ ነው።

ለ. በ“ሀ” ስር ያሉትን ዓረፍተነገሮችን የሃላፊ ጊዜውን ወደትንቢት ጊዜ፣ የትንቢት ጊዜውን ወደአሁን ጊዜ፣ የአሁን ጊዜውን ወደሃላፊ ጊዜ በመለወጥ ጻፉ።

ምሳሌ፡

የትንቢት ጊዜ፡ የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት የስራ አመራሮች ቀጣይ ሳምንት ስብሰባ ያደርጋሉ።

የአሁን ጊዜ፡ የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት የስራ አመራሮች ስብሰባ እ ያደረጉ ናቸው።

ሐ. ለአሁን ጊዜ፣ ለሃላፊ ጊዜና ለትንቢት ጊዜ ሁለት ሁለት አረፍተነገሮችን መስርቱ።

## የምእራፉ ማጠቃለያ

ምእራፍ ሁለት ግብር በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን በስሩም የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል። በማዳመጥ ክፍል ውስጥ “የግብር ጠቀሜታ እና አጀማመር” በሚል ርዕስ የቀረበውን ጽሁፍ አዳምጣችሁ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ሰርታችኋል፤ በጽሑፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙትን ጠቃሚ እና እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ መረጃዎችን ለይታችኋል።

በክፍል ሁለት ግብርን በሚመለከት ከመገናኛ ብዙኃን ወይም ከተለያዩ መጻሕፍት ያነበባችሁትን መረጃ፣ እንዲሁም ከተለያዩ ምንጮች ያገኛችሁትን መረጃ መሠረት በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ቃላዊ ዘገባ አቅርባችኋል፤ የክርክር አቀራረብ ሂደትን በመከተልም ክርክር አድርጋችኋል።

በክፍል ሦስት “ግብር እና ዓይነቶቹ” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በማንበብ ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥታችኋል። በክፍል አራት ጽሕፈትን በሚመለከት በቀረቡት መልመጃዎች አማካይነት የተዘበራረቁ ዓረፍተነገሮችን ማስተካከልን፣ የተሟላ አንቀጽ መጻፍን፣ ቁጥራዊ መረጃዎችን በአንቀጽ መጻፍን ተምራችኋል።

በክፍል አምስት ቃላትን በፊደል ተራ ቅደም ተከተል በማስተካከልን፣ ፍቺያቸውን ከመዝገበቃል በመፈለግንና ትርጉማቸውን ሊያመለክቱ የሚችሉ ዓረፍተነገሮችን በመስራት ተለማምዳችኋል።

በክፍል ስድስት ደግሞ የአሁን ጊዜን፣ ሃላፊ ጊዜን እና የትንቢት ጊዜን ሊያመለክቱ የሚችሉ ግሶችን መለየትና መጠቀምን ተምራችኋል።

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ቃላዊ ዘገባ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በክርክር የቅድመ ዝግጅት ተግባር ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት ዘርዝሩ።
3. በቀጥተኛና ቀጥተኛ ባልሆነ የግብር ዓይነት መካከል ያለውን ልዩነት በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡
4. በአሁንና በሃላፊ ጊዜያት ሦስት ሦስት አረፍተነገሮችን ጻፉ።
5. ኃይለ ቃል በአንቀጽ ውስጥ ሊገኝ የሚችልባቸውን ስፍራዎች ዘርዝሩ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምእራፍ ሁለት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች መልሳችሁ አንብቡ።

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የዳመጥኩትን ምንባብ ጠቃሚና እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ መረጃዎችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 2 | ሀሳቤን በራስ መተማመን መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 3 | ቃላዊ ዘገባ ማቅረብ ችያለሁ | | | |
| 4 | መረጃዎችን በጽሁፍ መተርጎም ችያለሁ | | | |
| 5 | አንቀጽ መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 6 | መዝገበ ቃላትን መጠቀም ችያለሁ | | | |
| 7 | የተለያዩ የጊዜ አመልካች ግሶችን መለየትና መጠቀም ችያለሁ | | | |

# ምእራፍ ሦስት

# ማእድን

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ጸሐፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት ትገልጻላችሁ።
- ተወያይታችሁ የቃል ዘገባ ታቀርባላችሁ።
- አንብባችሁ በጽሑፍ ውስጥ ያሉ ተደራስያንን ትለያላችሁ።
- ለጽሁፍ ማጠቃለያ ትሰጣላችሁ።
- ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- በጽሑፍ ውስጥ ስርአተነጥብን ትጠቀማላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት “የኢትዮጵያ ማእድናት” በሚል ርእስ የቀረበ ጽሁፍ ካዳመጣችሁ በኋላ የምትሰሯቸው የቅድመማዳመጥ፣ የማዳመጥጊዜና የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል። ጥያቄዎቹን በትእዛዛቸው መሠረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁባቸውን ነጥቦችም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. ማእድን ምንድን ነው?
2. ማእድናት ምን ምን ጥቅም የሚኖራቸው ይመስላችኋል?
3. በሀገራችን ከሚገኙት የማእድን አይነቶች ውስጥ የምታውቋቸውን ዘርዝሩ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እስካሁን ባዳመጣችሁት የምንባብ ክፍል መነሻነት በቃል መልስ ስጡ።

1. በአለማችን ላይ ማእድናት የሚገኙት ከየት ነው?
2. ከማእድናት መካከል የሰው ልጆች ልዩ ዋጋና ትርጉም የሚሰጡት ለየትኞቹ ነው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያደመጣችሁትን ጽሁፍ መሠረት አድርጋችሁ በመወያየት በቃል ምላሽ ስጡ።

1. በሀገራችን ማእድናትን ማምረት የተጀመረው መቼ ነው?
2. በሀገራችን ማእድናት በምን በምን መልኩ ይመረታሉ?
3. በኢትዮጵያ ከሚገኙት የተፈጥሮ ማእድናት ውስጥ የተወሰኑትን ጥቀሱ።
4. የጌጣጌጥ ማእድናት ተፈላጊነታቸውና ተወዳጅነታቸው ከፍ እንዲል ያደረገው ምንድን ነው?

5. ኢትዮጵያ ከጠጣር ማእድናት ጋር ከተዋወቀች ረጅም ዘመን ያስቆጠረች ለመሆኑ በማስረጃነት የሚጠቀሰው ምንድን ነው?

6. ጸሃፊው "ማእድናት በጠጣር፣ በፈሳሽና በጋዝ መልክ ይገኛሉ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

7. የጽሁፉን ዋና ሀሳብ በአጭሩ ግለጹ።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

ከዚህ በታች በቀረቡት ርእሶች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የቡድናችሁን ሀሳብ በቅደም ተከተል በማደራጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ቃላዊ ዘገባ አቅርቡ።

## ተግባር አንድ

1. የማእድን አይነቶችና መገኛ ቦታቸው
2. የማእድን አይነቶችና ጠቀሜታቸው
3. የባህላዊ እና የዘመናዊ የማእድን አወጣጥ ሂደት ላይ የሚስተዋሉ ልዩነቶች

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ



በዚህ ትምህርት "የከበሩ ማእድናት" በሚል ርእስ የቀረበ ምንባብን በለሆሳስ ታነበላችሁ። በዚህ ሂደት የምትሰሯቸው የቅድመ ማንበብ፣ የጊዜ ማንበብና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበውላችኋል። ጥያቄዎቹን በትእዛዛቸው መሠረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## ቅድመማንበብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የጋራ ምላሻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

1. ከላይ የቀረቡት የማእድን ምስሎች ምን በመባል እንደሚጠሩ በመገመት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሩ።
2. ሌሎች የምታውቋቸው ማእድናት ካሉ ዘርዝሩ።
3. የምንባቡ ምን ምን ይዘቶች ሊያካትት እንደሚችል ገምቱ።
4. የሚከተሉትን ቃላት ፍቺ ገምቱ።

ሀ. ማእድን ለ. ፈርጥ ሐ. ሀሴት መ. ዝገት

## የከበሩ ማእድናት

ኢትዮጵያ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በርካታ የማእድን አይነቶች አሏት። ካሏት የማእድናት አይነቶች መካከል የከበሩ የሚባሉት እንቁ፣ ወርቅ፣ ኦፓል፣ አኳማሪን፣ የድንጋይ ከሰል፣ ኳርትዝ፣ ሩቢ፣ ሳፋየር፣ ሰንፔር፣ ኢመራልድ፣ ታንታለም እና ሌሎችም ናቸው። ከነዚህ መካከል ጥቂቶቹን ቀጥሎ እንቃኛለን።

ወርቅ ከከበሩ ማእድናት መካከል አንዱ ነው። በጣም ብርሃን በሚስብ አንጸባራቂ ቀለም፣ ዝገትን የመቋቋም እና በብዙ ልዩ ባህሪዎቹ ምክንያት በሰዎች ዘንድ በጣም የተከበረ ነው። አነስተኛ የወርቅ መጠን በሁሉም ቦታ ይገኛል። ይሁን እንጂ ከፍተኛ የሆነ የወርቅ ክምችት በብዛት የሚገኘው በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉልና በሌሎች አካባቢዎች ነው።

እንደወርቅ ሁሉ ኦፓል ብርሃንን የመሳብና የማንፀባረቅ ባህሪው የሰውን ዓይን መማረክ ብቻ ሳይሆን ቀልብንም በመሳብ የመጫጫን ስሜትን አስወግዶ ዘና የማለት ስሜትንና ውስጣዊ ሃይልን የሚያበረታታ ልዩ ማእድን ነው። ውዱ ጠጣር ኦፓል በሃገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1990ዎቹ መጀመሪያ

አካባቢ በሸዋ አካባቢ ሲሆን፣ ትልቅ ሊባል የሚችለው ግኝት እንደ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2008 ከመዲናችን 550 ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኘው ደቡብ ወሎ ዞን ልዩ ስሙ ወገል ጤና አካባቢ ነው።

የድንጋይ ከሰልም ሌላው የከበረ ማእድን ሲሆን ከፍተኛ መጠን ያለው ካርቦን እና ሃይድሮካርቦኖች ያሉት ተቀጣጣይ ጥቁር ወይም ቡናማ ጥቁር የደለል ድንጋይ ነው። የድንጋይ ከሰል ለኃይል ምንጭነት ያገለግላል። በሙቀት አማካኝነት የእፅዋት ክምችት ወደከሰል እንዲለወጥ አድርገውታል። የድንጋይ ከሰል ከሃይል ምንጭነት በተጨማሪ ለሲሚንቶ፣ ለብረታብረት እና ለጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ግብዓትነት ያገለግላል።

ሩቢ በጣም ታዋቂ ከሆኑ የከበሩ ማእድናት ተጠቃሹ ሲሆን ጌጣጌጥ ለመስራት በስፋት ጥቅም ላይ ይውላል። ሩቢ የእጅ አምባር፣ የአንገት ጌጥ፣ ቀለበት እና የጆሮ ጌጥ ሌሎችንም የጌጣጌጥ ዓይነቶች ለመስራት ይጠቅማል። በሌሎች ጌጣጌጦች ላይ ፈርጥ በመሆን በርካታ ጌጣጌጦችን ለመስራት ይጠቅማል። በዓለም ላይ ውድ ከሚባሉት ድንጋዮች ውስጥ ሩቢ አንዱ ሲሆን ከሀምራዊ እስከ ደም የሚመስል ቀይ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይ ነው። ቀዩ እንቁ በማለትም ይጠሩታል። በአለም ላይ ከባድና ተፅእኖ ፈጣሪ ከሚባሉት ድንጋዮች ውስጥ አንዱ የሆነው ሩቢ ጥንታዊ እና ታሪካዊ ከመሆኑ ባሻገር እስካሁን ድረስ በባህላዊ፣ በማህበራዊና በሀይማኖታዊ መንገድ ተፅእኖው ከፍ ያለ ነው።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የወርቅ ቀለም ________ ነው።
2. የሩቢ ቀለም ________ ነው።
3. የሳፋየር ቀለም ________ ነው።
4. የኤመራልድ ________ ነው።

ሳፋየርም ከከበሩ ማእድናት ውስጥ ተጠቃሽ ነው። ሳፋየር በዓለም ላይ ውድ ከሚባሉት ጌጣጌጦች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን፣ ከአልማዝ በመቀጠል ሁለተኛው ውድ ድንጋይ ነው። በብዛት ሰማያዊ ቀለም ያለው ሲሆን ቢጫ፣ ሀምራዊ፣ ብርቱካናማ እና ነጭ ቀለሞችም አሉት። ብዙውን ጊዜ በቀን ብርሃን ወይም በፍሎረሰንት መብራት ሲታይ ሐምራዊ ቀለምን ያሳያሉ። ሳፋየር የጥንካሬ ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል። በከበሩ ድንጋዮች ላይ ተቆርጠው ፈርጥ የሚሆኑ እና ጌጣጌጥ ተሰርቶባቸው የሚለበሱ ናቸው። ሳፋየር ከቀይ ቀለም በስተቀር በሁሉም ቀለም በሚባል ደረጃ ይገኛል። ነገር ግን በአለም ላይ ተፅእኖ ፈጣሪና ተወዳጅ የሆኑት ሁለት ቀለሞች ናቸው።

ኢመራልድ ሌላው የከበረ ማእድን ሲሆን፣ የተለያዩ ስያሜዎች ነበሩት። ኢመራልድ የተለያዩ ትርጉሞችና ጥቅሞች አሉት። የወደፊት ተስፋና የእድገት ምልክትም ተደርጎ ይወሰዳል። የስነ ልቦና ባለሙያዎች ልብን በሃሴት የሚሞላ፣ ውስጣዊ የተነቃቃ ስሜትን የሚፈጥር ልዩ ማእድን ነው ይሉታል። በራስ መተማመንን የሚፈጥር፣ የማሰብ አድማስን የሚያሰፋና ጥበበኛ ለመሆንም የሚጠቅም እንደሆነም ይገልጻሉ። የመረዳትን ችሎታ የሚጨምር ነው የሚሉትም አሉ።

ኢመራልድ አረንጓዴ ቀለም ያለው ሲሆን፣ ሰማያዊ አረንጓዴ ወይንም ቢጫ አረንጓዴ ሆኖ ይገኛል። በሁሉም ቦታ የማይገኝ በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ የሚገኝ ነው። ኢመራልድ በአለም ላይ ኮሎምቢያ፣ ዛምቢያ፣ ብራዚልና ዚምባብዌ ሀገሮች ይገኛል። ሀገራችንም የኢመራልድ ማእድን ባለቤት ነች። በኢትዮጵያ የኢመራልድ ማእድን የታወቀው በባህላዊ አምራቾች በ2008 ዓ.ም መጨረሻ ላይ ነው። ማእድኑ በስፋት የተገኘው በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን ሰባቦሩ ወረዳ ነው። ኢመራልድ በሌሎች ቦታዎችም ይገኛል።

ሌላው ደግሞ የታንታለም ማእድን ሲሆን፣ በቀደሙት ጊዜያት ታንታሊየም እየተባለ ይጠራ ነበር። ስያሜው ታንታለስ ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው። ጠንካራ እና ሰማያዊ ግራጫ ቀለም

ያለው ከብረት ምድብ የሚመደብ ሲሆን በቅይጥ መልክም ይገኛል። ፕላቲኒየምን በመተካት ለቤተሙከራ መሳሪያዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። ለኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ለሞባይል ስልክ፣ ለዲቪዲ ማጫወቻና ለኮምፒዩተሮች ይጠቅማል። ለቴሌቭዥን ድምጽ ጥራት መጨመር ቁልፍ ሚና የሚጫወተው የታንታለም ማእድን ነው። ለህክምና መሳሪያዎች ያለው ጠቀሜታም ከፍተኛ ነው።

(ምንጭ፡ የኢትዮጵያ ማእድን ሚኒስቴር)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በቃል ለክፍል ተማሪዎች አብራሩ።

1. በኢትዮጵያ ከሚገኙት የከበሩ የማእድን አይነቶች ውስጥ ሦስቱን ጥቀሱ።
2. ዝገትን የመቋቋምና በሰዎች ዘንድ በጣም የተከበረው የማእድን አይነት የትኛው ነው?
3. ኦፓል የተባለው ማእድን በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው መቼ እና የት ነው?
4. የታንታለም ማእድን ምን ምን ናቸው?
5. ታንታለም በስፋት የተገኘው በየት አካባቢ ነው?
6. የጽሁፉን ዋና ሀሳብ ተናገሩ።
7. የምንባቡን ዘጠኝ አንቀጾች በዘጠኝ አረፍተነገሮች አጠቃላችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

**ለ. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።**

1. የስነልቦና ባለሙያዎች ኢመራልድ የተባለው ማዕድን ልብን በሀሴትየሚሞላ እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህን ሃሳብ የ ማ ያ መ ለ ክ ት የ ት ኛ ው ነ ው ?

   ሀ. የተነቃቃ ስሜትን የሚፈጥር፤

   ለ. በራስ መተማመንን የሚፈጥር፤

   ሐ. ሆድን እንዲሞላ ያደርጋል፤

   ሐ. የማሰብ አድማስን የሚያሰፋ፤

2. በምንባቡ መሰረት ማእድናት ከሚሰጡት ጥቅም ውስጥ ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ለጌጣጌጥ መስሪያነት

   ለ. ለፋብሪካዎች ለግብአትነት

   ሐ. ለሀይል ምንጭንት

   መ. ለምግብ ማጣፈጫነት

3. በፍሎረሰንት መብራት ሲታይ ሀምራዊ ቀለምን የሚያሳይ የትኛው ነው?

   ሀ. አሜቲስት ለ. ሩቢ ሐ. ሳፋሪየም መ. ኳርትዝ

4. በባህላዊ ማህበራዊና ሀይማኖታዊ ተጽእኖው ከፍ ያለው የከበረ ማእድን የትኛው ነው?

   ሀ. ታንታለም ለ. ኢመራልድ ሐ. ወርቅ መ. ሩቢ

5. ለቴሌቭዥን ድምጽ ጥራት መጨመር ቁልፍ ሚና የሚጫወተው ማዕድን የትኛው ነው?

   ሀ. ሰንፔር ለ. ሳፋየር ሐ. ወርቅ መ. ታንታለም

ሐ. በምንባቡ መሠረት በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ሀሳቦች ከ "ለ" ረድፍ ተስማሚውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ሩቢ | ሀ. ፕላቲኒየምን ይተካል። |
| 2. ሳፋየር | ለ. ለኃይል ምንጭነት ያገለግላል። |
| 3. የድንጋይ ከሰል | ሐ. በጉጂ ዞን በሰባቦሩ ወረዳ ይገኛል። |
| 4. ኢመራልድ | መ. ቀዩ እንቁ በመባልም ይጠራል። |
| 5. ታንታለም | ሠ. ከአልማዝ በመቀጠል ሁለተኛ ውድ ድንጋይ ነው። |

መ. ቀጥሎ የቀረበውን ሰንጠረዥ በምሳሌው መሰረት አሟሉ።

| የማእድን አይነት | ቀለም | ጥቅም |
|---|---|---|
| ሩቢ | ከሀምራዊ እስከ ደም የሚመስል ቀይ ቀለም አለው። | በሌሎች ጌጣጌጦች ላይ ፈርጥበመሆን በርካታ ጌጣጌጦችን ለመስራት ይጠቅማል። |
| ሳፋየር | | |
| የድንጋይ ከሰል | | |
| ኢመራልድ | | |
| ታንታለም | | |

## ተግባር ሁለት

ሀ. “የከበሩ ማእድናት” በሚል ርእስ የቀረበውን ምንባብ በመመርመር ጽሁፉን በማንበብ ሊጠቀሙ የሚችሉት አካላት እነማን እንደሆኑ በመወያየት ከነምክንያቱ ግለጹ።

ለ. የከበሩ ማእድናት ከሚባሉት ውስጥ የትኞቹን ተጠቅማችሁ ታውቃላችሁ?

# ትምህርት አራት፡ መፃፍ

በዚህ ትምህርት የስርአተነጥቦች ማስታወሻ እና ማስታወሻውን መሰረት አድርጋችሁ የምትሰሩት መልመጃ ስለቀረበላችሁ መልመጃውን በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

### ስርአተነጥቦች

በጽሁፍ ውስጥ የሚገቡ ነጥቦችና ምልክቶች የቃላት፣ የሀረጋት እና የአረፍተነገሮች አሰላለፍ፣ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት በመከተል፣ በጽሁፍ የሰፈረው መልእክት ያለምንም መድበስበስ፣ በአንድ አፍታ የንባብ እይታ ለአንባቢው እንዲከሰት፣ መልእክቱ አሻሚና የተዛባ እንዳይሆን የማድረግ ትልቅ ሚና አላቸው።

በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ በርካታ የሥርአተነጥብ አይነቶች አሉ። የስርአተነጥብ አይነቶች ከአንድ በላይ አገልግሎት ሊኖራቸው ይችላል። በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ የተካተቱት የስርአተነጥብ አይነቶች እና ከሚኖራቸው አገልግሎት ውስጥ አንዱን ሊያመለክት ከሚችል ምሳሌ ጋር ቀርበዋል።

# የስርአተነጥብ አይነቶች

| ተ.ቁ. | መጠሪያ | ምልክት | የአጠቃቀም ምሳሌ |
|---|---|---|---|
| 1 | አንድ ነጥብ | . | ነጋዴው በስድስት ወራት ውስጥ 1.25 ሚሊዮን ብር አተረፈ። |
| 2 | ሁለት ነጥብ | : | አንደኛው ክፍለ ጊዜ ጠዋት በ2፡ 30 ይጀምራል። |
| 3 | ነጠብጣብ | ... | ከአህያ የዋለች ጊደር... |
| 4 | ሁለት ነጥብ ከሰረዝ | :- | በመማርያ መጽሃፋችን ውስጥ አስር ምእራፎች ይገኛሉ። እነሱም፡- |
| 5 | አራት ነጥብ | :: | ልጆች ጨዋታ ይወዳሉ። |
| 6 | የጥያቄ ምልክት | ? | ምን እያደረጋችሁ ነው? |
| 7 | ትእምርተ አንክሮ | ! | ጎሽ!ደግ አደረጉ! |
| 8 | ድርብ ትእምርተ ጥቅስ | “” | የህመሙ መንስኤ የ“ነርቭ” መሸማቀቅ ነው። |
| 9 | ነጠላ ትእምርተ ጥቅስ | ‘’ | የክፍላችን አለቃ “ጥሩ ውጤት ለማምጣት ‘ተግታችሁ አጥኑ።’ የሚለውን የመምህራችንን ምክር መዘንጋት የለብንም።” አለ። |
| 10 | ነጠላ ሰረዝ | ፣ | ብርቱካን፣ ትርንጎ፣ ሎሚ፣ ኮክና መንደሪን ከፍራፍሬ አይነቶች ጥቂቶቹ ናቸው። |
| 11 | ድርብ ሰረዝ | ፤ | የባህል ልብሷን ለብሳለች፤ ጸጉሯን ተሰርታለች፤ አይኗን ተኩላለች፤ አዲስ ጫማም አድርጋለች፤ ከዚህም ወደአንድ በአል ቦታ ለመሄድ የተዘጋጀች መሆኗን መረዳት ይቻላል። |
| 12 | ንኡስ ሰረዝ | - | ኪነተ-ቃል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 13 | ሙሉ ሰረዝ | — | ከአምቦ—ወሊሶ 60 ኪ.ሜ. ያህል ይርቃል። |
| 14 | ጭረት | ’ | ካመቱ ’ለታት ባንዱ ቀን እስኪመጣ፣<br><br>ናፍቆ ’ጠብቃለሁ ከቤቴ ሳልወጣ፤ |
| 15 | ቅንፍ | () | ክትፎ ማንሻ አንቀፎ (የቀንድ ማንኪያ) ተሰጠው። |
| 16 | እዝባር | / | ት/ቤት |
| 17 | ትእምርተ ስላቅ | ¡ | እንዴት ያለ'ሽው ቆጣቢ ነህ ባክህ¡ (ለአባካኝ ሰው) |
| 18 | እመልክት | ^ | ክቡርነታቸው በበአሉ ፍጻሜ ተገኙ።<br>^ |

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. ከዚህ በታች ስርአተነጥቦቹ ያልተሟሉላቸው አረፍተነገሮች ቀርበውላችኋል። አረፍተነገሮቹን በሚገባ በማንበብ በተገቢው የስርአተነጥብ አይነት አሟልታችሁ እንደገና ጻፏቸው።**

1. አብክመ 21 የአስተዳደር ዞኖች አሉት
2. የሰዋስው ጊዜያት ሦስት ናቸው እነሱም የአሁን ጊዜ የሃላፊ ጊዜና የትንቢት ጊዜያት ናቸው
3. ከትልቅ ወይም ከትንሽ መወለድ ሙያ አይደለም ራስን ለታላቅ ሙያ መውለድ ግን ሙያ ነው ይሉ ነበር ብልሁ መሪ
4. ጎሽ ብዙ ስራ ሰርተው ውለዋል ለዚህ ምን አይነት ሽልማት ይዘጋጅላቸው እንደኔ ከሆነ ደብተር ብእር እርሳስና ላጲስ ቢሆኑ እመርጣለሁ

ለ. ከዚህ በታች ስርዓተነጥቦቹ ያልተሟሉለት አጭር ጽሁፍ ቀርቦላችኋል። ጽሁፉን በሚገባ በማንበብ በተገቢው የሥርአተነጥብ ዓይነት አሟልታችሁ እንደገና ጻፉ።

ከእለታት አንድ ቀን አንድ አዳኝ በወጥመድ አንዲት ዋኔ ይዞ ወደቤቱ ሲመለስ፣ ወዴት ነው የምትወስደኝ ብላ ዋኔዋ ጠየቀችው አዳኙም፣ ምን ትጠይቂኛለሽ አርጄ ልበላሽ ነዋ ብሎ መለሰላት እንዴት ያለኸው ሞኝ ነህ አሁን እኔን በልተህ ልትጠግብ ነው እስቲ አስተውለህ ተመልከተኝ! ሰውነቴ በጣም ያነሰ ፍጥረት ነኝ። ከጉሮሮህ እንኳ አልወርድም። ይልቅዬ እንስማማ! እኔ የሚጠቅሙህን ሶስት ምክሮች ልስጥህ እኔን ደግሞ ማረኝ በዚህ ከተስማማን አንዱን አሁን ሁለተኛውን ስትለቀኝ ከዛፉ ላይ ሁኜ ሶስተኛውን ደግሞ እዚያ ማዶ ካለው ዳገት አፋፍ ላይ ተቀምጬ እነገርሃለሁ አለችው።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት ለቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ለመስጠት የሚያስችላችሁ መልመጃ ስለቀረበላችሁ በትእዛዙ መሠረት ስሩ።

## መልመጃ አራት

በጥንድ በመሆን ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ ፍቺያቸውን የሚያመለክቱ አረፍተነገሮችን መስርቱ።

| | |
|---|---|
| 1. ማእድን | 6. ሀብል |
| 2. ምንጭ | 7. ከበረ |
| 3. ጠረጠረ | 8. ቁልፍ |
| 4. አልቦ | 9. ቀለበ |
| 5. ፈርጥ | 10. አምባ |

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት በምእራፍ ሁለት በትምህርት ስድስት ስር ስለ ሰዋስው ጊዜ የቀረበውን ማስታወሻ እንደገና ከከለሳችሁ በኋላ ከዚህ በታች የቀረበውን መልመጃ በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

## መልመጃ አምስት

ሀ. የሚከተሉት አረፍተነገሮች በየትኛው አይነት የሃላፊ ጊዜ እንደቀረቡ በቀረበው ክፍት ስፍራ ጻፉ።

1. ቦንቱ ልብሷን አጥባ ጨረሰች። ____________________________
2. ቦንቱ ልብሷን አጥባ ነበር።____________________________
3. ቦንቱ ልብሷን አጥባለች።____________________________

ለ. "ቦንቱ ልብሷን አጥባለች" የሚለውን አረፍተነገር ወደ የአሁን ጊዜ እና የትንቢት ጊዜ አረፍተነገር ለውጣችሁ በቀረበው ክፍት ስፍራ ጻፉ።

1. ____________________________
2. ____________________________

# የምእራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል። በማዳመጥ ክፍል "የኢትዮጵያ ማዕድናት" በሚል ርዕስ በንባብ የቀረበላችሁን ጽሁፍ መሠረት በማድረግ የተለያዩ የማዳመጥ ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ የመልመጃ ጥያቄዎችን ሠርታችኋል።

በክፍል ሁለት መናገር በሚለው ስር ደግሞ በመረጣችሁት ርዕስ ላይ በመዘጋጀትየቃል ዘገባ አቀራረብን ተለማምዳችኋል። በክፍል ሦስት በቀረበላችሁ ምንባብ መነሻነት የንባብ ክሂላችሁን ሊያዳብሩ የሚችሉ ጥያቄዎችን ሠርታችኋል።

በክፍል አራት የምንባቡን ዋና ሀሳብ አሳጥራችሁ መጻፍን፣ አንቀጽ መጻፍን፣ የአማርኛ ሥርዓተነጥብ ዓይነታቸውን እና አጠቃቀማቸውን ተምራችኋል፤ በቀረበላችሁ የመልመጃ ጥያቄ መነሻነትም ሥርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችኋል። በክፍል አምስት ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መስጠትን ተምራችኋል።

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

በ"ሀ" ስር የቀረቡትን የስርአተነጥብ አይነቶች በ"ለ" ስር ከተገለጹት አገልግሎታቸው ጋር አዛምድ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. አራት ነጥብ | ሀ. አማራጭ ሀሳብ ማቅረቢያ |
| 2. የጥያቄ ምልክት | ለ. አህጽሮተ ጽሁፍ መመስረቻ |
| 3. ትእምርተ አንክሮ | ሐ. ዝርዝር ነገሮችን መለያ |
| 4. ድርብ ትእምርተ ጥቅስ | መ. በግጥም የተጎረደ ቀለምን ማመልከቻ |
| 5. ነጠላ ትእምርተ ጥቅስ | ሠ. እስከ |
| 6. ነጠላ ሰረዝ | ረ. ድርብ ቃላትን ማጣመሪያ |
| 7. ድርብ ሰረዝ | ሰ. የስሜታዊ ንግግር ድምጸትን ማመልከቻ |
| 8. ንኡስ ሰረዝ | ሸ. የጥያቄ ድምጸትን ማመልከቻ |
| 9. ሙሉ ሰረዝ | ቀ. የአረፍተነገር መቋጨትን ማመልከቻ |
| 10. ጭረት | በ. የሌላ ወገን ሃሳብን መቀንበቢያ |
| 11. ቅንፍ | ተ. በሌላ ወገን ሃሳብ ውስጥ ተጨማሪ የሌላ ወገን ሃሳብን መቀንበቢያ |
| 12. እዝባር | ቸ. ተዛማጅነት ያላቸው አረፍተነገሮችን መለያ |
| 13. ትእምር ስላቅ | ኀ. ማስተካከያ እንዲደረግ ማመልከቻ |
| 14. እመጫት | ነ. ፊዝ |

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ሦስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች መልሳችሁ አንብቡ።

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥኩትን ምንባብ መልዕክት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | ባነበብኩት ምንባብ ስር የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት ችያለሁ | | | |
| 3 | የቀረበውን ጽሁፍ አሳጥሬ መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 4 | የስርዓተ ነጥብ ዓይነቶችና ጠቀሜታ በመለየት በጽሁፍ ውስጥ መገልገል ችያለሁ | | | |
| 5 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መስጠት ችያለሁ | | | |
| 6 | የሰዋስው ጊዜያትን መለየት ችያለሁ | | | |

# ምእራፍ አራት

# ልቦለድ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ታሪኩን ትተርካላችሁ።
- በታሪኩ ውስጥ ያሉትን ዋና ገጸባህርያት ትናገራላችሁ።
- የቀረበ ማስታወሻ አጥንታችሁ በራሳችሁ አገላለጽ ትጽፋላችሁ።
- የተለያዩ ሀረጎችን በመጠቀም አረፍተነገር ትመሰርታላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

ቀጥሎ መምህራችሁ "ሲጨልም" የሚል አጭር ልቦለድ ሲያነቡላችሁ አዳምጡ። ያዳመጣችሁትን አጭር ልቦለድ መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎችም ስለቀረቡላችሁ በትእዛዛቸው መሠረት በተገቢ ሁኔታ ስሩ።

### የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ከዚህ በፊት ልቦለድ አንብባችሁ ታውቃላችሁ? ካነበባችሁ የምታስታውሱትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ።
2. "ሲጨልም" በሚል ርእስ የሚቀርበው የማዳመጥ ጽሁፍ ስለምን ጉዳይ ሊያነሳ እንደሚችል ገምቱ።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በግል በቃል መልሱ።

1. በልቦለዱ ውስጥ ያሉትን ዋና እና ንኡሳን ገፀባህሪያት ዘርዝራችሁ ፃፉ።
2. ባዳመጣችሁት ልቦለድ ውስጥ የተገለጸው ድርጊት የተፈጸመበት ቦታ የት ነው?
3. የመድኃኒት ቤቱ አስተናጋጅ ለአዛውንቱ መድኃኒቱን ተቀብለው ብሩን የሚመልሱላቸው ይመስላችኋል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳቸውን በጽሑፍ ግለጹ።

1. በምንባቡ ላይ የአዛውንቱ ዕድሜ ምን ያህል ነው?
2. "… ለእንቶ ፈንቶ ጉዳይ የማባክነው ጊዜ የለኝም … " ያለው ማነው? ለምን?
3. ባዳመጣችሁት አጭር ልቦለድ ውስጥ አዛውንቱ "ለስራ ያልደረሱ ለእህል ያላነሱ" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው?
4. የአጭር ልቦለዱ ጭብጥ ምንድን ነው?
5. አዛውንቱ መድሃኒቱን ለምን መመለስ ፈለጉ?
6. ያዳመጣችሁትን አጭር ልቦለድ መልሳችሁ ለክፍል ተማሪዎች ተናገሩ።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

## መልመጃ ሁለት

ከዚህ በታች ካዳመጣችሁት ጽሁፍ የወጡ አባባሎችን በቡድን ካጠናችኋቸው በኋላ ፍቺያቸውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።

1. ነካ ያደርገዋል
2. የእርጎ ዝንብ
3. እንደማታራቁት
4. ሲዘላብድ
5. የነተበ
6. የእድሜዬ ጀምበር እየጠለቀ

## ተግባር አንድ

ያዳመጣችሁትን ልቦለድ ታሪክ እንደገና በራሳችሁ አገላለጽ ለጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት "አሁን አምኛታለሁ" በሚል ርእስ የቀረበ አጭር ልቦለድ ከማንበባችሁ በፊት፣ እያነበባችሁና ካነበባችሁ በኋላ የምትሰሯቸው ጥያቄዎች ስለቀረቡላችሁ በትእዛዛቸው መሰረት ስሩ።

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በታች ከቀረበው አጭር ልቦለድ ርእስ በመነሳት ልቦለዱ ስለምን እንደሚያወሳ በቡድን ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው።
2. ቀጥሎ የቀረቡትን ቃላት ፍቺ ገምቱ።

ሀ. ያነባሉ ለ. የደቀልሽው ሐ. አበጋዝ

# "አሁን አምኛታለሁ"

እጇ ወደ ኋላ ከጎጆው ምሰሶ ጋር ታስሮ እርቃኗን ተቀምጣለች። ግርማ ትልቅ ቢላ በእጁ ጨብጦ ከፊት ለፊቷ እንደ ጅብራ ተገትሯል። በጉልበቷ ልትሸፍን የምትሞክረውን ሀፍረቷንና የገፉ ሆዷን በእልህ እየተመለከተ በንዴት ቀረባት። ሁለመናዋ ያስፈራል። የሚቁለጨለጩ ዓይኖቿና የሚጉረጠረጡ ዓይኖቹ እኩል ያነባሉ፤ በርከክ ብሎ በቢላው ጫፍ ጉንጯ ላይ የሚንከባለለውን የእንባ ዘለላ ለመገደብ ሞከረና ሳግ አፍኖት ዓይኑን ጨፈነ።

"እመነኝ ግርምሽ፣ ልቤ ዛሬም ካንተ ጋር ነው" ትክ ብሎ አያትና "ልብሽ ቆሽሿል፤ ዓይኖችሽና ምላስሽ እኩል ይዋሻሉ" "እመነኝ! ግርማ" "ዝጊ!" ብሎ በመጮህ አራስ ነብር ሆነባት። በርግጋ ዝም አለች። "የገደልሽው ልጄና ከማንም የደቀልሽው ጽንስ..." ቃላት አጠረውና ተነስቶ ከቤቱ ወጣ። ደጅ መደብ ላይ ተቀምጦ ስቅስቅ ብሎ አነባ። "ፈጣሪዬ ምን በደልኩህ?" አለ ጉንጮቹን ጥብቅ አድርጎ እየያዘ።

በጦር ግንባር ሳለ ከማንም በላይ ትናፍቀው የነበረችው እሷ ነበረች። በትዝታ ሲብሰከሰክ ለጠላት ተኩስ በተደጋጋሚ ተጋልጧል። ጓደኞቹ ወደ ከተማ እየሄዱ በሚደሰቱበት የዕረፍት ጊዜያቸው እሱ ከፎቶዋ ጋር ሲጫወት ያመሻል። በነኛ ስድስት ዓመታት የቀን ከሌት ጸሎቱ በሰላም ተመልሶ ከእርሷ ጋር መኖር ነበር። ሁኔታዎቹ የተገላቢጦሽ ሆኑበት። እጁን ያጣለት ልጁ በአውሬ መበላቱ ተነገረው። ያ ቀፋፊ የመጨረሻው የውጊያ ውሎ ታወሰው።

ጠላት ወሮ በመሸገበት አነስተኛ ከተማ እየተዋጉ ነበር። ብዙ ጓዶቹ የተሰዉበት መራር ጦርነት ስለሆነ ለማፈግፈግ ተገደዱ። በዚህ ውስጥ ነበር በእሳት ተያይዞ እየፈረሰ ካለ ቤት ውስጥ የህጻን ጩኸት የሰማው፤ በደመነፍስ ሮጠ። በርግጥ አቅፎት ከእሳቱ ሲወጣ ሁሉ የራሱ ልጅ መስሎት ነበር። የወገን ጦር አፈግፍጎ ስለነበር

ልጁን ታቅፎ እየሸሸ ያካሄደው ጦርነት ሰቀቀን ሆኖት ቀርቷል። በህጻኑ ደረት ዘልቆ እጁን የመታው ጥይት... በቃ ሁሉን ነገር ደመደመው።

ግርማ በልጁ ምክንያት ሆዱ ሲባባ ከርሟል። ስለህጻኑ በእጁ ላይ መሞት አምላኩን ሊወቅስ ሁሉ ዳድቷል። ቀኝ እጁን አጥቶ ከጦር ሰራዊቱ ሲቀነስም ሀዘኑ አብሮት ነበር። ያ ሰቀቀን በሚስቱ እቅፍ፣ በልጁ ደስታ አልተሻረም። "የትም ስትማግጥ ልጄን ላውሬ ሰጠችው" ለራሱ ነበር ያወራው። ሚስቱ ልጁን ቀብራለት፣ የስምንት ወር ነፍሰ ጡር ናት፤ የራሷን አዲስ የታሪክ ምእራፍ ጀምራለች። ቀዬው ሲደርስ እሱ ባሰበው ደስታ አልተቀበለችውም። ገና ስታየው ጮኻ ራሷን ሳተች። ልቡ ተሰብሮ፣ በሁሉ አቂሞ ነበር።

እየተብሰከሰከ ሁለት ሳምንታት አሳልፏል። ያቀረበችለትን አልበላም፤ የነገረችውንም አላመነም፤ አንድም ቃል አልተነፈሰም። እንኳን ደህና መጣህ ሲሉትና የልጁንም ሞት ሊደርሱት የመጡትን ሁሉ በዝምታ ሸኛቸው። እጁን ስላጣለት ህጻን ፈጣሪ የእርሱን ብላቴና ሊጠብቅለት ይገባ ነበር ብሎ አምኗል። ደሙን የገበረለት ሕዝብ ሚስቱንና ልጁን ሊንከባከብ ይገባ ነበር። ቀን ከሌት ሀሳቡ የነበረች ሚስቱ ራሷንና ልጇን ልትጠብቅ ግዴታዋ ነበር። ሟች ልጁም ቢሆን ስላባቱ ናፍቆት ራሱን ከሞት መከላከል ነበረበት። ድቅድቅ ጨለማው ላይ አፍጥጦ እንባውን ጠረገ። ለምን ነበር መትረየስ ጥይት እጁን የመታው? ትዝ አለው፤ ያ አይኑ ላይ ተስሎ ግርማ ከሁሉ ተጣልቶ፣ ሁሉን ዘንግቶ ከረመ። የሚስቱ እንባ እየቀፈፈው ሁለት ሳምንት የናፈቀው ገላዋን ሳይጠጋ ቆየ። ዛሬ ግን ቢያንስ የሚችለውን ሊበቀል ስለት አነሳ። አያል እንደነገሩ ያሰረውን እጇን ካላቀቀች በኋላ ግራ ገብቷት ቆመች። እርቃኗን መሸፈን አላሰኛትም፤ ሽሽታ ማምለጥም አልፈለገች። "እሪ!" ብላ ብትጮኽ ትወድ ነበር፤ መፍትሔ ግን አልመሰላትም።

# የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ባነበባችሁት የልቦለዱ ክፍል ተሳታፊ ገጸ ባህርያት እነማን ናቸው?
2. ቀጥሎ በሚቀርበው የልቦለድ ክፍል ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

ባሏን ትወደዋለች፤ ስድስት አመት ሙሉ ራሷን በንጽህና ለማቆየት ከስንቱ ዋልጌ ጋር ታግላለች። የሚልክላትን ደብዳቤ እየመላለሰች ሃምሳ ጊዜ በማንበብ ፍቅርና ናፍቆቷን ስትጠብቅ ኖራለች። ልጅሽን አልተንከባከብሽም የሚላት ማንም የለም፤ የባሏን ምትክ ከማንም በላይ አንቀባራ አሳድጋዋለች፤ ትምህርት ቤት ልትልከው ሁሉ ወስና ነበር፤ ሰውነቱ መንገዱን መቋቋም እስኪችል ቤት ውስጥ ፊደል ስታስጠናው ቆይታለች። ላባቱ በራሱ እጅ ነበር ደብዳቤ የሚጽፈው፤ ለእርሱ የተጻፈውን የሚያነበው ራሱ ነበር። ግን ምን ያደርጋል! ያን ክፉ ቀን አትረሳውም።

የዛሬ ስምንት ወር ገደማ ከገበያ ስትመለስ ልጇን አጣችው። ከአካባቢ ልጆች ጋር ሊጫወት ሄዷል ተባለች። አይና ደጅ ደጁን እያየ መጨለም ጀመረ። ኋላም ልጆቹ ተደናግጠው እየተንጫጩ መጡ። ልጇን አውሬ እንደበላው አረዷት። ከማንም ቀድማ ነጠላውን ጥላ በረረች። እየጮኸች ወዲያ ወዲህ በረረች። በርቀት እያየች ጥቅጥቅ ወዳለው ጫካ በድፍረት ገባች… ሁለት ጎረምሶች ጫካው መሃል አፍነው አስቀሯት፤ ታገለች፤ አልቻለችም፤ ደፈሯት። እየተፈራረቁም አደከሟት።

ጎረቤቶቿ ፋና ይዘው ሲደርሱ ልብሷ ተገልቦ ካንዱ ዛፍ ስር ወድቃ ነበር። እሷን ተሸክመው ወደውስጥ ሲዘልቁ የልጇን አካል ተበታትኖ አገኙት። ፍቅሯ ግን አላመናትም፤ እንባዋን እንዳዘ እንባ ቆጥሮላታል፤ ያ ፍልቅልቅ ፊቱ ተጫዋች እንደበቱ ታስሯል።

ነገን ስታየው ጨለመባት እናም ሞቷን ናፈቀች። የጸነሰችውን ጠልታ፣ በባሏ ተጠልታ፣ በባንነ ቁጥር ስለት እያነሳባት የምትኖረው ኑሮ ከበዳት። እንደተገተረች ፈገግ ለማለት ሞከረች። እጇ የታሰረበት ገመድ በእጇ ነው። የልጇን እርሳስና ደብተር አንስታ ሞነጫጨረችና ቀና ብላ ምሰሶውን ተመለከተችው።

ግርማ መወሰን ከብዶታል። የልቡ ገዳይ በቤቱ ምሰሶ ስር በሀሰት ተጀቡና ትጠብቀዋለች። አወጣ አወረደ፤ ነገ ከዛሬ በላይ መራር ሆኖ ታየው። በዚህ ውለታ ቢስ ዓለም አንዳች ጣእም እንደሌለ ገባው። በጨለማ ውስጥ ብልጭ እያሉ የሚያስፈራሩትን የሞት አበጋዞች ሸሽቶ ወደቤት ገባ። ተንገዳግዶ ቆመ። የአያል ርቃን በድን ምሰሶው ላይ ተንጠልጥሎ አፍጥጦበታል። በድን ሰውነቱ ለምንም አልታዘዝ አለው። ከመሬት ላይ የወደቀችውን ብጣሽ ወረቀት አነበባት፤ "ስለአንተና ስለልጄ ኖሬያለሁ፤ ልጄና አንተን አጥቻለሁ፤ በእንባዬ ያላመንከኝን እውነት በሞቴ ተጋፈጠው፤ ጨካኝ! አውሬ!" እየበረረ ወጣ።

አሁን ስለአያል አያውቅም። ጎዳና ላይ ድሪቶውን ተጀቧቡኖ ጥንድ ወጣቶች ሲያይ እየሮጠ ከፊታቸው ይገተራል። ሴቶቹ ሁል ጊዜ ይበረግጋሉ። አፍጥጦ ያያቸውና ወንዱን እየጠቆመ "ጨካኝ! አውሬ! አይደለም እሺ!" ይላል። ወደወንዱ ይዞርና "እውነቷን ነው እሺ! እመናት" ይለዋል። ከዚያም እንደቆሙ ጥሏቸው ቁርጥራጭ ሲጋራ እየለቃቀመ "እኔ ግን አሁን አምኛታለሁ" ይላል።

(ምንጭ፡ የኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም ሚስቴር መሰረታዊ የስነጽሑፍ ማሰልጠኛ ሞጁል (2008) ገጽ 56-59 ላይ የተወሰደ)

# የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በቡድን ተወካዮቻችሁ አማካይነት በቃል ግለጹ።**

1. በታሪኩ ውስጥ የተገለጹትን ገጸ ባህርያት ለይታችሁ አውጡ።
2. ግርማ ለልጁ ሞት እና ከሌላ ወንድ ለመጸነሷ አያልን ተጠያቂ ማድረጉ ተገቢ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?
3. አያል ራሷን ማጥፋቷ ተገቢ ነው ትላላችሁ? እናንተ አያልን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?
4. "... በእንባዬ ያላመንከኝን እውነት በሞቴ ተጋፈጠው... ጨካኝ አውሬ" የሚለው የአያልን የጽሁፍ ቃል በራሳችሁ አባባል አብራሩ።
5. ግርማ የተሰኘው ባለታሪክ ስራው ምን ነበር?
6. ግርማ የተባለው ገጸባህርይ በመጨረሻ ምን አጋጠመው?
7. የልቦለዱን ጭብጥ ግለጹ።

**ለ. ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ዘይቤያዊ አነጋገሮችና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በልቦለዱ ውስጥ ያላቸውን ፍቺ በምሳሌው መሰረት ግለጹ።**

| | | |
|---|---|---|
| እንደ ጅብራ ተገትሯል | ሆዱ ባባ | የሞት አበጋዝ |
| አራስ ነብር ሆነባት | ልቡ ተሰበረ | ውለታ ቢስ |
| ሲያወጣ ሲያወርድ | | |

ምሳሌ፡

1. ከፊት ለፊቷ <u>እንደ ጅብራ</u> ተገትሯል።

   (የተሰመረበት አባባል አነጻጻሪ ዘይቤ ነው። ጅብራ በሰሜን ተራሮች አካባቢ የሚገኝ ተክል ሲሆን ድንገት ሲታይ ቀጥ ብሎ የቆመ ሰው ይመስላል። ስለዚህም ነው የግርማን አቋቋም

ከጅብራ ጋር በማነጻጸር "እንደ ጅብራ ተገትሯል" የተባለው።)

2. ግርማ በልጁ ምክንያት <u>ሆዱ ሲባባ</u> ከርሟል።

(የተሰመረበት አባባል ፈሊጣዊ አነጋገር ነው። ፍቺውም ስሜቱ ሲረበሽ ማለት ነው።)

ሐ. ቀጥሎ የቀረቡትን አረፍተነገሮች በአጭር ልቦለዱ በቀረበው ታሪክ መሰረት በቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ጻፏቸው።

1. ግርማ እጁ በጥይት ተመታ።
2. ግርማ አበደ።
3. አያል ልጇን ትንከባከብ ነበር።
4. ግርማ ወደጦር ግንባር ሄደ።
5. አያል የሆነችውን ልታሳምነው ብትጥርም ግርማ ሊያምናት አልቻለም።
6. በሚስቱ ማርገዝ ተረበሸ።
7. አያል በጎሮምሶች ጫካው ውስጥ ተደፍራ አረገዘች።
8. ልጁ ጫካው ውስጥ በአውሬ ተበላ።
9. ሊበቀላት ቢላ አነሳ።
10. ግርማ አያልንና ልጁን ይናፍቅ ነበር።
11. አለሚ ራሷን አጠፋች።
12. ግርማ ከጦር ግንባር ወደቤቱ ተመለሰ።

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት የሚቀርብላችሁን ማስታወሻ አንብባችሁ ማስታወሻውን መልሳችሁ ትጽፋላችሁ።

## ተግባር ሁለት

ቀጥሎ የቀረበውን ማስታወሻ ካነበባችሁ በኋላ ለአጭር ልቦለድ አላባውያን ከ"አሁን አምኛታለሁ" ምሳሌ በማውጣት ጽፋችሁ ለጓደኞቻችሁ አስረዱ።

## የአጭር ልቦለድ ባህርያትና አላባውያን

ልቦለድ ደራሲው እውነተኛውን አለም መነሻ በማድረግ ምናባዊ ፈጠራውን ተጠቅሞ የሰውን ልጅ አጠቃላይ ማህበራዊና ግላዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ገጽታዎች የሚያሳይበት የስነጽሑፍ ዘርፍ ነው። ልቦለድ አጭር እና ረጅም ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

### የአጭር ልቦለድ ባህርያት

አጭር ልቦለድ ሰብሰብ ያለ ወይም የታመቀ፣ ጠባቃ ትስስር ያለው፣ ፈጣንና ጎልቶ የሚታይበትና የሁሉም ነገር መቋጫ የሆነ ብቸኛ የትኩረት ነጥብ ያለው የልቦለድ ዓይነት ነው። ከአጭር ልቦለድ ባህርያት ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

ሀ. ነጠላ ውጤት፡ ሁሉም የአጭር ልቦለድ አላባውያን ተሳስረው ወደአንድ ዋነኛ ትኩረት የሚፈሱበትና ደራሲው በአንባቢው አእምሮ ተቀርጾ እንዲቀር የሚፈልገው አንድ ኪነጥበባዊ ግብ ነው።

ለ. ጥድፊያ፡ የሚተረከው ታሪክ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ በመተረክ፣ ትልሙና የተለያዩ ክፍሎች ፍሰታቸውን ጠብቀው ዝርዝር ነገር ሳያበዙ፣ የተስፋፋ የመቼት ገለጻና የገጸ ባሕርይ ዳራ ሳይሰጥ በፍጥነት መጓዝ ነው።

ሐ. ቁጥብነት፡ በዋናነት በአጭር ልቦለድ አላባውያንና አኗኗር እርስ በእርስ በሚፈጥሩት አይቀሬ ቅንጅት ውስጥ የሚታይ ነው። ምሳሌ፡

የአጭር ልቦለድ ታሪክ የአንድን ገጸ ባህሪ ታሪክ ከልደት እስከሞት የሚተርክ ሳይሆን በአንድ ዋና ገጸ ባህሪ ላይ በማተኮር የሱን ህይወት አንድ ዘለላ በመምረጥ ሌሎችንም አላባውያን በዚሁ ዙሪያ በማጠንጠን ያቀርባል።

የአጭር ልቦለድ አላባውያን

ሀ. ታሪክ፡ በጊዜ ቅደም ተከተል የሁነቶች ትረካ ነው።

ለ. ገፀባህሪያት፡ በልቦለዱ ጽሁፍ ውስጥ ደራሲው የሚፈጥራቸው የገሃዱን አለም ሰዎች የሚወክሉ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው።

ሐ. መቼት፡ መቼ እና የት ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገነባ ነው። በልቦለዱ ዉስጥ የተሳሉት ገጸባህሪያት የሚኖሩበት፣ ታሪካቸውን የሚፈጽሙበት ቦታ እና ጊዜ ነው።

መ. ግጭት፡ በልቦለዱ ዓለም የሚኖሩ ገጸባህሪያት በታሪኩ ውስጥ በተፈጠረላቸው የእርስ በእርስ ግንኙነት የተነሳ በተለያዩ ምክንያቶች ቅራኔዎች ወይም አለመግባባቶች ሲከሰቱ አንዱ ገጸባህሪ ከሌላዉ ገጸባህሪ ጋር የሚፈጥረው ንትርክ፣ ገጸባህሪያቱ ይህን ልፈጽም ወይም አልፈጽም በሚል ሁኔታ ከራሳቸው የሚፈጠር ፍጭት (ፍለሚያ) ነው።

ሠ. ትልም፡ በልቦለድ ውስጥ በምክንያት እና ውጤት የተሰናሰሉ ሁነቶች እና ድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ ትረካ ነው።

ረ. ጭብጥ፡ ከአጠቃላዩ የልቦለዱ ታሪክ ተጨምቆ ወይም ተፈልቅቆ የሚወጣ መልዕክት (ቁምነገር) ነው።

ሰ. አንፃር፡ ደራሲው ታሪኩን የሚያቀርብበት የትረካ አቅጣጫ ነው።

(ምንጭ፡ ዘሪሁን አስፋው (2005) የስነጽሁፍ መሰረታውያን)

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት የቃላትን አውዳዊና ተቃራኒ ፍቺ እንድትሰጡ የሚጠይቅ መልመጃ ስለቀረበ በትእዛዙ መሰረት ትሰራላችሁ።

## የቃላት አውዳዊ ፍቺ

የቃላት ፍቺ በአረፍተ ነገር ውስጥ በሚኖራቸው አገባብ ይወሰናል። ይህም ማለት አንድ ቃል በተለያዩ አረፍተነገሮች ውስጥ ሲገኝ የሚኖረው አገባባዊ ወይም አውዳዊ ፍቺ በመባል ይጠራል። የቃላትም ፍቺ እንደየ ዐውዱ የተለያየ ይሆናል። ስለሆነም የቃሉ ትክክለኛ ፍቺ የሚታወቀው በገባበት አረፍተነገር ውስጥ ነው። ለምሳሌ፡ "ከፈለ" የሚለውን ቃል ወስደን እንመልከት

ነጋዴው ማህበረሰብ ግብሩን በወቅቱ ከፈለ። (ሰጠ)

ልጁ የገዛውን ብርቱካን ለሁለት ከፈለ። (ገመሰ) ---

"ከፈለ" የሚለው ቃል በሁለት አረፍተ ነገሮች ውስጥ እንደየአገባቡ የያዘው የተለያየ ፍቺ አውዳዊ ፍቺ በመባል ይጠራል።

## መልመጃ አራት

ሀ. ከዚህ በታች ከምንባቡ በተወሰዱ አረፍተነገሮች ውስጥ ከስራቸው

ለተሰመረባቸው ቃላት ማስታወሻውን መሰረት አድርጋችሁ አውዳዊ ፍቺያቸውን ጻፉ።

1. ደጅ መደብ ላይ ተቀምጦ ስቅስቅ ብሎ አነባ።
2. ብዙ ጓዶች የተሰዉበት መራራ ጦርነት ስለነበረ ማፌግፌግ ተገደዱ።
3. ግርማ በልጁ ምክንያት ሆዱ ሲባባ ከርሟል።
4. ስለህፃኑ በእጁ ላይ መሞት አምላኩን ሊወቅስ ዳድቷል።
5. ቀየው ሲደርስ እሱ ባሰበው ደስታ አለተቀበለችውም።

6. የባሏን ምትክ ከማንም በላይ <u>አንቀባራ</u> አሳድጋዋለች።

7. ጎረቤቶቿ <u>ፋና</u> ይዘው ሲደርሱ...።

8. <u>ሲብሰከሰክ</u> ሁለት ሳምንታት አሳለፈ።

ለ. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምሳሌው መሰረት ተቃራኒ ፍቺ ስጡ።

ምሳሌ፡ በደመነፍስ = በአስተውሎት

1. ተጀቡና
2. ብላቴና
3. ዋልጌ
4. አፈገፈገ
5. ፍልቅልቅ
6. ድሪቶ

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

ቀጥሎ ስለሀረግ አይነቶች የቀረበ ማስታወሻ ቀርበውላችኋል። ማስታወሻውን ካነበባችሁ በኋላ መልመጃዎቹን በትእዛዛቸው መሰረት ስሩ።

## የሀረግ አይነቶች

ሀረግ ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ሰፊ መዋቅር ነው። የሀረግ መሰረት ቃላት ናቸው። የሀረጋቱ ዓይነት ሀረጉን በሚመሰርቱት የቃላት ዓይነት ይወሰናል። በዚህም መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙት የቃል ክፍሎችና የሚመሰሩት የሀረግ ዓይነቶች በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርበዋል።

| ተ.ቁ. | የቃል ክፍሎች | የሀረግ ዓይነቶች |
|---|---|---|
| 1 | ስም | ስማዊ ሀረግ |
| 2 | ግስ | ግሳዊ ሀረግ |
| 3 | ቅጽል | ቅጽላዊ ሀረግ |
| 4 | ተውሳከ ግስ | ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ |
| 5 | መስተዋድድ | መስተዋድዳዊ ሀረግ |

ስማዊ ሀረግ፡ ከስም የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው። በስማዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል ስም ነው። መሪው ከአጀቢዎች በስተቀኝ ይገኛል። ምሳሌ፡ ታታሪው ልጅ

ግሳዊ ሀረግ፡ ግስን መሰረት አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው። በግሳዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል ግስ ነው። መሪው ከአጀቢዎች በስተቀኝ ይገኛል። ምሳሌ፡ በፍጥነት መጣች

ቅጽላዊ ሀረግ፡ ቅጽልን መሰረት አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው። በቅጽላዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል ቅጽል ነው። መሪው ከአጀቢዎች በስተቀኝ ይገኛል። ምሳሌ፡ በጣም ደግ

ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ፡ ተውሳከ ግስን መሰረት አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው። በተውሳከ ግሳዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል ተውሳከ ግስ ነው። መሪው ከአጀቢዎች በስተቀኝ በኩል ይገኛል። ምሳሌ፡ በጣም ክፉኛ

መስተዋድዳዊ ሀረግ፡ መስተዋድድን መሰረት አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው። በመስተዋድዳዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል መስተዋድድ ነው። መሪው ከአጀቢዎች በስተቀኝና በስተግራ ሊገኝ ይችላል።

ምሳሌ፡ በመኪና፣ እንደ እናቱ፣ ከአባቱ ጋር

(ምንጭ፡ ጌታሁን አማረ (1989) ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው)

## መልመጃ አምስት

ሀ. የሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጋት ከየትኛው የሀረግ አይነት ውስጥ እንደሚመደቡ ግለጹ።

1. ስኬት <u>የአንድ ቀን</u> ጥ ረ ት አይደለም።
2. ቃላት <u>በስርአት</u> ተዋቅረው ሀረጋትን ይመሰርታሉ።
3. <u>በጣም ብልህ</u> ልጅ ናት።
4. <u>አሁን ገና</u> ወደትምህርት ቤት ሂደ።
5. የክፍላችን ተማሪ <u>አርፍዶ መጣ</u>።

ለ. የሚከተሉትን ሀረጋት በማገጣጠም የተሟላ አረፍተነገር መስርቱ።

1. ለቱሪስቶች ተሸጠ
2. የቆዳ ቀበቶ
3. ያ የአባቴ
4. ረጅም ቀይ
5. በውድ ዋጋ

ሐ. የሚከተሉትን ቃላት የሀረጉ መሪ በማድረግ ሀረግ መስርቱ። የመሰረታችኋቸውን ሀረጋት አይነትንም ግለጹ።

1. ጥናት
2. በላ
3. አዋቂ
4. እንደ
5. ክፉኛ

## የምእራፉ ማጠቃለያ

ምእራፍ አራት “ልቦለድ” በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፣ በውስጡም የተለያዩ ይዘቶች ተካተውበታል። በምዕራፉ ውስጥ አጭር ልቦለድን አዳምጣችሁና አንብባችሁ የአድምጦ መረዳት እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሠርታችኋል። የቃላትንና የሀረጋትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍቺም ተምራችኋል።

በምእራፉ ውስጥ የአጭር ልቦለድ ምንነት፣ ባህርያት እና አላባውያን ቀርበዋል። የአጭር ልቦለድ ባህርያት ነጠላ ውጤት፣ ጥድፊያ እና ቁጥብነት መሆናቸውን፣ የአጭር ልቦለድ አላባውያን ደግሞ ታሪክ፣ ገጸ ባህርይ፣ መቼት፣ ግጭት፣ ትልም፣ ጭብጥ፣ አንጻር እንደሆኑ ተምራችኋል።

በሰዋስው ክፍል የሀረግ ዓይነቶችን ተምራችኋል። ሀረግ ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ሰፊ መዋቅር ነው። የሀረግ ዓይነት የሚወሰነው ሀረጉን በሚመሰርተው የቃል ዓይነት ነው። በዚህም መሠረት ከስም ስማዊ ሀረግ፣ ከግስ ግሳዊ ሀረግ፣ ከቅጽል ቅጽላዊ ሀረግ፣ ከተውሳከ ግስ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ እና ከመስተዋድድ ደግሞ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊመሰረት እንደሚችል ተምራችኋል።

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. የአጭር ልቦለድን ባህርያት ከገለጻችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ካነበባችሁት ማንኛውም ልቦለድ ምሳሌ ስጡ።
2. የሚከተሉት ሀረጋት ከየትኛው የሀረግ ዓይነት ሊመደቡ እንደሚችሉ ግለጹ፡

   ሀ. ታላላቆቹን አከበረ

   ለ. ሰፋፊ ሜዳዎች

   ሐ. በትምህርት ቤት

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምእራፍ አራት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች መልሳችሁ አንብቡ።

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ካዳመጥኩት ልቦለድ የታሪኩን ትልም፣ መቼት፣ ገጸባህርያት መለየት ችያለሁ | | | |
| 2 | ያነበብኩትን ምንባብ ዋና ገጸባህርይ መለየት ችያለሁ | | | |
| 3 | የልቦለዱን ታሪክ በራሴ አገላለጽ መተረክ ችያለሁ። | | | |
| 4 | ከምንባቡ ውስጥ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 5 | የቃላትንና የሀረጋትን ተመሳሳይ ፍች መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 6 | የቃላትንና የሀረጋትን ተቃራኒ ፍች መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 7 | የሀረግ ዓይነቶችን መለየትና መመስረት ችያለሁ | | | |

# ምእራፍ አምስት

# ቃላዊ ስነጽሑፍ

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ:-

- ቃላዊ ስነጽሑፍ አዳምጣችሁ የተረዳችሁትን ትገልጻላችሁ።
- የምታውቁትን ቃላዊ ስነጽሑፍ ትናገራላችሁ።
- የቃላዊ ስነጽሑፍን ባህርያት ትገልጻላችሁ።
- ለቃላዊ ስነጽሑፍ አይነቶች ብያኔ ትሰጣላችሁ።
- የቃላዊ ስነጽሑፍ ጭብጥን ትገልጻላችሁ።
- ለቃላት አገባባዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- የሀረግ አይነቶችን ከአንቀጽ ውስጥ ታመለክታላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህራችሁ “ዶሮና ጭልፊት” የሚል ተረት ሲያነቡላችሁ አዳምጡ። ያዳመጣችሁትን መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎች ስለቀረቡ ጥያቄዎቹን በትእዛዛቸው መሠረት ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

### ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ

የቡድናችሁን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

ሀ. ዶሮ በሰማይ የማትበረው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ዶሮ መሬት የምትጭረው ለምንድን ነው?

ሐ. "ዶሮና ጭልፊት" በሚል ርዕስ የሚቀርበው ታሪክ ይዘት ምን ይመስላችኋል?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ሀ. በታሪኩ መሠረት ጭልፊት መብረር የቻለችው በምን ምክንያት ነው?

ለ. ዶሮ ወደጭልፊት ሳትሄድ ብዙ ቀናትን ያሳለፈችው ለምንድን ነው?

ሐ. ዶሮ የጭልፊትን መርፌ የምታገኝ ይመስላችኋል?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መነሻነት በቡድን በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በጽሁፍ አስፍሩ።

1. የታሪኩ ተሳታፊዎች እነማን ናቸው?
2. "ራቴም ምሳዬም መርፌው ነበር።"ያለው ማነው?ይህን ያለውስ ለምንድን ነው?
3. በታሪኩ መሠረት ዶሮ መሬት የምትጭረው ለምንድ ነው?
4. ጭልፊት የዶሮን ጫጩት ስትነጥቅ የምትታየው ለምንድነው?

5. ያደመጣችሁት ታሪክ ደራሲ ይታወቃል? መልሳችሁ "ይታወቃል" ከሆነ ደራሲው ማነው? "አይታወቅም" ከሆነለምን?

6. ያዳመጣችሁት ምንባብ ከየትኛው የስነቃል ዓይነት ይመደባል?

7. ከታሪኩ ምን ተረዳችሁ?

### ተግባር አንድ

ካዳመጣችሁት ቃላዊ ስነጽሑፍ ጋር የሚመሳሰል ሀተታተፈጥሮ በይነ መረብ ወይም ቤተመጻህፍት በመጠቀም ቃላዊ ስነፅሁፍ አሰባስባችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

# ትምህርት ሁለት: መናገር

በዚህ ትምህርት ንግግር እንድታደርጉ የሚመሯችሁ ተግባራት ቀርበውላችኋል። ተግባራቱን ትእዛዛቸውን ተከትላችሁ በትጋት ስሩ።

### ተግባር ሁለት

ከዚህ በታች በቀረቡት መነሻ ሀሳቦች ላይ በቡድን ተወያይታችሁ የቡድናችሁንም ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ።

ሀ. የምታውቁትን ተረት ለቡድን አባሎቻችሁ ተናገሩ።

ለ. በተናገራችሁት ተረት ውስጥ የተሳተፉትን አባላት ዘርዝሩ።

ሐ. የተረቱን መልዕክት ግለጹ።

### ተግባር ሦስት

በጥንድ በመሆን የሚከተሉትን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ የምታውቋቸውን እንቆቅልሾች ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር ተጠያየቁ።

ምሳሌ ሀ

ጠያቂ --- እንቆቅልህ/ሽ

ተጠያቂ --- ምን አውቅልህ/ሽ?

ጠያቂ --- ለማታምነው ፊቷ ምራቅ ነው ቅባቷ

ተጠያቂ --- ድመት

ጠያቂ --- አውቀህዋል/ሽዋል

ምሳሌ ለ

ጠያቂ --- እንቆቅልህ/ሽ

ተጠያቂ --- ምን አውቅልህ/ሽ?

ጠያቂ --- እትዬ ሰፈፏ እየተንሳፈፉ መልካም ሰፌድ ሰፉ

ተጠያቂ --- ንብ

ጠያቂ --- አውቀህዋል/ሽዋል

ምሳሌ ሐ

ጠያቂ --- እንቆቅልህ/ሽ

ተጠያቂ --- ምን አውቅልህ/ሽ?

ጠያቂ --- ባለ ካባ ባለጭራ የተከበረ ደብተራ

ተጠያቂ --- ንጉስ

ጠያቂ --- አላወከውም፤ ሀገር ስጠኝ፤

ተጠያቂ --- (ተጠያቂ ሀገር ይሰጠዋል)

ጠያቂ --- ዋለብህ አደረብህ፣

እንደ ሰርዶ ነፈሰብህ፣

እንዳልሰድብህ ወንድሜ ነህ፣

እንዳልተውህ ተፎካካሪዬ ነህ፣

ከቤትህ በታች ያለው ልምጭ፣

እንዳንተው ነጭ፤

ከዚህ እንደሮቤ

ያብርህ እንቅፋት፣

ምርት ምርቱን ለራሴ፣

ግርድ ግርዱን ለፈረሴ፣

በአንተ ጉሮሮ አጥንት ይሰንቀር፣

በኔ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር፣

ይብቃህ ወይስ ልጨምርልህ

ተጠያቂ --- ኧረ በቃኝ

ጠያቂ --- በቆሎ

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት “የስነቃል ምንነትና ባህርያት” በሚል የቀረበ ምንባብን አንብቡ። ከዚያም ምንባቡን መሠረት አድርገው የቀረቡ ጥያቄዎችን ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ስነቃል ምንድን ነው?
2. ስነቃል ለማህበረሰቡ ምን ምን ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል?
3. የስነቃል ባህርያት ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

# የስነቃል ምንነትና ባህርያት

ስነቃል በመነገር፣ በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ፣ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነጥበብ ነው። ይህ ኪነጥበብ ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙትና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰት ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሯቸው ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅምና የገጠመኞቹም ማንጸባረቂያ ነው። ይህ ቃላዊ ኪነጥበብ በተለይ ፊደል ቀርጸው በጽሁፍ በማይገለገሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ማንነትንና ምንነትን፣ እምነትን፣ የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን፣ አጠቃላይ የዓለም አመለካከትን ቀርጾ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።

በስነቃል ህዝቦች ማንነታቸውን ያሳውቁበታል፣ የዝርያቸውን አመጣጥ ይተርኩበታል፣ ስለአካባቢያቸውና በአጠቃላይ ስለዓለማቸው ያላቸውን ፍልስፍና ይቀርጹበታል። ወግና ልማዳቸውን አጠንክረው የሚያቆዩበት ዋነኛ መሳሪያቸውም ነው። ሀዘን ደስታቸውን፣ ምኞት ተስፋቸውን፣ ፍቅር ጥላቻቸውን፣ ድል ሽንፈታቸውን፣ ድጋፍ ተቃውሟቸውን በአጠቃላይ የህይወታቸውን መልኮች ያንጸባርቁበታል። ታሪካቸውን ለተከታዮቻቸው በማስተላለፍ የዝርያቸውን ተከታታይነት ያረጋግጡበታል። ሰናይ የሚሏቸው ማህበራዊ እሴቶችና ልማዶች ተጠብቀውና ተከብረው እንዲቆዩ፣ እኩይ የሚሏቸው ደግሞ እንዲወገዱ ያደርጉበታል። በአንድ ማህበረሰብ ላይ የደረሱ አስከፊ ሁኔታዎች የተፈጥሮ አደጋ፣ ስደት፣ ረሀብ፣ ወረርሽኝ፣ ጦርነት የመሳሰሉት ኑሮን አናጊ አጋጣሚዎች የነበረው አመለካከትና የደረሰበት ጉዳት በስነቃሉ አማካይነት ተቀርጾ ለተከታዩ ትውልድ ይተላለፋል።

የስነቃል ምንጭ የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ገጠመኞች ናቸው። በተለይ ከጥንታዊ የአኗኗር ዘይቤ ብዙ ባልራቁ ማህበረሰቦች በእለት ተእለት ህይወታቸው ውስጥ በሚከሰቱ የተለያዩ ግንኙነቶች ምክንያት አያሌ ስነቃሎች ይቀርባሉ። ለምሳሌ ተረቶች፣ ውዳሴ አማልክትና ዝማሬዎች፣ እንጉርጉሮዎች፣ የሙሾ ግጥሞች፣ ባህላዊ ዘፈኖች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ወጎች፣ ቀልዶች፣ አፈታሪኮች ተጠቃሾች ናቸው።

በማህበረሰብ ውስጥ ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች በስነቃል ያሉበትን ሁኔታ በማጤን ሂስ ይሰጣሉ፤ ድጋፍ ተቃውሟቸውን ይገልጻሉ፤ ያለፈውን ያስተላልፋሉ፤ የወደፊቱን ይተነብያሉ፤ የአፈጣጠራቸውን ምስጢር ይመረምራሉ። በተጨማሪም የሰውን ልጅ መሰረታዊ ባህርያት ይገነዘባሉ፤ ለህልውናቸው ምክንያት ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ነገሮች ያሞግሳሉ። ድክመት ጥንካሬንም ይመረምራሉ፤ ህጻናቱንና ወጣቶቹን ያስተምራሉ።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ባነበባችሁት የምንባብ ክፍል የስነቃል ምንጭ ተብሎ የተገለጸው ምንድን ነው?
2. እስካሁን ካነበባችሁት የንባቡ ክፍል ስነቃልን በተመለከተ የተነሱ ነጥቦች ምን ምን ናቸው?

ከስነቃል ባህርያት አንዱ አመንጭውን ወይም ደራሲውን ለማወቅ አለመቻሉ ነው። አንድን ተረት፣ ቀልድ ወይም ባህላዊ ዘፈን ለመጀመሪያ ጊዜ የተረተው፣ የተናገረው ወይም የዘፈነው እገሌ ነው ብሎ ዛሬ በደራሲነት አንድን ሰው ለመጥቀስ አይቻልም። አፈጣጠሩና ክንውኑ በጋራ በመሆኑ ባህላዊው ምግባር ለግለሰቡ ትኩረት አይሰጥም። ስነቃሉም ሀብትነቱ የማህበረሰቡ ነው። ስለዚህ የአቀንቃኙ ወይም የፈጣሪው ስም አይታወቅም። ስነቃል በቃል ከአንዱ ወደ አንዱ

የሚተላለፍ በመሆኑ መጀመሪያ ያፈለቀውን ግለሰብ ወይም ቡድን ማወቅ አይቻልም። ስነቃሉን ሲነገር ወይም ሲዜም ሰምቶ በማስታወስ መልሶ ለሌሎች ለመንገር ወይም ለማዜም የቻለ የማህበረሰቡ አባል ካንዱ ወደ ሌላው ሊያስተላልፈውና ለጊዜው ባለቤቱ ለመሆን ይችል ይሆናል። ከዚህም የተነሳ ነው ስነቃል የህዝብ ሀብት ነው እየተባለ የሚነገርለት። የባህሉ ሰው የሆነ ሁሉ ችሎታው ካለው ከመተረትና ከማዜም የሚያግደው አይኖርም። ምንም እንኳን የአንድን ስነቃል ደራሲ ለይቶ ማወቅ አይቻልም ቢባልም ቀደም ባለጊዜ አንድ የፈጠራ ችሎታ ያለው ሰው የፈጠረው መሆኑን እንገነዘባለን። የግለሰቡ ኪናዊ ፈጠራ አሻራም እንዳለበት ግልጽ ነው። ስነቃሉን ካንዱ ሰምቶ ለሌላ የሚነግረው፣ የሚተርተው ወይም የሚያዜመው ደግሞ የራሱን ፈጠራ በመጨመር ለሌላ ያስተላልፈዋል። ከዚህም የተነሳ "ስነቃል ብዙ ህልውና አለው" ይባላል።

አፈጣጠሩና ክንውኑ በጋራ በመሆኑ ስነቃሉ ቡድናዊ ተግባር ነው። ብዙዎቹ የስነቃል ዓይነቶች ባንድ ሰው ብቻ የሚባሉ አይደሉም። ብዙዎቹ በህብረት የሚነገሩ፣ የተናጋሪንና የአድማጭን ተሳትፎ የሚጠይቁ ናቸው። ለምሳሌ በተረት ተራች አለ፤ ተረቱን የሚያዳምጡ አሉ። ተረቱ በሚተረትበት ጊዜ አድማጮቹ ዜማ ካለው አብረው ያዜማሉ፤ ተራቹ ጥያቄ ቢጠይቃቸው ይመልሳሉ ወይም እንደተረቱ ባህርይ በአንድ ነገር ይሳተፋሉ። በባህላዊ ዘፈንም አቀንቃኝ አለ፤ ተሳታፊዎች ወይም ደግሞ ተቀባዮች አሉ። በድምጻቸው ያጅባሉ፤ ያጨበጭባሉ ወይም ከዘፈኑ ጋር የሚዛመድ የሰውነት እንቅስቃሴ ያደርጋሉ። የስነቃል የተሳታፊነት ወሰንና አግባብ እንደየስነቃሉ ዓይነት ይለያያል። ለምሳሌ በእንቆቅልሽ የጥያቄና መልስ ተሳትፎ ጊዜ ስህተት ቢፈጠር አድማጩ ማረሚያ ሊሰጥ ይችላል። በፉከራ አይዞህ! በርታ! በማለት ማደፋፈር የተለመደ ነው። በሙሾ ደግሞ ዋይ! ዋይ! እያሉ ደረት መምታት፣ እጅ ማርገብገብ ወይም መዝለል ይኖራል። የስነቃል አይነቶች የራሳቸው የሆነ ቡድናዊ አሰራር አላቸው።

ስነቃል ብዙውን ጊዜ የሚቀርበው በአጫጭር ቅርጾች ነው። የሰው የማስታወስ አቅም የተወሰነ በመሆኑና የስነቃሉም ተሳታፊዎች በአንዳንድ አሰባሳቢ አጋጣሚዎች በመገኘት ሊያዳምጡና ሊመለከቱ የሚችሉት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ቆይታ በመሆኑ ከጊዜውና ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝ ለመሆን የግድ በአጫጭር ቅርጾች መቅረብ ይኖርባቸዋል። በአንጻሩ ደግሞ በአንዳንድ አካባቢዎች እንደ "ኤፒክ" ያሉ ረጃጅም የስነቃል ቅርጾች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም። እስከአሁን ከተገለጸው በመነሳት ስነቃል ሁለት ዋነኛ ባህርያት አሉት ማለት ይቻላል። እነሱም ክዋኔና ተለዋዋጭነት ናቸው።

(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነጽሑፍ መሰረታውያን፣ 2005፣ 20-22፣ ለማስተማሪያነት እንዲያመች ተሻሽሎ የቀረበ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።**

1. ሙሾ በመተረት የሚገለጽ የስነቃል ዓይነት ነው።
2. የስነቃል ባለቤት በውል ስለማይታወቅ የሕዝብ ሀብት ነው ይባላል።
3. ስነቃል አፈጣጠራዊ ክንውኑ በጋራ የሚከወን በመሆኑ ቡድናዊ ባህርይ አለው።
4. ስነቃል በደራሲው ተጽፎ በመተረትና በመዜም ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል።
5. በስነቃል አማካይነት ማንነትን ማሳወቅ፣ ምኞትና ተስፋን ማንጸባረቅ ይቻላል።

6. ስነቃሎች ከትውልድ ወደትውልድ በሚተላለፉበት ጊዜ ምንም ነገር አይጨመርበትም፤ አይቀነስበትም።

**ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተገቢውን መልስ ምረጡ።**

1. ቀጥሎ ከቀረቡት የስነቃል አይነቶች ውስጥ በአቀራረብ ቅርጽ ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ተረት ለ. አፈታሪክ

ሐ. ቀረርቶ መ. እንቆቅልሽ

2. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የስነቃል ዋነኛ ባህርያት ተብለው የሚጠሩት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ቡድናዊና ባለቤት የለሽ ለ. ክዋኔና ተለዋዋጭነት

ሐ. ክዋኔና ሀሳብ አመንጭነት መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ስነቃልን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የበርካታ ገጠመኞች ነጸብራቅ ነው።

ለ. በተገኘው አጋጣሚ ይቀርባል።

ሐ. የህይወት መልኮች ነጸብራቅ ነው።

መ. የተደራሲያንን ተሳትፎ አይፈልግም።

4. "አንድ ሰው የሰማውን ተረት ለሌላ ሰው በሚናገርበት ጊዜ በጎደለው እየሞላና የራሱን ፈጠራ እያከለ ይናገራል።" የሚለው የትኛውን የስነቃል ባህሪ ያመለክታል?

ሀ. የህዝብ ሃብትነት ለ. የተለዋዋጭነት

ሐ. የአውዳዊነት መ. የተከዋኝነት

5. በምንባቡ መሰረት ስነቃል በአጫጭር ቅርጾች የሚቀርበው ለምንድን ነው?

   ሀ. የተሳታፊዎች የመከታተያ ጊዜ ውሱን ባለመሆኑ
   ለ. ትረካው ከጊዜውና ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝ በመሆኑ
   ሐ. የሰው ልጅ የማስታወስ አቅሙ የተወሰነ በመሆኑ
   መ. ሁሉም መልስ ናቸው።

# ትምህርት አራት: መጻፍ

በዚህ ትምህርት ስለስነጽሑፍ ጉዳዮች እንድትጽፉ የሚያግዙ ተግባራት ስለቀረቡላችሁ በትእዛዛቸው መሰረት ጻፉ።

## ተግባር አራት

ያነበባችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ቃላዊ ስነጽሑፍ በጽሑፍ ከሚቀርብ ስነጽሑፍ የሚለይበትን ባህሪ ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ አስፍሩ።

| ቃላዊ ስነጽሑፍ | ጽሑፋዊ ስነጽሑፍ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |

## ተግባር አምስት

ከዚህ በታች የቀረቡትን ምሳሌያዊ ንግግሮች መልእክት አብራርታችሁ ጻፉ። ከዚያም መምህራችሁ በሚያብራሩላችሁ መሰረት የምሳሌያዊ አነጋገሮቹን ተግባራት ወስኑ።

1. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር፤
2. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ፤
3. ሳይርቅ በቅርቡ፣ ሳይደርቅ በርጥቡ፤
4. ቀይና ወርቅ፣ ሲብለጨለጭ ያልቅ፤
5. ጤፍ ከነወንድሟ ጎተራ ትሞላለች፤

6. ላም እሳት ወለደች፤ እንዳትልሰው ፈጀች፤

   እንዳትተወው ልጅ ሆነባት፤

## ተግባር ስድስት

ቀጥሎ በቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች ላይ በጥንድ በመወያየት የያዙትን መልዕክት ጻፉ።

ሀ. ገበሬ ቢኮራ ምርቱን አምርቶ ነው፣

   ነጋዴ ቢኮራ ትርፉን አትርፎ ነው፣

   የሰነፍ ኩራቱ ከምን የመጣ ነው?

ለ. በጎምላላ በሬ ሂድ ብሎ ሂድ ብሎ፣

   ቆርቆሮ አለበሰ ሳሩን ወዲያ ጥሎ፤

ሐ. ቁም ነገረኛ ሴት ለትዳሯ ጠጅ፣

   የልብ ታደርሳለች በቤትም በደጅ፤

መ. የአባይ ውሀ ሞልቶ በዘንግ ይታሰሳል፣

   ያንተ ልብ እንዴት ነው የኔስ ይዋልላል፤

ሠ. የፈተለች እንደሁ አስመስላ ጭራ፣

   የጋገረች እንደሁ አስመስላ ሞራ፣

   የጠመቀች እንደሁ የማሩን ወለላ፣

   እሷን የሠራ 'ለት አልሠራም ወይ ሌላ፤

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

ቀጥሎ በአረፍተነገር ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት ቀርበውላችኋል። ለቃላቱ አገባባዊ ፍቺ ስጡ።

## መልመጃ ሦስት

ሀ. ቀጥሎ በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላትና ሀረጋት አገባባዊ ፍቺ ስጡ።

1. ስነቃል የሕብረተሰብ ቅርስ ነው።
2. ስነቃል ሰናይ የሚባሉ ማህበራዊ እሴቶችና ተጠብቀውና ተከብረው እንዲቆዩ ያደርጋል።
3. ስነቃል እኩይ የሚባሉ ልማዶች እንዲወገዱ ያደርጋል።
4. ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች በስነቃል ያሉበትን ሁኔታ በማጤን ሂስ ይሰጣሉ።
5. ስነቃል የግለሰብ ኪናዊ ፈጠራ አሻራ እንዳለበት ግልጽ ነው።
6. ከስነቃል ባህርያት አንዱ አመንጭውን ወይም ደራሲውን ለማወቅ አለመቻሉ ነው።

ለ. አገባባዊ ፍቺ በሰጣችኋቸው ቃላት የራሳችሁን አረፍተነገር መስርቱ።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት በምእራፍ አራት የተማራችሁትን የሀረግ አይነቶች ከከለሳችሁ በኋላ ቀጥሎ የቀረበውን መልመጃ ስሩ።

## መልመጃ አራት

ከዚህ በታች ከቀረበው አንቀጽ ውስጥ ስማዊ ሀረግና መስተዋድዳዊ ሀረግ የሆኑትን በመለየት በምሳሌው መሰረት በሰንጠረዡ ውስጥ አስፍሩ።

አካባቢው እንደስንሰለት ተያይዘው ከአድማስ አድማስ ከአይን እየራቁ በሚነጉዱ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ከመሬት ወደ ህዋው ቀጥ ብለው በሚወረወሩ ሹል ድንጋያማ ተራራዎች የተሞላ ነው። ተደራርበው የተቀመጡት ያገጠጡ ድንጋዮች ተፈጥሮ በዘመናት የቆለላቸው አይመስሉም።

| | ስማዊ ሀረግ | መስተዋድዳዊ ሀረግ |
|---|---|---|
| 1 | ድንጋያማ ተራራዎች | እንደስንሰለት |
| 2 | | |
| 3 | | |
| 4 | | |

## የምእራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በማዳመጥ ክፍል ውስጥ ባዳመጣችሁት ትረካ አማካይነት የታሪኩን ተሳታፊዎች፣ ትረካው ግላዊ ባለቤት የሌለው መሆኑንና በየትኛው የስነቃል ክፍል ውስጥ እንደሚመደብ፣ የታሪኩ መልዕክት (ጭብጥ) ምን እንደሆነ ተምራችኋል።

በክፍል ሁለት በቡድን በመሆን ባቀረባችሁት ተርት መሠረት የተረቱን ተሳታፊዎችና መልዕክቱን በመግለጽ ተለማምዳችኋል። የእንቆቅልሽ አከዋወንን በቀረበላችሁ ምሳሌና በጻፋችኋቸው እንቆቅልሾች አማካይነት ተለማምዳችኋል። በክፍል ሦስት የስነቃል ምንነትንና ባህርያትን በቀረበው ምንባብና በሠራችኋቸው መልመጃዎች አማካይነት ተምራችኋል። በክፍል አራት ደግሞ በቃላዊ ስነጽሁፍ ምንነት ላይ ተወያይታችኋል። ቃላዊ ስነጽሁፍ (ስነቃል) ከጽሁፋዊ ስነጽሁፍ የሚለይበትን ባህሪ፣ የስነቃልን ተግባራት፣ዓይነቶች ለይታችኋል፤ የምሳሌያዊ ንግግርን መልዕክት (ጭብጥ) ተምራችኋል፡

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች ከክፍል ጓደኞቻችሁ ጋር በመወያየት መልሱ።

1. ስነቃል ማለት ምን ማለት ነው?
2. ሁለት እንቆቅልሾች ጻፉ።
3. የስነቃል ባህርያት ምን ምን ናቸው?
4. ስነቃል ለማኅበረሰቡ የሚኖረውን ፋይዳ ግለጹ።

5. በመዜም ከሚቀርቡ የስነቃል ዓይነቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ጻፉ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች እንደገና አንብቡ።

| | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥኩትን ተረት መልእክት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | የስነቃልን ጽንሰ ሀሳብ መለየት ችያለሁ | | | |
| 3 | የእንቆቅልሽ ጥያቄዎችን መጻፍና መልሳቸውን መመለስ ችያለሁ | | | |
| 4 | የስነቃልን ባህርያት መለየት ችያለሁ | | | |
| 5 | የስነቃል ዓይነቶችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 6 | በመነገር፣ በመተረትና በመዜም የሚቀርቡት የስነቃል ዓይነቶችን መዘርዘር ችያለሁ | | | |
| 7 | የስነቃልን ጭብጥ (መልዕክት) መግለጽ ችያለሁ | | | |

# ምእራፍ ስድስት

# ግጥም

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- የግጥሙን ሀሳብ ካዳመጣችሁ በኋላ በቃላችሁ ትገልጻላችሁ።
- በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሱ የተለያዩ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን ትለያላችሁ።
- የቅስቀሳ እና የማነቃቂያ ንግግር ይዘትን ትለያላችሁ።
- የግጥም ባህርያትን፣ አይነቶችንና ሙያዊ ቃላትን ትለያላችሁ።
- የቃላትን መዝገበቃላዊ፣ አገባባዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ፤ በቃላቱም ግጥም በመጻፍ ትለማመዳላችሁ።
- ቅጥያዎችን ከዋና ቃል ትለያላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

መምህራችሁ "መስከረም ሲጠባ" በሚል ርእስ የቀረበ ግጥም ሲያነቡላችሁ በጥሞና አዳምጣችሁ መልመጃዎችንና ተግባራትን ስሩ።

## ቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ተማሪዎች ከአሁን በፊት ግጥም አንብባችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ "አዎ" ከሆነ እስኪ የምታስታውሱትን ግጥም ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው።
2. ግጥም ምንድን ነው? በቡድን ተወያዩና መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በተወካዮቻችሁ አማካኝነት ግለጹላቸው።

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ግጥሙ የሚናገረው ስለየትኛው ወቅት ነው?
2. ወቅቱን እንድታውቁ የረዱችሁ ስንኞች የትኞቹ ናቸው?
3. በግጥሙ ውስጥ "መሬት ትታያለች የክት ልብሷን ለብሳ" የሚለው ስንኝ በምን አይነት ዘይቤ የተገለጸ ነው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡት ስንኞች ካዳመጣችሁት ግጥም ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። በየስንኞቹ ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት እና ሀረጋት በምሳሌው መሰረት በሌሎች ተመሳሳይ ቃላትና ሀረጋት ተኳቸው። ስትተኳቸው የግጥሙን ስልተምት እንዳያናጋ ጥንቃቄ አድርጉ።

ምሳሌ፡ ስንዴ <u>ጨበጨበ</u> እሸቱ ደረሰ።

ስንዴ <u>ተዘናፍሎ</u> እሸቱ ደረሰ።

1. ዝናቡም ሲፈጸም ተከተለ <u>ብራ</u>።
2. <u>ካፋፍ</u> ላይ ሲያስተውሉት አገሩን በሰፊ፣
3. ደመና እየሸሸ ሰማዩ <u>ሲጠራ</u>፣
4. ያበቦቹ ሽታ አየሩን <u>አደሰው</u>።

ለ. ያዳመጣችሁት ግጥም በአብዛኛው የተጻፈው በየትኛው ዘይቤያዊ አገላለጽ ነው? ካዳመጣችሁት ግጥም ምሳሌ ስጡ።

ሐ. የግጥሙን መልእክት በአጭሩ አብራሩ።

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት "አደን" በሚል ርእስ የቀረበ ግጥምን መሰረት ያደረገ የንግግር ተግባር ቀርበውላችኋል። ተግባሩን ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

ተግባር አንድ

ሀ. የሚከተለውን ግጥም በግጥም የአነባበብ ስልተምት መሰረት አንብቡ።

### አደን

አሣዳጄን አመለጥኳት፣
አመለጠችኝ ያሣደድኳት።
ፏሪ ሆንኩኝ እንደፍየል፣
በነብርና ቅጠል መሀል።
አቤት አለች ያልጠራኋት
የጠራኋት ድምጽም የላት።
ራቂኝ 'ምላት ጎኔ ወድቃ፣
ቅረቢኝ 'ምላት ከኔ ርቃ።
አንዴ ስታደን አንዴም ሳድን፣
እረፍት አጥቼ ስባክን።
የእድሜዬን ጀንበር ብታዘባት
ልትጠልቅ ምንም አልቀራት።

(ደበበ ሠይፉ፣ 1992)

ለ. የግጥሙ ገጸባህሪይ ራሱን ከምን ጋር አነጻጸረ?

ሐ. ከጥያቄ "ለ" መልስ በመነሳት ግጥሙ ምን አይነት ዘይቤ ጎልቶ ታይቶበታል?

ተግባር ሁለት

በቡድን በመወያየት በግጥም እና በዝርው ትረካ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ። በቀረበው ምሳሌ መሠረት የሁለቱንም ልዩነት ለማመልከት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተጠቀሙ።

| የግጥምና የዝርው ትረካ ልዩነት | |
|---|---|
| ግጥም | ዝርው |
| ስንኞቹ በአንድ አንድ መስመር እየተጻፉ ወደታች ይደረደራሉ | ዐረፍተ ነገሮቹ በመስመሮቹ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው መስመር ተከታትለው ይጻፋሉ |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

## ተግባር ሦስት

### የቅስቀሳና የማነቃቂያ ንግግር ምሳሌ

*መማርና መረጃ መሰብሰብ ለየቅል ናቸው። ትምህርት ቤት በመግባት መረጃ አእምሮ ውስጥ ስለተጠራቀመ ብቻ ትምህርት ተገኝቷል ማለት አይቻልም። የመረጃ መጋዘን መሆን ብቻ ትልቅ ነገር አይደለም። ትምህርት መረጃ በማጠራቀም ከሆነ በእጃችን የያዝነው ስልክ ከኛ የተሻለ መረጃን የመያዝ አቅም አለው።*

*መማር ማለት ማሰብ ማለት ነው። እውነተኛ ትምህርት አእምሮ የሚሰራበትን መንገድ ተረድቶ እሱን በአግባቡ መጠቀም ነው። ቀለበት ያላት ፕላኔት የቷ እንደሆነች ማወቁ ብቻውን ጥቅም የለውም። የማንትስ ሀገር ዋና ከተማ ስምን ማወቁ ብቻውን ጥቅም የለውም። አእምሮን በሆነ ባልሆነ መረጃ ማጨናነቁ ብቻውን ትርፉ በራስ ላይ ውዝግብ መፍጠር ነው። ዋናው ነገር መረጃውን ከተግባር ጋር ማገናኘትና ወደተግባር ማሸጋገር ነው። አእምሮ የሚለኮስ ሻማ እንጂ የሚሞላ ሳጥን መሆን የለበትም።*

ከላይ የቀረበው የቅስቀሳ (አንድን ነገር እንድታደርጉ የሚገፋፋ) እና የማነቃቂያ (በአንድ ነገር ላይ ያላችሁን እምነት እንድታጠናክሩ የሚያደርግ) ንግግር ምሳሌ ነው። ይህ ንግግር

- ምን እንድታደርጉ ገፋፋችሁ?
- ምን አይነት ጉዳይ ላይ እምነታችሁ እንዲጠናከር አለመ?
- እስቲ ከዚህ ቀደም ያዳመጣችሁትን የቅስቀሳ ወይም የማነቃቂያ ንግግር ለጓደኛችሁ ንገሩ።

## ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት "የግጥም ዘይቤ" በሚል ርእስ የቀረበ ምንባብን መሰረት ያደረጉ የቅድመማንበብ፣ የማንበብ ጊዜና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎቹን ትኩረት ሰጥታችሁ ስሩ።

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ዘይቤ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የምታውቁትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ።
2. የምታውቋቸውን የዘይቤ አይነቶች ዘርዝሩ።

# የግጥም ዘይቤ

ዘይቤ አንድን ሃሳብ ወይም ድርጊት፣ የአንድን ነገር ቅርጽ፣ የሰውን ባህሪ፣ ስሜትና መልክ አጉልቶና አድምቆ ለአንባቢም ሆነ ለአድማጭ ምናባዊ ፍስሃ በመስጠት የሚቀርብ የአነጋገር ስልት ሲሆን በግጥምም ሆነ በዝርው ጽሁፍ ውስጥ ሊቀርብ ይችላል።

በቋንቋው ውስጥ በርካታ የዘይቤ ዓይነቶች አሉ። ዋና ዋና ከሚባሉት ውስጥ ሰውኛ ዘይቤ፣ እንቶኔ ዘይቤ፣ ተለዋጭ ዘይቤ፣ አነጻጻሪ ዘይቤ እና ግነት ዘይቤ ይጠቀሳሉ።

ሰውኛ ዘይቤ የሰውን ልዩ ልዩ ባህርያት፣ ድርጊት፣ መልክ፣ ችሎታ፣ ወዘተ. ሰው ላልሆኑ ህይወት ላላቸውና ለሌላቸው ነገሮች በመስጠት፣ የሰውን ባህርይ በማላበስ፣ እንዲሁም አንደበታዊ በማድረግ የሚገለጽ ነው።

ምሳሌ፡ እህል ዱር አደረ ብቻውንም ዋለ፣

ጠላት እንደሌለው ሰው እንዳልገደለ።

እንቶኔ ዘይቤ ከሰውኛ ዘይቤ ጋር ተቀራራቢ ሲሆን በአጠገባችንና በቅርብ የሌለን ረቂቅና ግዑዝ ነገር፣ በህይወት የሌለ፣ እንዲሁም የማይናገሩ እጽዋትና እንሰሳት በቅርብ እንዳሉና መልስ እንደሚሰጡ በመቁጠር የሚመሰረት የዘይቤ ዓይነት ነው። ይህ ዘይቤ ከላይ የተጠቀሱትን ነገሮች በመማፀን፣ በመለመን፣ በማመስገን፣ በመመረቅ ወይም በመርገም፣ በመጠየቅ፣ በማዋየትና መልስ እንደሚሰጡ በመቁጠር የሚፈጠር ዘይቤ ሲሆን፣ በሁለተኛ መደብ (አንተ፣ አንቺ፣

እናንተ) ተውላጠ ስም ይቀርባል።

ምሳሌ፡ አዕዋፍ በጠዋቱ ተነሳ እምትሉኝ ለምን ይሆን ከቶ፣

ባማረ ድምጻችሁ መስኮቴ ተንኳኩቶ።

በሉ እኔስ ተነሳሁ ነቃሁኝ ታግዬ፣

አዎ! በእርግጥ ነግቷል የሰው እግር ታዬ።

ግን ልጠይቃችሁ አዕዋፍ በያይነቱ፣

ነጋ ጠባ ባዮች ሰርክ በየጠዋቱ።

ያነጋችሁት ቀን ባማረ ዜማችሁ፣

ለማን እንደጠባ ግን ታውቁታላችሁ?

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በምሳሌ የቀረቡ ሁለቱ ግጥሞች ዘይቤዎቻቸው ምን ምን ናቸው?
2. ግጥሞቹ የጠቀሳችኋቸውን ዘይቤዎች አሏቸው ያላችሁት ከምን ተነስታችሁ ነው?

በቀጣይ የሚቀርቡላችሁ ዘይቤዎች ምን ሊሆኑ ይችላሉ? ተለዋጭ ዘይቤ በነገሮች መካከል የባህሪ ምስስል በመፍጠር የአንዱን ባህሪና መልክ ለሌላው በመስጠት የሚፈጠር የዘይቤ ዓይነት ነው። ይህ ዘይቤ አንድ ቃል ወይም ሀረግ የአንድን ሰው፣ እንስሳ፣ ተክል ወይም ግዑዝ አካል ባህርይ፣ መልክ፣ ቅርጽ ወይም ድርጊት ወስዶ ለሌላ በመስጠት ተገላጩን የበለጠ እንዲጎላና ምስል እንዲፈጥር የሚያደርግ ነው።

ምሳሌ፡ አባቱ ነበር የጣር ገበሬ፣

ልጁ ደረሰ የወይፈን በሬ።

አነጻጻሪ ዘይቤ ሁለት ነገሮች፣ ባህሪዎች፣ ድርጊቶችና ሃሳቦች በሚመሳሰሉባቸው ገጽታዎችና የጋራ ባህርያት እየተነጻጸሩ የሚቀርቡበት የአገላለጽ ስልት ነው። ይህ የዘይቤ ዓይነት እንደ፣ ያህል፣ ይመስል፣ ወዘተ. የማነጻጸሪያ ቃላትን ይጠቀማል።

ምሳሌ፡ ብቸኝነት ጥምቡሳሱ፣

የፍርሀት ግሳንግሱ።

እንዳልተገራ ፈረስ ሲያደባየኝ፣

እንደደራሽ ውሃ ሲያፍነኝ።

እንደተጋለጠ ሐሜት ሲሰብረኝ፣

አለ "በርታ! ጠና በል" የሚለኝ።

ግነት ዘይቤ ነገሮችንና ሁኔታዎችን ካላቸው ነባራዊ ሁኔታ በላይ ሆን ብሎ በማግዘፍና በማግነን የማቅረብ ሁኔታ ነው።

ምሳሌ፡ አልማዝ ያስነጠፈች

ወርቅ ያስጎዘጎዘች፣

በቫነር በዲዩር ሽቱ የታጠበች፣

በጌጥ ተብረቅርቃ

ጌጥ ሆና ጌጥ ይዛ

ጨረቃ ታፍራለች

ፀሀይ ትጠፋለች፣

ፀዳል፣ ብርሃን፣ ንጋት

ሁሉን ታስንቃለች።

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።

1. ዘይቤ በግጥምም ሆነ በዝርው ጽሁፍ ውስጥ ሊቀርብ የሚችል የአነጋገር ስልት ነው።
2. ሰው ያልሆኑ ነገሮችን የሰውን ባህርይ በማላበስ የሚገለጽ የአነጋገር ስልት እንቶኔ ዘይቤ ይባላል።
3. በቅርብ የሌለን ረቂቅና ግዑዝ ነገሮች መልስ እንደሚሰጡ በመቁጠር በማናገር የሚፈጠር ዘይቤ ሰውኛ ዘይቤ ይባላል።
4. የአንዱን ባህሪና መልክ ለሌላው በመስጠት የሚፈጠር የዘይቤ አይነት አነጻጻሪ ዘይቤ ይባላል።
5. እንደ፣ ያህል፣ ይመስል፣ ወዘተ. የማነጻጸሪያ ቃላትን በመገልገል የሚገለጽ ዘይቤ ተለዋጭ ዘይቤ ተለዋጭ ዘይቤ ይባላል።
6. ሰዎችን ወይም ነገሮችን ካላቸው ነባራዊ ሁኔታ በላይ ሆን ብሎ በማግዘፍና በማግነን የማቅረብ ዘይቤ ግነት ዘይቤ ይባላል።

ለ. በ"ሀ" ስር የቀረቡትን የዘይቤ አይነቶች በ"ለ" ስር በምንባቡ ከተገለጹት ምሳሌዎቻቸው ጋር አዛምዱ።

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| 1. ተለዋጭ ዘይቤ | ሀ. ፀዳል፣ ብርሃን፣ ንጋት ሁሉን ታስንቃለች። |
| 2. አነጻጻሪ ዘይቤ | ለ. ልጁ ደረሰ የወይፈን በሬ። |
| 3. ሰውኛ ዘይቤ | ሐ. አዕዋፍ በጠዋቱ ተነሳ እምትሉኝ ለምን ይሆን ከቶ? |
| 4. እንቶኔ ዘይቤ | መ. እህል ዱሩ አደረ ብቻውንም ዋለ። |
| 5. ግነት ዘይቤ | ሠ. ብቸኝነት እንደ ደራሽ ውሃ አፈነኝ። |

**ሐ. የሚከተሉት ግጥሞች ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ግጥሞቹን ድምጻችሁን ከፍ በማድረግ ተራ በተራ ለክፍል ተማሪዎች ካነበባችሁ በኋላ ግጥሞቹን በተመለከተ የቀረቡላችሁን ጥያቄዎች በቡድናችሁ በመወያየት መልሱ።**

1. "እህል ዱር አደረ ብቻውንም ዋለ፣

   ጠላት እንደሌለው ሰው እንዳልገደለ።" በሚለው ግጥም

   - ግጥሙን ሰውኛ ዘይቤ ያሰኘው ጉዳይ ምንድን ነው?
   - የሰውን በህሪይ የተለባሰው ምንድን ነው?
   - ምን አይነት የሰው ባህሪይን ተላበሰ?

2. "ግን ልጠይቃችሁ አእዋፍ በያይነቱ፣

   ነጋ ጠባ ባዮች ሰርክ በየጠዋቱ።" በሚለው ግጥም

   - ግጥሙን እንቶኔ ዘይቤ ያሰኘው ጉዳይ ምንድን ነው?
   - ጸሀፊው ለማን ጥያቄ እያቀረበ ነው?
   - ምን ጠየቀ?
   - ጥያቄው መልስ የሚያገኝ ይመስላችኋል? ለምን?

3. "አባቱ ነበር የጣር ገበሬ፣

   ልጁ ደረሰ የወይፈን በሬ።" በሚለው ግጥም

   - ግጥሙን ተለዋጭ ዘይቤ ያሰኘው ጉዳይ ምንድን ነው?
   - የማን በህሪይ ለማን ተሰጠ?
   - ሌላ ባህሪይ የተሰጣቸው ገጸባህሪያት ለምን ባህሪዩ የተሰጣቸው ይመስላችኋል?

4. "እንዳልተገራ ፈረስ ሲያደባየኝ፣

   እንደደራሽ ውሃ ሲያፍነኝ።" በሚለው ግጥም

- ተነጻጻሪ ዘይቤ ያሰኘው ጉዳይ ምንድን ነው?
- ምን እና ምን ተነጻጸሩ?
- ማነጻጸሪያ ቃሉ የትኛው ነው?
- ሁለቱ ገጸባህሪያት በምን ባህሪይ ተነጻጸሩ?

5. “አልማዝ ያስነጠፈች

ወርቅ ያስጎዘጎዘች፣

በቫነር በዲዩር ሸቱ የታጠበች፣” በሚለው ግጥም

- ገጸባህሪይዋ ማን ትመስላችኋለች?
- ግጥሙን ግነት ዘይቤ ያሰኘው ጉዳይ ምንድን ነው?

ተግባር አራት

ዘይቤያዊ አነጋገርን የያዘ ግጥም ከተለያዩ ምንጮች በመፈለግ ወደክፍል በማምጣት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው። ግጥሙ የተጻፈበትን ዘይቤውንም ግለጹላቸው።

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ክፍል ስለግጥም ጉዳዮች እንትጽፉ የሚያግዙ ማስታወሻና ተግባራት ስለቀረቡላችሁ ማስታወሻውን ካነበባችሁ በኋላ ተግባራቱን በትእዛዛቸው መሰረት ስሩ።

## 1. የግጥም ባህርያት

ግጥም እንደአንድ ኪናዊ የመግባቢያ ዘዴ በተለይ ከዝርውና ከዕለት የዕለት ንግግር የሚለይባቸው በርካታ ባህርያት አሉት። እነዚህም ተጨባጭነት፣ እምቅነት እና ቁጥብነት፣ ሙዚቃዊነት፣ ምናባዊነት እና ተውኔታዊነት ናቸው።

ሀ. ተጨባጭነት፡ ገጠመኞችን፣ ስሜቶችን፣ አተያዮችን ወይም የገጣሚው ግንዛቤ አንድ የተወሰነ ተጨባጭ ሁኔታን ወይም ድርጊትን በማቅረብ ወይም በመሳል ይገለጣል።

ለ. እምቅነት እና ቁጥብነት፡ ግጥም ቁጥብ ነው። ቁጥብነቱም እምቅ ስለሆነ ነው። ግጥም ቁጥብ ነው ሲባል ስለአንድ ነገር ለመናገር ዝርዝር ነጥቦችን አያቀርብም፤ እነሱን አይተነትንም፤ አያብራራም ማለት ነው።

ሐ. ሙዚቃዊነት፡ ግጥም ሙዚቃዊ ነው። አንዱ ሀረግ ተብሎ (ተነቦ) ከትንሽ እረፍት ወይም ቆምታ በኋላ ተከታዩ ሲቀጥል የሚፈጠረው የአነባበብ ተከታታይነት ምት የጠበቀ ከሆነ ዜማው ሙዚቃዊ ቃናውን ጠብቆ ይሄዳል።

መ. ምናባዊነት፡ ግጥም በተጻፈው ወይም በተነገረው ቃል ኃይል አማካኝነት አንባቢ በዓይነ ህሊናው የሚያየውን ሰዕል፣ በእዝነ ህሊናው የሚሰማውን ድምጽ የመፍጠር ሃይል አለው።

## 2. የግጥም ሙያዊ ቃላት

ቀደምት ከሆኑት የስነጽሁፍ ዘርፎች አንዱ ስነግጥም ነው። የሰው ልጆች ሀሳባቸውን በጽሁፍ መግለጽ ከመጀመራቸው በፊት ግጥም በቃል ሲባል የኖረ ነው። ግጥም የጠበቀ ምት ያለው በምርጥ ቃላት እና ምስል ከሳች በሆኑ ዘይቤዎች ተመጥኖ የሚቀርብ ነው።

ግጥም የተለያዩ ሙያዊ ቃላት አሉት። ከእነሱም መካከል ቀለም፣ ስንኝ፣ ሀረግ፣ ቤት፣ ቤት ደፋ፣ ቤት አፈረሰ፣ አንጓ (አርኬ) ይጠቀሳሉ።

ሀ. ቀለም፡ በግጥም ውስጥ ጫን ተብሎ የሚነበብ ሆሄ ቀለም ይባላል። (ከዚህ በታች በተራ ቁጥር 2 በግጥም አይነቶች ማስታወሻ ስር በተሰጡት ምሳሌዎች ጎልተው የተጻፉት ቀለማት ናቸው) ለ. ስንኝ፡ የግጥም አንድ መስመር ተሳክቶ ሲያበቃ ስንኝ ይባላል።

ምሳሌ፡ እንደሀምሌ ወራት/ ፊቷ ጭጋግ ለብሶ፣ እንደመኸር ድርቆሽ/ ልብሷ ተልኮስኩሶ፣ አየኋት አየኋት/ እንዲቱን ቀዘባ፣ ዘንጠፍ ዘና ብላ/ እንደመስከ አበባ።

ከላይ የቀረበው ግጥም በአራት መስመሮች ላይ የሰፈሩ ሀሳቦች አሉት። ስለዚህ ግጥሙ አራት ስንኞች አሉት ማለት ነው።

ሐ. ሀረግ፡ በአንድ ትንፋሽ የሚነበብ የስንኝ አካል ነው። ከላይ በቀረበው ባለአራት ስንኝ ግጥም በአንድ ትንፋሽ የሚነበቡ ስምንት ሀረጎች አሉት። በህዝባር ተለይተው የተመለከቱት ሀረጎች ናቸው።

መ. ቤት፡ አንድ ስንኝ ተሳክቶ የሚያበቃበት ፊደል ቤት ይባላል። ከላይ በቀረበው ግጥም ቤት የሚባሉት "ሶ" እና "ባ" ናቸው።

ሠ. ቤት መታ፡ የመጀመሪያ ስንኝ ከሚቀጥለው ስንኝ ጋር በቀለሞች መጠን እንዲሁም በስንኝ መድረሻ ሆሄ ተመሳሳይ ሆኖ ሲጠናቀቅ ቤት መታ ይባላል። ከላይ የቀረበውን ግጥም በምሳሌነት መውሰድ ይቻላል።

ረ. ቤት ፈረሰ፡ የአንድ ግጥም ስንኞች በቀለሞች መጠን እንዲሁም በስንኝ መድረሻ ሆሄ ካተመሳሰሉ ቤት ፈረሰ ይባላል።

ሰ. አንጓ (አርኬ)፡ በተመሳሳይ ሆሄ ከሚጨርሱት ሆሄ መካከል በአራ ነጥብ የሚጠናቀቀው የግጥም አንድ ሃሳብ ማቅረቢያ ክፍል አንጓ ወይም አርኬ ይባላል። ከላይ የቀረበው ግጥም አንድ አንጓ ነው።

## 1. የግጥም አይነቶች

በአማርኛ ግጥም ተዘውታሪነት ያላቸው የተለያዩ የምጣኔ ስልቶች አሉ። የግጥም ዓይነቶች በሀረግ ወይም በስንኝ ከሚይዟቸው የምጣኔ ስልትና የቀለማት መጠን አኳያ በተለያዩ ክፍሎች ይመደባሉ። ከዚህም በመነሳት ከግጥም ዓይነቶች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል። በምሳሌዎቹ ጎልተው የተጻፉት ፊደላት ቀለማት ናቸው።

ሀ. ቡሄ በሉ ግጥም፤ ቡሄ በሉ ግጥም በሀረግ አራት በስንኝ ስምንት ቀለሞችን አለው። ምጣኔው "ቡሄ ቡሄ" ከሚባለው የልጆች ጭፈራ ዜማ መጠሪያውን ያገኝ ይመስላል። ሃረጎች ፈጣኖች፣ ዜማው ቁርጥ ቁርጥ የሚል በጥድፊያ የሚከወን ስንኝ ነው።

ምሳሌ፡- ቡሄ በሉ (4) / ቡሄ በሉ (4) = 8

ልጆች ሁሉ (4) / እንድትበሉ (4) = 8

ለ. ሰንጎ መገን ግጥም፤ የሰንጎ መገን ምጣኔ በሀረግ አምስት በስንኝ አስር ቀለማት አሉት። ይህ የምጣኔ ስልት በፈጣንና እልክ፣ ኃይልና ግለት በተቀላቀለበት ሁኔታ ይከወናል። ብዙ ጊዜም ጀግንነት እና ሙያ ይነገርበታል።

ምሳሌ፡- ውረድ እንውረድ (5) / ተባባሉና (5) = 10

አስደበደቡት (5) / አፋፍ ቆሙና (5) = 10

ሐ. የወል ግጥም፤ ይህ የግጥም ዓይነት በአብዛኛው በሀረግ ስድስት፣ በስንኝ አስራ ሁለት ቀለማት አሉት።

ምሳሌ፡- እስከ ጊዜው ድረስ (6) / እስኪሞላ ልኩ (6) = 12

የጀግና ፈረስ ነው (6) / የሰው ሁሉ መልኩ (6) = 12

## ተግባር አምስት

1. ኀሰሳ ስጋ

   እልፍ ከሲታዎች ቀጥነው የሞገጉ፣

   ስጋችን የት ሄደ? ብለው ሲፈልጉ፣

   በየሸንተረሩ በየጥጋጥጉ፣

   አስሰው አስሰው በምድር በሰማይ፣

   አገኙት ቦርጭ ሆኖ አንድ ሰው ገላ ላይ።

   (በዕውቀቱ ስዩም፣1995)

   - ግጥሙ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ስለምን ጉዳይ ነው?
   - ከግጥም ባህርያት አኳያ ገምግማችሁ ግምገማችሁን በአንድ አንቀጽ ጽፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

2. በቡድን በመሆን ከላይ በማዳመጥ እና በማንበብ ክፍል የቀረቡትን ግጥሞች ስንኝ፣ ሀረግ፣ ቤት ለይታችሁ ጻፉ።

3. ከተለያዩ ምንጮች ግጥሞችን ካነበባችሁ በኋላ የግጥሞቹን አይነት ለይተችሁ ጻፉ።

## መልመጃ ሦስት

**ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በተሰጠው ግጥም መሰረት መልሱ።**

አልሰማኝም ጎራው ጆሮው ላይ ተኝቶ፣

አላየኝም ጎራው ዐይኑ ላይ ተኝቶ፣

እያልኩ ስተክዝ ስናገር በሮሮ፣

እሱስ ሰምቷል ለካ እሱስ አይቶ ኖሮ፣

ያለውን አንድ ሆድ ባንዲት አፉ አስሮ።

(ፈቃደ አዘዘ፣ 1985)

1. ግጥሙ ስንት ስንኞች አሉት? ስንኞቹን ለይታችሁ አመልክቱ።
2. ግጥሙ ስንት ሀረጋት አሉት? ሀረጋቱን ለይታችሁ አመልክቱ።
3. የግጥሙ ቤት ____ እና ____ናቸው።
4. ግጥሙ ቤት መምታቱን ወይም ማፍረሱን ካረጋገጣችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ጻፉ።
5. የግጥሙን አርኬ አመልክቱ።
6. የግጥሙ መልእክት ምን እንደሆነ በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

**ለ. በሚከተሉት ግጥሞች ላይ በመወያየት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ ምላሽ ስጡ።**

- ግጥሞቹ ከየትኛው የግጥም አይነት እንደሚመደቡ ጻፉ።
- ግጥሞቹ በስንኝ ያላቸውን የቀለም መጠን (ቁጥር) ለይታችሁ ጻፉ።

1. እዝያ ማዶ ጭስ ይጨሳል፣

   አጋፋሪ ይደግሳል።

2. አለስልሰህ ዝራ የስንዴውን ማሳ፣

   የተዘራችው ዘር ፈርሳና በስብሳ፣

   ታፈራለች ፍሬ ሞታ ስትነሳ።

3. አፈጣጠኑ የፈረስ ጭራ፣

   አፈጣጠኑ የሎስ አሞራ።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት የአዳዲስ ቃላትን ፍቺ እንድትሰጡና ቃላቱን እንድትገለገሉባቸው የሚያግዝ መልመጃ ስለቀረባላችሁ በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

## መልመጃ አራት

የሚከተሉትን ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቺያቸውን ጻፉ። ከዚያም በማዳመጥና በማንበብ ትምህርት ስር በቀረቡ ግጥሞች ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ፍቺ ስጡ፤ በመጨረሻም ከቃላቱ መርጣችሁ በመገልገል አጫጭር ግጥሞች በመጻፍ ተለማመዱ።

1. መስክ
2. ሎስ
3. አጋፋሪ
4. ጎራ
5. ጥርኝ
6. ስንዝር
7. ሮሮ
8. አፋፍ
9. ጥምቡሳስ
10. መኸር
11. ቀዘባ
12. ጭጋግ
13. ዱር
14. ግሳንግስ

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ስለቅጥያዎች ማስታወሻ እና ቅጥያዎችን ከዋና ቃል እንድትለዩ የሚረዳ መልመጃ ስለቀረበ በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

## ቅጥያዎች

በቃል ላይ ተለጥፈው ወይም ተቀጥለው የሚገኙ ጥገኛ ምዕላዶች ቅጥያዎች ተብለው ይጠራሉ። ለምሳሌ "ከቤታችሁ" በሚለው ቃል ላይ "ከ-" እና "-ኣችሁ" የሚሉት ጥገኛ ምዕላዶች "ቤት" በሚለው ቃል ላይ ተቀጥለው የሚገኙ ቅጥያዎች (ጥገኛ ምዕላዶች) ናቸው።

ቅጥያዎች ከሚቀጠሉበት ቦታ አኳያ የሚከተሉትን ስያሜዎች ይዘው ይገኛሉ። እነሱም፡-

ሀ. ቅድመ ግንድ ቅጥያ፡ ከሚቀጠልበት ቃል መነሻ (መጀመሪያ) ላይ ታክሎ የሚገኝ ቅጥያ ነው።

ምሳሌ፡

"ከታች" "ከ-" "ታች" በሚለው ቃል መጀመሪያ ላይ በመቀጠሉ ቅድመ ዐምድ ቅጥያ ተብሎ ይጠራል።

ለ. ውስጠ ግንድ ቅጥያ፡ በሚቀጠልበት ቃል መካከል (ውስጥ) ላይ የሚገኝ ቅጥያ ነው።

ምሳሌ፡

"ሰፋፊ" "-ፋ-" "ሰፊ" በሚለው ቃል መካከል ላይ በመቀጠሉ ውስጠ ዐምድ ቅጥያ ተብሎ ይጠራል።

ሐ. ድህረ ግንድ ቅጥያ፡ ከሚቀጠልበት ቃል መድረሻ (መጨረሻ) ላይ ተቀጥሎ የሚገኝ ቅጥያ ነው።

ምሳሌ፡

"ቤታቸው" "-አቸው" "ቤት" በሚለው ቃል መድረሻ ላይ በመቀጠሉ ድህረ ዐምድ ቅጥያ ትብሎ ይጠራል።

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ላይ "ታች"፣ "ሰፊ" እና "ቤት" የሚሉት በየተራ "ከ- "፣ "-ፋ-" እና "-አቸው" የሚሉትን ቅጥያዎች ያስከተሉ በመሆናቸው ምክንያት "ግንድ" ተብለው ይጠራሉ።

(ምንጭ፡- ጌታሁን አማረ (1989) የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ከሚለው ላይ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ።)

## መልመጃ አምስት

በምሳሌዎቹ መሰረት በሚከተሉት ቃላት ላይ ተቀጥለው የሚገኙትን ቅጥያዎች ለይታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ1፡ ጎመኑ

ጎመን-ኡ (ዋናው ቃል "ጎመን"፣ ቅጥያው ደግሞ "-ኡ" ሲሆን ቅጥያውም ድህረ ቅጥያ ነው።)

ምሳሌ2፡ በሀገራችን

በ-ሀገር-ኣችን (ዋናው ቃል "ሀገር"፣ ቅጥያዎች ደግሞ "በ-" እና "-ኣችን" ናቸው። "በ-" ቅድመቅጥያ፣ "-ኣችን" ድህረቅጥያ ናቸው።

1. ካረንጓዴው
2. የመንደሩ
3. ያባት
4. ድርቆሹ
5. እየሸሸ
6. የተቀደሰውን
7. አይበርድም

## የምእራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ግጥምን በሚመለከት የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል። በማዳመጥ ክፍል ውስጥ የግጥምን ምንነት፣ በግጥም ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ዐውዳዊ ፍች እና በግጥሙ ውስጥ ምስል ከሳች ቃላትንና ዘይቤያዊ አገላለጾች በቀረቡላችሁ የመልመጃ ጥያቄዎች በመታገዝ ተምራችኋል።

በክፍል ሁለት የቀረበላችሁን ግጥም በመጠቀም የግጥም አነባብ ስልትን በመጠቀም ልምምድ አድርጋችኋል፤ በግጥም እና በዝርው ትረካ መካከል ባለው ልዩነት ላይ በቡድን ተወያይታችኋል። በመረጣችሁት ርዕስ ላይም አሳማኝ የንግግር ዝግጅት በማድረግ የቅስቀሳ ንግግር ልምምድ በማቅረብ ተለማምዳችኋል።

በክፍል ሦስት የቃላትና የሀረጋት በግጥም ውስጥ ተደጋግመው የመቅረባቸው ምክንያት ምን እንደሆነ፤ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ዘይቤያዊ አገላለጾች፣ የተመረጡ ቃላት በግጥም ውስጥ ምን ፋይዳ እንዳላቸው በቡድን ተወያይታችኋል። በቀረቡላችሁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነትም የተለያዩ የመልመጃ ጥያቄዎችን ሠርታችኋል።

በክፍል አራት ግጥም የተጨባጭነት፣ የእምቅነትና የቁጥብነት፣ የምናባዊነት እና የሙዚቃዊነት ባህሪ እንዳለው ተምራችኋል። በግጥም ውስጥ የሚገኘውን ምጣኔ መሠረት በማድረግ የቡሄ በሉ ቤት፣ የወል ቤት፣ የሰንጎ መገን ቤት ግጥም ዓይነቶችንም ተምራችኋል። በግጥም ውስጥ የሚገኙትን የቀለማት መጠን በመለየት የግጥሞችን ዓይነትም መግለጽን ተለማምዳችኋል።

በክፍል አምስት የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች በመፈለግ ፍቻቸውን የሚያመለክቱ ዐረፍተ ነገሮችን በመሥራት ተለማምዳችኋል። በክፍል ስድስት ደግሞ በቃላት ላይ ተቀጥለው የሚገኙትን ቅጥያዎች በመለየት ልምምድ አድርጋችኋል።

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ተገቢ መልስ ስጡ።

1. ግጥም ምንድን ነው?
2. ከግጥም ባህርያት ውስጥ ሁለቱን በመጥቀስ አብራሩ።
3. በግጥም ውስት ምስል ከሳች ቃላትን፣ ዘይቤያዊ አገላለጾችን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ምን ፋይዳ እንዳላቸው አብራሩ።
4. የግጥም ሙያዊ ቃላትን አብራሩ።
5. የግጥም ዓይነቶችን ግለጹ።

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች እንደገና አንብቡ።

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥኩትን ግጥም መልዕክት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | የግጥምን ምንነት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 3 | በግጥም ውስጥ የተጠቀሱትን ዘይቤያዊ አገላለጾች መለየት ችያለሁ | | | |
| 4 | ምስል ከሳች ቃላትንና ሀረጋትን በመጠቀም ግጥም መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 5 | የግጥም ባህርያትን መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 6 | የግጥም ዓይነቶችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 7 | መዝገበ ቃልን በመጠቀም የቃላትን ፍች መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 8 | በቃላት ላይ የተቀጠሉትን ቅጥያዎች መለየት ችያለሁ | | | |

# ምእራፍ ሰባት

## ኮሮና (ኮቪድ -19)

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ስለኮሮና (ኮቪድ-19) የተጻፈ ጽሑፍ ካዳመጣችሁ በኋላ የጽሑፉን ዋና ሀሳብ ታብራራላችሁ።
- በነጻነት ወይም በራስ መተማመን መንፈስ ሃሳባችሁን ትገልጻላችሁ።
- መመሪያዎችን ትተገብራላችሁ።
- ግጥምንና ስእልን ወደዝርው በመለወጥ ትጽፋላችሁ።
- በቃላት ውስጥ ያሉ ሆሂያትን በማጥበቅና በማላላት በማንበብ የፍቺ ልዩነታቸውን ትገልጻላችሁ፡
- የፊደል ገበታ በመገልገል ቃላትን በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ትሰድራላችሁ።
- ቅድመቅጥያና ድህረቅጥያን ከዋና ቃሉ ወይም ከግንዱ በመለየት አገልግሎቱን ትገልጻላችሁ።

# ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ስለኮሮና የቀረበ ጽሁፍ ሲነበብላችሁ በጥሞና አዳምጣችሁ መልመጃዎችንና ተግባራትን ስሩ።

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ኮሮና (ኮቪድ-19) ምንድን ነው?
2. ኮሮና (ኮቪድ-19) መተላለፊያ መንገዶች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
3. ኮሮና (ኮቪድ-19) በሚል ርእስ የሚቀርበው ምንባብ ይዘት ምን ይመስላችኋል?
4. በሚከተሉት ቃላት ፍቺ በቡድን በመወያየት ግምታችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ሀ. ቫይረስ ለ. እክል ሐ. ግዴለሽነት

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የኮሮና ቫይረስ አይነቶች የተባሉት እነማን ናቸው?
2. በጽሁፉ የተገለጹት የኮቪድ-19 በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ሀ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ጽሁፍ መሠረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በቃል ግለጹ።

1. የኮሮና ቫይረስ ሰውነት ውስጥ ከገባ በኋላ የበሽታው ምልክት እስከሚታይ ለምን ያህል ጊዜ ሊቆይ ይችላል?
2. ኮቪድ-19 የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ምን ምን ናቸው?

3. ሁሉም የጉንፋን ምልክቶች በኮቪድ ምክንያት የሚመጡ ናቸው? ለምን?

4. የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን መከላከል የማን ኃላፊነት ነው?

### ለ. በጥንድ በመሆን ያዳመጣችሁት ጽሁፍ ዋና ሃሳቦች

- የኮሮና ምንንት፣
- የኮሮና በሽታ ምልክቶች፣
- ከኮሮና ጋር ተመሳሳይ ጉንፋኖች፣
- የኮሮና በሽታ ስርጭት መከላከል፣
- በኮሮና መከላከል የሚታዩ እክሎች

ላይ በመወያየት የደረሰባችሁትን ማጠቃለያ በቃል ግለጹ።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ኮሮናን በተመለከተ የቀረበ ተግባርን መሰረት በማድረግ የቃል ዘገባ አቅርቡ፤ ክርክርም አድርጉ።

### ተግባር አንድ

1. እስካሁን በተደረገው ጥናት መሠረት በኮቪድ-19 የጸና ህመም የመያዝ እድላቸው ሰፊ እንዲሆን ሊያደርጉ የሚችሉ የህመም አይነቶች በሚመለከት መረጃዎችን በመሰብሰብ የቃል ዘገባ በማዘጋጀት አቅርቡ።
2. በምእራፍ ሁለት ክርክር ሁለት ተቃራኒ አመለካከት ባላቸው ቡድኖች መካከል የሚካሄድ ሙግት መሆኑን፣ በክርክር ቅድመ ዝግጅትና ክርክር በሚቀርብበት ጊዜ ምን ምን ተግባራት መከናወን እንዳለባቸው ተምራችኋል። በተማራችሁት መሠረት “ኮሮና ቫይረስን በባህላዊ መድኃኒት መከላከል ወይም ማከም ይቻላል/አይቻልም” በሚለው ርዕስ ላይ በሁለት ቡድኖች በመከፈል፣ የክርክር አቀራረብን ሂደት በመከተል ክርክር አድርጉ።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት "ኮሮና (ኮቪድ-19)" በሚል ርእስ የቀረበ ጽሁፍ መሰረት በማድረግ የቅድመ፣ የጊዜና የድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ስሩ።

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

1. ወረርሽኝ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. ኮሮና (ኮቪድ-19) በሰዎች የአኗኗር ሥርዓት ላይ ምን ምን ለውጦችን የሚያስከትል ይመስላችኋል?
3. ከዚህ በታች "ኮሮና (ኮቪድ-19)" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ይዘት ምን ይመስላችኋል?

## ኮሮና (ኮቪድ-19)

ሀገራችንም ሆነች ዓለማችን በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱ ወረርሽኞች አልፈዋል። አያንዳንዱ ወረርሽኝና ጥፋት ዛሬ ላይ ዓለም ለደረሰበት ስልጣኔ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ይህ አዎንታዊ ጎናቸው ነው። በቅርቡ የተከሰቱት እንደ ሳርስና ኢቦላም ለሰው ልጆች የማስጠንቀቂያ ደወል ሆነው አልፈዋል። በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጥረው የነበሩ እንደፈንጣጣ፣ ኩፍኝና ፖሊዮ ያሉት በክትባት ኃይል እንዲጠፉ ተደርገዋል። ይህ ክትባት እስኪገኝ ድረስ ግን ረጅም ጊዜ ፈጅቷል፤ ብዙ ጥፋቶችንም አስከትለዋል። ቫይረሶች በባህሪያቸው አስቸጋሪ ናቸው፤ እንደባክቴሪያ በቀላሉ በፀረ-ባክቴሪያ መድኃኒቶች የምናክማቸው አይደሉም። ለአብነት እንኳ ባለፉት 40 ዓመታት ውስጥ 40 ሚሊዮን ሕዝብ የጨረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ማጤኑ በቂ ነው።

ከቀደሙ ወረርሽኞች ዓለም ተምሮ ካስቀመጣቸው መፍትሔዎች በወረርሽኝ ወቅት ምልክት ያለባቸው ወይም ታማሚ ሰዎችን ነጥሎ

ማስቀመጥና ማከም (ኳራንቲን) አንዱ ነው። ይህ መፍትሔ ድንበር ዘለል የሆኑ ወረርሽኞችን ለመገደብ ብዙ ያግዛል። ኳራንቲን ለህዝብ ጤና ጠቃሚ እርምጃ ሆኖ የተጀመረው በአውሮፓ አቆጣጠር በ1580 በእስያ ተከስቶ በነበረው የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ ወቅት ነበር። ሌላው የሚተገበረው የመጀመሪያውን ታማሚ ፈልጎ ማግኘትና፣ ይህ ሰው ያገኛቸውን ሰዎች፣ እንዲሁም ለህመሙ ተጋላጭ የሆነባቸውን ተዋህስያን ምንጭ የመለየት ሥራ (ትሬሲንግ) ነው። ይህም የተጀመረው በህንድ፣ በእንግሊዝና በራሺያ ተከስተው ሰፊ አካባቢዎችን ከሸፈኑ የኮሌራ ወረርሽኞች በኋላ እንደነበር በአሜሪካው ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ታሪክ አጥኚ የሆኑት ግራሃም ሞኒ ይናገራሉ።

በዓለም የህክምና ታሪክ ከፋው ወረርሽኝ የሚባለው የ1918 የስፓኒሽ ፍሉ ደግሞ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ መገደብን እንደ አንድ መፍትሔ መውሰድን ዓለም የተማረበት መሆኑን ባለሞያዎች ያስረዳሉ። ብዙዎቹ የተከሰቱ የጉንፋን ወረርሽኞች ያስተማሩት ሁነኛ ትምህርት ደግሞ አገራት በደንብ የተደራጁ የበሽታ ቁጥጥር ማዕከላትን ማቋቋም እጅግ አስፈላጊ መሆኑንና ዓለም አቀፍ ትብብር ወሳኝ እንደሆነ ነበር። ይህን ተከትሎ ነበር አሜሪካ ሲዲሲ የተባለውን የበሽታ ቁጥጥር ማዕከል ያቋቋመችው። የዓለም ጤና ድርጅትም የተቋቋመው በዚህ እሳቤ ነበር። ይሁንና ዓለም ወረርሽኞችን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠርና እንዳይከሰቱም ጭምር ለማድረግ የምትችልበት አቅም ላይ አልደረሰችም። የክትባቶችና የጸረ-ተዋህስያን መድኃኒቶች መፈጠር፣ እንዲሁም የተሻለ አቅም ያላቸው የጤና ተቋማትን መገንባት መቻሉ ከወረርሽኞች መመከት የተወሰዱ ትምህርቶች ተደርገው ይወሰዳሉ።

ይሁንና ወረርሽኞችን የመመከት አቅም፣ ከቀደሙ ጉዳቶች ተምሮ ጠንካራ ግንዛቤ ያለው ማኅበረሰብና የጤና ስርዓት መገንባት ለብዙ ደሃ ሀገሮች ፈታኝ ነው። ኢትዮጵያውያንንም የፈተነው ከ16ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ የተከሰቱ የታይፈስ (ንዳድ)፣ ኮሌራ፣ ፈንጣጣ እንፍሉዌንዛ (ህዳር በሽታ)ይጠቀሳሉ። እነዚህ ወረርሽኞች ከጦርነትና ድርቅ ጋር

ተደምረው የቀደሙ ዘመናት መሪዎች የሰልጣን ዘመንን በብዙ ፈትነዋል። እነዚህን ወረርሽኞች በቅጡ ተረድቶ ምላሽ ለመስጠት፣ ዳግም እንዳይከሰቱም ብልሃት ለማበጀት የቀደሙት ነገሥታትና መሪዎች የየአቅማቸውን ቢጥሩም፣ በዘመናቱ የነበረው የሳይንስ ዕውቀት አነስተኛ መሆን፣ የባለሞያ እጥረትና የዘመናዊ መድኃኒት እጦት ኢትዮጵያን ከጠርነት ባላነሰ ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ኳራንቲ፣ ትሬሲንግ የሚሉትን ቃላት የያዙትን ፍቺ ግለጹ።
2. እስካሁን ባነበባችሁት ውስጥ የተጠቀሱትን የተላላፊ በሽታ ዓይነቶች ዘርዝሩ።

ኮሮና (ኮቪድ-19) በመባል የሚጠራው አዲሱ ወረርሽኝም ልክ እንደ ፍሉ-18 ከሰውና ከእንስሳት ዝርያ የተቀዳ በመሆኑ ከአሁን ቀደም በሰዎች ዘንድ ሲሰራጭ የነበረው የኮሮና ቫይረስ ከእንስሳት ኮሮና ጋር በመዳቀል የተገኘ አዲስ ዓይነት ዝርያ ነው። አዲስ ዲቃላ ቫይረስ በመሆኑም “ኖቭል” (አዲስ) የሚል ቅጥያ ተሰጥቶታል። ቻይና ውስጥ ታህሳስ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር 30/2019 ለመጀመሪያ ጊዜ ዉሃን ግዛት ውስጥ የታየው ቫይረስ ቀድሞ እንስሶችን ብቻ ያጠቃ የነበረና ሰውን ወደማጥቃት የቀየረ ስለነበር ነው የውሃን ቫይረስ የ2019 ኖቭል ኮሮና ቫይረስ የተባለው።

ስለቫይረሱ አጀማመር የተሰጠው መላምትም የቫይረሱ ተሸካሚዎች ከሆኑት እንስሳት (የሌሊት ወፍ፣ ድመት፣ ከብት፣ ግመል ወይም እባብ) አፈጣጠሩን በመቀየር ከእንስሳቱ ጋር ቀጥታ ንክኪ ወደነበራቸው ሰዎች ተዛመተ የሚለው ነው። ቫይረሱ አንዴ የሰው ልጅ ህዋሳት ውስጥ ከገባ ራሱን በማባዛትና የሰውነት መቆጣት (ኢንፌክሽን) በማምጣት የበሽታውን ምልክቶች ያሳያል። እስካሁን ድረስ የወረርሽኙ ምንጭ በትክክል አልታወቀም። የቫይረሱ አመጣጥ ከዉሃን ግዛት የባህር ምግቦችና የእንስሳት ገበያ ጋር የተገናኘ ነው የሚል እምነት አለ።

ይህ የዉሃን ግዛት ገበያ ወዲያውኑ እንዲዘጋ አድርጎታል።

ኮሮና ቫይረስ በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ውስጥ ባሉ ሀገሮች ውስጥ በመዛመት ላይ ያለ ወረርሽኝ ሲሆን፣ ወረርሽኙን አስፈሪ ያደረገው እንደ አብዛኛዎቹ በቫይረስ የተነሳ የሚመጡ ህመሞች ሁሉ ፈዋሽ መደረኃኒት የሌለው መሆኑ ነው። በሽታው በአጭር ጊዜ እንዲሰራጭ ያደረገው ደግሞ በቀላሉ በትንፋሽና በንክኪ መተላለፍ መቻሉ ሲሆን፣ ይህም አደገኛነቱ የላቀ እንዲሆን አድርጎታል። ከሰዎች ጋር በቅርበት በማውራት እና በእጅ በመጨባበጥ፣ እንዲሁም ሰዎች የነኩትን ነገር በመንካት በቀላሉ ሊተላለፍ ይችላል።

ቫይረሱ በዋናነት ሳንባን፣ ልብንና ኩላሊትን ያጠቃል። የሳንባ አየር አስተላላፊ ህዋሳትን በማሳበጥና ሳንባ ሙሉ በሙሉ ሥራውን እንዳይሠራ በማድረግ የመተንፈስ ስርዓትን የሚያስቆም ሲሆን፣ ኩላሊትንም ደምን የማጣራት ተግባሩን እንዳይሠራ በመከላከል ያዳክማል። በእነዚህ ባህርያቱ የተነሳ በሽታው ገዳይ ሊሆን ይችላል።

ኖቭል ኮሮና ቫይረስ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎችን እንደሚያጠቃ ተረጋግጧል፤ ይሁን እንጂ እንደማንኛውም የቫይረስ በሽታዎች ሁሉ የተወሰኑ ሰዎች በሽታው ይጸናባቸዋል፤ ህፃናት፣ አረጋውያን፣ በሽታ የመከላከል አቅማቸው የተዳከመ ሰዎች፣ የስኳር ህመም፣ የልብ ህመም፣ የኩላሊት መድከም፣ የጉበት ህመም፣ አስም፣ የሳንባ ህመም እና ሌሎች የመተንፈሻ አካል ችግሮች ያለባቸው ሰዎች ቫይረሱ በቀላሉ ህመም ሊፈጥርባቸው ይችላል። ከታመሙ በሽታው በጣም ሊጸናባቸው ይችላል። ራሳችንንና በዙሪያችን ያሉ ሰዎች ከቫይረሱ ለመከላከልም ትክክለኛዎችን የመከላከያ እርምጃዎች መውሰድ፣ ዙሪያችንንም መከታተል አለብን።

የኮቪድ-19 ሁነኛ የመከላከያ መፍትሄዎቹም አዘውትሮ እጅን በውሃና በሳሙና መታጠብ፣ ከተፋፈጉ ቦታዎች አለመገኘትና እና ከሚያስሉና ከሚያነጥሱ ሰዎች በቂ ርቀት ማበጀት፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ንፁህ

ሆኖ መገኘት ነው። ከዚህ ውጪ ይፋዊ መግለጫዎችን ከጤና ሚኒስቴርና ተመሳሳይ ተቋማት እንዲሁም ተአማኒ የመረጃ ምንጮች ብቻ በመውሰድ ራስን ማስታጠቅና መምራት ወረርሽኙን ለማሸነፍ፣ በጤናም ለመሰንበት ያግዛል።

(ምንጭ፡- አቡሽ አያሌውና ሌሎች (ዓ.ም. ያልተጠቀሰ) የኮሮናው መብረቅ ከሚለው ላይ ለማስተማሪያነት ተሸስሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

**ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባብ መሠረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በጽሑፍ አስፍሩ።**

1. በምንባቡ ውስጥ የተገለጹትን የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቁ በሽታዎችን ዘርዝሩ።
2. የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቁ በሽታዎች ከኮሮና (ኮቪድ-19) ጋር የሚያመሳስሏቸውን ባህርያት ግለጹ።
3. ዓለም ከቀደሙት ወረርሽኞች በመነሳት ወረርሽኙን ለመገደብ ያስቀመጣቸው መፍትሔዎች ምን ምን ናቸው?
4. ኮሮና (ኮቪድ-19) የሚያጠቃው በየትኛው የዕድሜ ክልል ያለን ሰው ነው?
5. የኮቪድ-19 የመከላከያ መፍትሔዎች ምን ምን ናቸው?
6. በምንባቡ ውስጥ "እያንዳንዱ ወረርሽኝና ጥፋት ዛሬ ላይ ዓለም ለደረሰበት ስልጣኔ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ይህ አዎንታዊ ጎናቸው ነው።" በሚል ተገልጿል። የዚህን ሀሳብ እውነታ ከምንባቡ ውስጥ ማስረጃ በመንቀስ ግለጹ።

### ለ. በ“ሀ” ስር የቀረቡትን የአንቀጾች ቁጥሮች በ“ለ” ስር በምንባቡ ከገለጹት ዋና ሀሳቦቻቸው ጋር አዛምዱ።

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| 1. አንቀጽ አንድ | ሀ. ኮሮና (ኮቪድ-19) ማንን እንደሚያጠቃ የተገለጸበት አንቀጽ |
| 2. አንቀጽ ሁለት | ለ. የኮሮና (ኮቪድ-19) በሽታ መከላከያ መንገዶች |
| 3. አንቀጽ ሦስት | ሐ. ኮሮና (ኮቪድ-19) ቫይረስ የሚያጠቃው የሰውነት ክፍሎች |
| 4. አንቀጽ አራት | መ. የኮሮና (ኮቪድ-19) ቫይረስ መዛመቻ መንገዶች |
| 5. አንቀጽ አምስት | ሠ. የኮሮና (ኮቪድ-19) ቫይረስ አነሳስ መላምት |
| 6. አንቀጽ ስድስት | ረ. የኮሮና (ኮቪድ-19) ቫይረስ ምንነት |
| 7. አንቀጽ ሰባት | ሰ. የኮሮና (ኮቪድ-19) ቫይረስን የመመከት ፈተናዎች |
| 8. አንቀጽ ስምንት | ሸ. እንቅስቃሴን ሙሉ በሙሉ መገደብ |
| 9. አንቀጽ ዘጠኝ | ቀ. ኳራንቲንና ትሬሲንግ |
| 10. አንቀጽ አስር | በ. ወረርሺኞች የሚያመጧቸው መልካም አጋጣሚዎች |

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ስለኮሮና (ኮቪድ-19) አንቀጾች እንድትጽፉ የሚያግዝ ተግባር ስለቀረበላችሁ ተግባሩን በትኩረት ስሩ።

ተግባር ሦስት

ሀ. በምእራፍ ስድስት ስለግጥም ስትማሩ አንጓ (አርኬ) የግጥም አንድ ሀሳብ ማቅረቢያ ክፍል እንደሆነ ግንዛቤ ወስዳችኋል። እንደዚሁም የግጥምና የዝርው ጽሁፍ ልዩነቶች ምን እንደሆኑ ተረድታችኋል። በመሆኑም ቀጥሎ የቀረበውን ባለአንድ አንጓ ግጥም ወደዝርው ጽሁፍ በአንድ አንቀጽ አደራጅታችሁ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

| |
|---|
| ከቻይና ዉሃን - ድንገት አፈትልኮ፣<br>የአውሮፓ አሜሪካን - ጉልበት አብረክርኮ፣<br>በባቡር ጢያራ - ሃገራትን ዞሮ፣<br>ምስቅልቅ አውጥቶ - የሰውን ልጅ ኑሮ፤<br>ምቾት ስለሰጠው - ህብረአደር ጎዳና፣<br>እቤታችን ደርሷል - ተውሳኩ ኮሮና። |

ለ. የሚከተሉትን ምስሎች መሠረት በማድረግ "የኮቪድ-19 ምልክቶች" በሚል ርዕስ አንድ አንቀጽ ጽፉችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።



# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት የቃላት ሆሄያት ላልተውና ጠብቀው ሲነበቡ በቃሉ ላይ የሚያስከትሉትን የፍቺ መለያየት እንዲሁም ቃላትን በፊደል ተራ ቅደም ተከተል መሰደርን የሚያለማምዱ ችሁ ጥያቄዎች ስለቀረቡ በትኩረት ስሯቸው።

## መልመጃ ሦስት

ሀ. ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የፍች ልዩነት ያስከትላሉ። ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት የንበት ልዩነት ለመረዳት በማጥበቅና በማላላት ካነበባችሁ በኋላ በምሳሌው መሰረት በሁለቱም የንበት ሁኔታ የሚኖራቸውን ፍቺ ጻፉ።

ምሳሌ፡ በሽታ

“የኮሮና በሽታ በትንፋሽ ይተላለፋል።” በሚለው አረፍተነገር ውስጥ “በሽታ” ላልቶ ይነበባል፤ ፍቺውም “ህመም” የሚል ፍቺ ይሰጣል፤ “የአስም ህመሜ በሽታ ይቀሰቀስብኛል።” በሚለው አረፍተነገር ውስጥ ጠብቆ ይነበባል ፍቺውም በጠረን የሚል ፍቺ ይሰጣል።

| | | |
|---|---|---|
| 1. ጎልቶ | 4. አያት | 7. አይበላም |
| 2. መሳል | 5. ፍራሽ | 8. አማት |
| 3. ያለው | 6. አዛባ | 9. አዘመረ |

ለ. የሚከተሉትን ቃላት በሀ፣ለ፣ሐ፣መ… ፊደል ተራ ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ጻፉ። (የፊደል ገበታ በአጋዥነት መገልገል ትችላላችሁ)

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1.ብርቱ | 4. ፍቅር | 7. ጉሬዛ | 10. ደረጀ |
| 2.ኃይለኛ | 5. ዑደት | 8. ወይፈን | |
| 3.ክረምት | 6. ወጣትነት | 9. ቢጋር | |

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ቅጥያዎችን በተመለከተ መልመጃ ስለቀረበላችሁ በትእዛዙ መሰረት በትኩረት ስሩ።

## መልመጃ አራት

ሀ. በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ በሚገኙት ባዶ ቦታዎች ላይ በሳጥን ውስጥ ከቀረቡት ተገቢ የሆኑ ቅጥያዎችን በመምረጥ አስፍሩ።

| |
|---|
| -ኦች፣ -ኡ፣ -ኤ፣ -ን፣ በ-፣ -ኣችን፣ -ዎች፣ -ን፣ ለ- |

1. ሀገር_ም ሆነች ዓለማችን _ተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱ ወረርሽኝ_ አልፈዋል።
2. አብዛኛ_ _በቫይረስ የተነሳ የሚመጥ_ ህመሞች ሁሉ ፈዋሽ መድኃኒት የላቸውም።
3. ከጤና ሚኒስቴርና ከመሰል ድርጅቶች የሚወጡ ይፋ_ መግለጫ__መከታተል ያስፈልጋል።
4. ኮሮና (ኮቪድ-19) ታህሳስ 30/2019 እ.ኤ.አ _መጀመሪያ ጊዜ ዉሀን ግዛት ውስጥ ታየ።
5. ቤት__ ሸጥኩት።

ለ. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ግንድ ቃል ወይም ዋና ቃል፣ ቅድመግንድ ቅጥያ እና ድህረግንድ ቅጥያ በምሳሌው መሰረት ከለያችሁ በኋላ አገልግሎታቸውን ጻፉ።

ምሳሌ፡ ዘመዶቻቸውን (ዘመድ - ኦች - ኣቸው - ን)

ዘመድ = ዋና ቃል
-ኦች = ብዛትን ያመለክታል
-ኣቸው = የነሱ መሆኑን ወይም ባለቤትነትን ያመለክታል
-ን = ተሳቢ አመልካች

1. ልጆቻችን
2. መኪናዬ
3. ልብሱ
4. ሙሽራው
5. መጽሃፋችን

# የምእራፉ ማጠቃለያ

በምእራፍ ሰባት ኮሮና (ኮቪድ-19) በሚል ርዕስ የቀረበ ነው። በምእራፉ የማዳመጥ ክፍል ውስጥ በቀረበላችሁ ጽሁፍ የቫይረሱን ምንነት፣ ምልክቶች እና በመሳሰሉት ይዘቶች ዙሪያ ተወያይታችኋል፤ የጽሁፉንም ዋና ዓላማ ገልጻችኋል፤ በተገቢ ሆሄያት የተዋቀሩ ቃላትንም በመጠቀም ለጽሁፉ የማጠቃለያ ሀሳብ ሰጥታችኋል።

በክፍል ሁለት የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም በኮቪድ-19 ፅኑ ህመም የመያዝ ዕድላቸው ሰፊ እንዲሆን ሊያደርጉ የሚችሉትን የህመም ዓይነቶች በሚመለከት መረጃዎችን ሰብስባችኋል፤ ያገኛችሁትንም መረጃ መነሻ በማድረግ ዘገባ አዘጋጅቶ ማቅረብን ተለማምዳችኋል። በቡድንም በመሆንም በጥያቄው በቀረበው ርዕስ ላይ በቡድን ሆናችሁ በመከራከር ክርክር የማቅረብ ሂደትን ተምራችኋል።

በክፍል ሦስት የቀረበውን ጽሁፍ በማንበብ ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥታችኋል። የቃላትን ዐውዳዊ ፍቺ ገልጻችኋል፤ የምንባቡንም ዋና ዋና ነጥቦች ለይቶ ማውጣትን ተምራችኋል።

በክፍል አራት በተለያዩ ርዕሰጉዳዮች ላይ አንቀጽ መጻፍን ተምራችኋል። የቀረቡትን ምስሎች መሠረት በማድረግም "የኮቪድ-19 ምልክቶች" የሚል ርዕስን በመጠቀም አንቀጽ ጽፋችኋል።

በክፍል አምስት የቀረቡትን ቃላት በማጥበቅና በማላላት በትክክል መጥራትን፣ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የፍቺ ልዩነት እንደሚያስከትሉ፣ ቃላትን በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ማስቀመጥን ተምራችኋል።

በክፍል ስድስት ደግሞ ቅጥያዎች በቃል ላይ ተጨማሪ ሆነው

የሚገቡ መሆናቸውን፣ ከሚቀጠሉበት ቦታም አኳያ ቅድመ፣ ድህረ እና መካከለኛ ቅጥያ ተብለው ሊጠሩ እንደሚችሉ፣ በቃላት ላይ የተጓደሉ ቅጥያዎችን በመቀጠል ሀሳቡን ማሟላትን፣ ከቃላት ላይ ቅጥያዎችን መለየትን ተምራችኋል።

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ቅጥያ ማለት ምን ማለት ነው?
2. ጠብቀውና ላልተው በመነበብ የተለያዩ ፍቾችን የሚሰጡ ሦስት ቃላትን ጻፉ።
3. በሚከተሉት ቃላት ላይ የተቀጠሉትን ቅጥያዎች ለይታችሁ አመልክቱ።

   ሀ. ሰባበረው　　ለ. ርቀታቸውን　　ሐ. ነገረኛነቱን

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች እንደገና አንብቡ።

| | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የዳመጥኩትን ምንባብ ዋና ዓላማ መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም መረጃዎችን መሰብሰብ ችያለሁ | | | |
| 3 | ከተለያዩ ምንጮች ያገኘኋቸውን መረጃዎች በቃል ዘገባ መልክ ማቅረብ ችያለሁ | | | |
| 4 | ግጥምንና ስእልን ወደዝርው/አንቀጽ መለወጥ ችያለሁ | | | |
| 5 | ቃላትን በማጥበቅና በማላላት በማንበብ በትክክል መጥራት ችያለሁ | | | |
| 6 | የፊደል ገበታን በመጠቀም ቃላትን በቅደም ተከተል መደርደር ችያለሁ | | | |
| 7 | በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ቅድመ ግንድ እና ድህረ ግንድ ቅጥያዎችን በማስገባት ዓረፍተ ነገሮቹን ማሟላት ችያለሁ | | | |
| 8 | በቃላት ላይ ተቀጥለው የሚገኙትን ቅድመ ዐምድ እና ድህረ ዐምድ ቅጥያዎች ከዋና ቃል ላይ መለየት ችያለሁ | | | |

# ምእራፍ ስምንት
# ተውኔት

## የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- ተውኔት በውስጡ የሚያጠቃልላቸውን ነገሮች በመለየት ትገልጻላችሁ።
- የተውኔት አይነቶችን ታብራራላችሁ።
- የተወኔት ጭብጦችን ትገልጻላችሁ።
- ጅምር ቃለተውኔቶችን ታጠናቅቃላችሁ፤ ትተውናላችሁ።
- ለቃላት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ።
- የምእላድና የቃል አንድነትና ልዩነትን ታብራራላችሁ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት ለማዳመጥ ግብአት "የተውኔት ምንነትና አላባውያን" በሚል ርእስ ጽሁፍ ቀርቦላችሁኋል። ይህን ጽሁፍ መሰረት አድርጋችሁ የቅድመማዳመጥ፣ የጊዜ ማዳመጥና የድህረማዳመጥ ጥያቄዎችን ስሩ።

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

1. ተውኔት ምንድን ነው? በቡድን በመሆን ተወያዩና መልሳችሁን በቡድን ተወካያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።
2. ከዚህ በፊት በሬዲዮ ካዳመጣችሁት፣ በቴሌቪዥን ወይም በመድረክ ከተከታተላችሁት ተውኔት የትኛውን ታስታውሳላችሁ? የምታስታውሱትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው።
3. ተዋንያን ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. እስካሁን ካዳመጣችሁት የጽሁፍ ክፍል ምን ምን ጉዳዮች ተነስተዋል?
2. ተውኔት በመድረክ ላይ እስኪቀርብ ድረስ ተሳታፊ ከሆኑት ባለሙያዎች ቢያነስ ሁለቱን ግለጹ።
3. አንድ የተውኔት ጽሁፍ ለመድረክ እንቅስቃሴ እንዲበቃ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲደረግ ሀላፊነቱን የሚወስደው የትኛው ባለሙያ ነው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።

1. ተውኔት ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች መድረክ ላይ መቅረቡ ያመሳስለዋል።
2. በተውኔት ገጸባህርያት ተዋንያንን ወክለው መድረክ ላይ ጥበቡን ይከውናሉ።

3. በተውኔት ውስጥ የሚታይ የፍላጎት አለመጣጣም ወይም ቅራኔ ግጭት ይባላል።

4. አንድ ተውኔት ከአንድ በላይ ንዑስ ጭብጥ ሊኖረው አይችልም።

5. የአንድ ተውኔት ትርጉም ከተውኔት አላባዎች ይመዘዛል።

ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

1. የምክንያትና የውጤት ትስስር ምን ይባላል?

   ሀ. ሴራ ለ. መቼት ሐ. ቃለተውኔት መ. ጭብጥ

2. አንድ ተውኔት የሚከናወንበትን ቦታና ጊዜ የሚያመለክተው የተውኔት አላባ________ይባላል።

   ሀ. ገጸባህርይ ለ. ትልም ሐ. ቃለተውኔት መ. መቼት

3. በተውኔት ውስጥ ገጸባህርያት እርስ በእርሳቸው የሚያደርጉት የምልልስ ንግግር ምን ይባላል?

   ሀ. ቃለምልልስ ለ. ቃለተውኔት ሐ. መቼት መ. ሴራ

4. የአንድ ተውኔት ማዕከላዊ ሀሳብ ምን ተብሎ ይጠራል?

   ሀ. ቃለተውኔትለ. ግጭት ሐ. ሴራ መ. ጭብጥ

5. ተዋንያን የሚወክሉትን ገጸባህርያት ሆነው እንዲገኙ የሚያስችሉ ባለሙያዎች ምን በመባል ይጠራሉ?

   ሀ. የቅብ ወይም የስእል ባለሙያ

   ለ. የድምጽና የሙዚቃ ባለሙያ

   ሐ. የሜካፕና ያልባሳት ባለሙያ

   መ. ጸሐፊ ተውኔትና መራሂ ተውኔት

# ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ቅንጫቢ ተውኔት የያዘ ተግባር ቀርቦላችኋል። ተግባሩን በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

## ተግባር አንድ

ቀጥሎ የቀረበውን ቅንጫቢ ተውኔት መሰረት በማድረግ ከስሩ የቀረቡትን ትእዛዞች አከናውኑ።

ጥበቃ፡ ጌታዬ አንድ አዛውንት በጧት የመጡ እደጅ ተጎልተዋል።
እርሶን ካላየሁ ይላሉ።

ተጫኔ፡ ማነኝ ይላሉ?

ጥበቃ፡ ስማቸውን አልነገሩኝም። ስሜን ያውቁታል ይላሉ።

ተጫኔ፡ (ይጮሀል) ወይ መከራ! የስንቱን ሰው ስም ላውቅ ነው
እንግዲህ? መልኩ ምን ይመስላል?

ጥበቃ፡ ረዘም ቀጠን ያሉ ናቸው፤ ሽበቶ።

ተጫኔ፡ እድሜያቸውስ?

ጥበቃ፡ ጠና ያሉ ናቸው። ከሰባ ያንሳሉ? ከሩቅ አገር መጣሁ ይላሉ።

ተጫኔ፡ ጉዳዩ ምንድን ነው?

ጥበቃ፡ ጉዳይ የለኝም አሉ። የርስዎን አይንዎን ለማየት ብቻ
ነው አሉ። እግራቸው አቧራ ለብሷል፤ ተሰነጣጥቋል።

ተጫኔ፡ ወዲያ አባርልኝ! ጊዜ የለኝም። የለም በል!

ጥበቃ፡ ብዬአቸዋለሁ፤ አሁን በመኪና ሲገባ አይቼዋለሁ ብለው ድርቅ
አሉብኝ። ደግሞ የቸገረኝ ነገር አለ።

ተጫኔ፤ ምን?

ጥበቃ፡ ከፈቀዱልኝ ልንገርዎ አዛውንቱ የሚሉትን።

ተጫኔ፡ ወይ ጣጣ! ምንድን ነው ነገሩ? ተንፍሰው ይውጣልህ።

ጥበቃ፡ ኸረ ከበድ ያለ ነገር ነው የሚናገሩት።

ተጫኔ፡ ምን ይላሉ?

ጥበቃ፡ አባ...ት አባትዎ ነኝ ይላሉ።

ተጫኔ፡ (ብው ይላል በቁጣ) ቀጣፊ ነው! አባት የለኝም! አባቴ ገና ድሮ ሞቷል ጦርሜዳ፤ ለሀገሩ ሲዋጋ።

ጥበቃ፡ (ሳይደነግጥ ይሽቆጠቆጣል) እኔም ነግሬአቸዋለሁ። ሽማግሌው አይሰሙም፤ "ወንድሜ! አባቱ እኔ ነኝ፣ አለሁ፤ ይኸው እዚህ በህይወት እገኛለሁ።" ይላሉ።

መንግስቱ ለማ (1975፣147-9)

1. የቡድኑ አባላት ቃለ ምልልሱን አጥኑ።
2. ፈቃደኛ ሁለት ተማሪዎች ክፍል ውስጥ የገጸባህርያቱን ንግግር እየተቀባበላችሁ አንብቡ፤ ከቻላችሁም በቃል (ሳታነቡ) ተውኑ፤ ሌሎች ተማሪዎች ትወናውን ተከታትላችሁ የትወናቸውን ጠንካራና ደካማ ጎን ንገሯቸው።
3. የተውኔቱ መልእክት ላይ ተወያዩ።
4. ተውኔቱ የሚጠናቀቅበት ሃሳብ ላይ ተነጋገሩ።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት "ፀሐፌ ተውኔት እና ባለቅኔው ሎሬት" በሚል ርእስ የቀረበ ጽሁፍ መሰረት በማድረግ የቅድመ፣ የጊዜና የድህረ ማንበብ ጥያቄዎችን ስሩ።

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች



1. ከላይ የምትመለከቱት ፎቶ የማን እንደሆነ ገምታችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሩ።
2. ከምንባቡ ርእስ በመነሳት በጽሁፉ ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ እንደሚችሉ ገምታችሁ ለጓደኞቻችሁ ንገሩ።

## ፀሐፌ ተውኔት እና ባለቅኔው ሎሬት

ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ሮባ የተወለደው ነሐሴ 17 ቀን 1928 ዓ.ም በደንዲ ወረዳ ከአምቦ ከተማ በ30 ኪሎ ሜትር ርቃ በስተደቡብ በምትገኘው ቦዳ በምትባል መንደር ነው። በወቅቱ አባቱ አቶ ገብረመድህን ሮባ ማይጨው ጦርነት ዘምተው ነበር። በዚሁ ጦርነት ወቅት በባንዳዎች ቤታቸው በመቃጠሉ፣ እናቱ ፀጋዬንና እህቱን ይዘው አምቦ አካባቢ ጎሮምቲ በሚባል ስፍራ እንደቆዩ ይነገራል። ከዚያም እናቱ የቤተክህነት ትምህርት እንዲማር አድርገው ነበር። ከዘመቻ መልስ አባቱ ከቤተክህነት ትምህርት አስጥለው ዘመናዊ ትምህርት እንዲማር በአምቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስገቡት።

እያደገ ሲሄድ በ15 ዓመቱ የመጀመሪያ ተውኔቱን ስለፍትህ የሚያወሳውን የዲዮኒሰስ እና የሁለቱ ወንድማማቾች ታሪክን ፅፎ በአምቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በንጉሱም ጭምር ታየለት፤ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይም ታተመለት። ከዚያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በጀነራል ዊንጌት ትምህርትቤት ተከታተለ። ከፍተኛ ትምህርቱን ጸጋዬ የተከታተለው በንግድ ሥራ ኮሌጅ ነው።

የቤተክህነት ትምህርትን መነሻው አድርጎ የተነሳው ፀጋዬ፣ በአገሩ የላቀውን የብላቴን ጌትነት ደረጃ በመያዝ እውቅ ባለቅኔና ሎሬት ሆኗል። በዘመናዊው ትምህርትም እስከብሪትሽ ትምህርትቤት ዘልቆ የምእራባውያኑን የድራማ ስልት ተክኗል። በእነርሱ አጠራር "ፓንቶማይም" የተባለ የድራማ አይነት ላይ ዐይኑን ጣለ።

የተውኔት አዘጋጁ፣ የታሪክ ተመራማሪው፣ ገጣሚው (ባለቅኔው)፣ ፀሐፊ ተውኔቱ፣ የሰላም አክቲቪስቱ፣ የማህበራዊ እውነታዎችን ተንታኙ፣ መምህሩ ፀጋዬ ገብረመድህን በኢትዮጵያ ስነፅሁፍ ውስጥ በታላቅነታቸው ተምሳሌት ተደርገው ከሚወሰዱት ደራሲያን መሐል አንዱ ነበር። ከፈጠራ ስራዎቹ የአብዛኞቹ ጭብጦች በማህበራዊ ህይወት ውስጥ በሚመላለሱ እውነቶች፣ በፍትህ መዛባትና ጭቆና ለሚሰቃዩ አፍሪካውያን ነፃነት፣ በጥቁሮች እኩልነትና ህብረት ላይ፣ በአፍሪካ ጥንታዊ ሚቶሎጂዎች ላይ ያተኮሩ ናቸው። በዚህም ስለአፍሪካ የነፃነት ትግል፣ ስለፍትህ፣ ስለረሃብና ጉስቁልና፣ ስለአፍሪካ ጥንታዊነትና የሰው ዘር ምንጭነት፣ ስለአፍሪካውያን ቀዳሚ ስልጣኔና እምነት፣ ስለቅኝ ገዢዎች ጭቆና፣ በርካታ ግጥሞችን፣ ከ33 በላይ ተውኔቶችን፣ ከግማሽ ደርዘን የበለጡ ግጥሞችን የያዘ መድብል ደርሶ ለዓለም አበርክቷል።

ፀጋዬ ገብረመድህን ከሀገር ውስጥ ይልቅ በይበልጥ የሚታወቀው በውጭው ዓለም ነው። ስራዎቹ በታላላቅ የአፍሪካ የስነፅሁፍ ሰዎች የተደነቁ ልዩ ክብርና አድናቆት የተቸራቸው ናቸው።

ፀጋዬ በ1990 ዓ.ም ጀምሮ ይኖርበት በነበረበት አሜሪካ ኒውዮርክ ውስጥ የካቲት 18 ቀን 1998 ዓ.ም ከሞተ በኋላ በፀሎት እንዲታሰብና ግብአተመሬቱ

በአገሩ ምድር እንዲጠናቀቅ አዲስ አበባ ሲደርስ ዝነኛው ጋዜጠኛና የስነፅሁፍ ሰው፣ ማእረጉ በዛብህ "ዛሬ ኢትዮጵያ ውድ ሐብቷን አጣች" ሲሉ መናገራቸውን የኒውዮርክ ታየምስ ጋዜጣ ዘግቧል። እንደተባለው፣ ፀጋዬ ገብረመድህን የኢትዮጵያን ስነፅሁፍ በግጥምና በቴአትር ማሳደጉና ብሔራዊ ቅርስ መሆኑም እውነት ነው።

የህይወቱ ማሳረጊያ ግጥሙም የሚከተለው ነው።

> የማይነጋ ሕልም ሳልም፣
>
> የማይድን በሽታ ሳክም፣
>
> የማያድግ ችግኝ ሳርም፣
>
> የሰው ሕይወት ስከረክም፣
>
> እኔ ለኔ ኖሬ አላውቅም፤

እውቁ ፀሐፊ ተውኔትና ባለቅኔ ፀጋዬ ገብረመድህን፣ ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያሰማ የነበረ ሰው ሲሆን፣ በዚህም የተነሳ በደርግ አገዛዝ ዘመን በመራው ሰላማዊ ሰልፍ የተነሳ ለእስርና እንግልት ተዳርጎ ነበር። እስኪሞትም ድረስ የተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ጉዞዎችን በማድረግና ልዩ ልዩ ሴሚናሮች ላይ በመሳተፍ፣ ትምህርት በመስጠት፣ ጥናታዊ ፅሁፍ በማቅረብና በኮንፈረንሶች ላይ ንግግር በማድረግ የኢትዮጵያን ጥንታዊነትና ዘመናዊውንም የባህል ስልጣኔ ለማስተዋወቅና ለማስፋፋት ጥረት አድርጓል።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ሮባ የትና መቼ ተወለደ?
2. ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ሮባ በልጅነቱ ዘመናዊ ትምህርት የጀመረው የት ትምህርት ቤት ነበር?
3. የባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ሮባ የመጀመሪያ ተውኔቱን በስንት አመቱ ጻፈ?

4. የባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ሮባ ሙያዎችን ዘርዝሩ።
5. ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ሮባ የሞተው ______ የተቀበረው ደግሞ ______ ሀገር ነው።

በስነፅሁፍ ለኖቤል ሽልማት ሊታጭ እንደሚገባው የሚገልፁ አንዳንዶች ቢኖሩም፣ የኢትዮጵያን ባለቅኔ ሎሬትነትና በስራው ለሰው ልጆች ሰብዓዊ መብት ባደረገው ጥረትና ቀና አስተሳሰቡ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን አግኝቷል።

በስራዎቹ የተነሳ ከባለቅኔ ሎሬትነቱ በተጨማሪ በ1962 ዓ.ም ከወቅቱ ንጉስ የስነፅሁፍ ሽልማት ከእጃቸው ተቀብሏል። በ1968 ዓ.ም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መዝሙርን በመድረሱ ተሸላሚ ሆኗል። የአፍሪካ ህብረት በ2002 እንደገና ሲመሰረትም ግጥሙ ማሻሻያ ተደርጎበት አገልግሎቱን ቀጥሏል። በ1974 ዓ.ም የሂዩማን ራይትስ ዎች ከኒዎርክ የዓለም ፕሬስ ኮንግሬስ ሀሳብን የመግለፅ ሽልማት ተቀብሏል።

ከፀጋዬ ስራዎች መካከል በልግ፣ የሾህ አክሊል፣ የከርሞ ሰው፣ ሁ-ሁ በስድስት ወር፣ አቡጊዳ ቀይሶ፣ መልእክተ ወዛደር፣ ሰቆቃወ ጴጥሮስ፣ ሁ-ሁ ወይም ፐ-ፑ፣ እናት ዓለም ጠኑ (የቤርቶልት ብሬሽት ተዛማጅ ትርጉም ነው)፣ ኦቴሎ፣ ሀምሌት፣ ማክቤዝ (ከሼክስፒር የተተረጎሙ)፣ ዚቀኛው ጆሮ (ከፈረንሳዩ ፀሐፌ ተውኔት ሞልዬር የተተረጎመ)፣ እና ኦዳ ኦካ ኦራክል (The Oda Oak Oracle) የተሰኙ ተውኔቶች ይጠቀሳሉ። እሳት ወይ አበባ የተባለ የግጥም መድብል ደግሞ ተወዳጁ ስራው ነው።

አባ ገዳ የተሰኘውን ግጥም መነ ገልማ አባገዳን በ1964 ዓ.ም ደቡብ ቦረና ድሬ ሊበን ሄዶ በአካል አግኝቶት በሁኔታውና በአንደበተ ርቱእነቱ ተደንቆ እዛው ቦታው ወድያው የፃፈው እንደሆነ ራሱ ተናግሯል። ፀጋዬ ግጥሙን ከመጀመሩ በፊት ገዳ ማለት ካ-አዳ፣ ካ = ፈጣሪ፣ አዳ = ስርአት፣ ባህል፣ ሃይማኖት እንደሆነ በአጠቃላይ የ‹‹ካ መመሪያ›› ወይም የፈጣሪ መመሪያ ማለት እንደሆነ ገልጿል። በዚህም የኦሮሞ ህዝብ ከቅድመ ኦሪት ጀምሮ በገዳ ስርዓት እንደሚተዳደር አብራርቷል። ከዚህ ግጥም የተወሰነ ቀንጭበን በማየት ፀጋዬ በገዳ ስርዓት ዙርያ ያለው እውቀት ጥልቅ እንደነበር መገንዘብ እንችላለን።

ኢ.ልማ ገልማ አባ ገዳ፣

ርቱእ ጀማ፣ ብፁዕ ጀማ፣ ለካ አንተ ነህ አባ ገዳ

ኢ.ልማ ገልማ፣ ያዳ ኦሮሞ ሻማ፣

ዋቃ ገዷኒ፣ ነማ ኦሊኒ፣ ሱማ አክሱማ የተባልከው ፍፁም ጀማ፣

ለካ አንተ ነህ፣ ኢጋ ኡጋ፣ ጂጋ ሎጋ

አባ ሰርዳ፣ አባ ገዳ አባ ፈርዳ፣ ነበልባሉ እምቅድመ ኦሪት ባህሉ፣

ያኢ ቢያ አባ ቃሉ፣ ቃሉ! የማይቀለበስ ቃሉ፣

ለካ አንተ ነህ፣ ሴራ አርካ

ኦጋ ገዳ የአድባር ዋርካ...

ከዚህ የምንገነዘበው ፀጋዬ የበቀለበትንና ያደገበትን ባህል ጠንቅቆ የሚያውቅና ለባህሉ ፍቅር፣ ክብርና ሞገስ የሚሰጥ የጥበብ ሰው እንደነበረ ነው።

ተውኔቶቹን በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቋንቋዎች ከመድረሱም በተጨማሪ፣ ጊዜ አይሽሬ የሆኑ የምእራባውያኑን ተውኔቶች ወደ አማርኛ በመተርጎምና ከመጥለፊያው ቋንቋና ከአገሩ ባህል ጋር አስማምቶ በመፃፍ ለኢትዮጵያ ስነፅሁፍ እድገት የጎላ አስተዋፅዖ አበርክቷል።

(ምንጭ፡ ከተለያዩ ድህረገጾች)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ።

1. ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ትምህርት የጀመረው በዘመናዊ ትምህርት ነው።

2. የባለቅኔው የሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን የመጀመሪያ ተውኔቱን ስለፍትህ የሚያወሳው የዲዮኒሰስ እና የሁለቱ ወንድማማቾች ታሪክ ነው።

3. ፀጋዬ አባ ገዳ የተሰኘውን ግጥም በ1964 ዓ.ም ደቡብ ቦረና ድሬ ሊበን በአካል ተገኝቶ እዛው እቦታው ላይ ወድያው የፃፈው ነበር።

4. እንደፀጋዬ ገዳ ማለት የፈጣሪ መመሪያ ማለት ነው።

5. ፀጋዬ በ1968 ዓ.ም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መዝሙርን በመድረሱ ተሸላሚ ሆኗል።

6. ፀጋዬ በብዛት የሰራው ተውኔቶችን ነው።

7. ፀጋዬ የተካነበት የውጭ ሀገር የድራማ ስልት ፓንቶማይም በመባል ይታወቃል።

8. ፀጋዬ የበቀለበትንና ያደገበትን ባህል ጠንቅቆ የሚያውቅና ለባህሉ ፍቅር፣ ክብርና ሞገስ የሚሰጥ የጥበብ ሰው ነበር።

9. ፀጋዬ ገብረመድህን ከሀገር ውስጥ ይልቅ በይበልጥ የሚታወቀው በውጭው ዓለም ነው።

10. ፀጋዬ በኢትዮጵያ በብላቴን ጌትነት ደረጃ የባለቅኔ ሎሬትነት ማእረግ ተሰጥቶታል።

11. ፀጋዬን ከኒዎርክ ሀሳብን በመግለፅ በሚል ምክንያት የሸለመው ደርጅት ሂዩማን ራይትስ ዎች ይባላል።

12. በስራው ለሰው ልጆች ሰብዓዊ መብት ባደረገው ጥረትና ቀና አስተሳሰቡ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን አግኝቷል።

ለ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን በመወያየት መልሱ።

1. ከዚህ በታች የቀረበውን ፀጋዬ በህይወቱ ማሳረጊያ የጻፈውን ግጥም ስታነቡ ምን ዓይነት ስሜት አደረባችሁ? ለምን?

የማይነጋ ሕልም ሳልም፣
የማይድን በሽታ ሳክም፣

የማያድግ ችግኝ ሳርም፣
የሰው ሕይወት ስከረክም፣
እኔ ለኔ ኖሬ አላውቅም፤

2. ፀጋዬ ባለብዙ ሙያ የጥበብ ሰው ነው፤ የሚባለው ለምን ይመስላችኋል? ከምንባቡ ማስረጃ በማውጣት ግለጹ።
3. ከፀጋዬ ተውኔቶች መካከል ትርጉም ያልሆኑ ወይም በቀጥታ በአማርኛ ከተጻፉት ውስጥ ስምንቱን ጥቀሱ።
4. ከፀጋዬ ተውኔቶች መካከል በቀጥታ በእንግሊዝኛ ከተፃፉት መካከል አንዱን ጥቀሱ።
5. ከፀጋዬ ተውኔቶች መካከል የትርጉም ስራዎች መካከል አራት ያህሉን ጥቀሱ።
6. ጋዜጠኛው ‹‹ዛሬ ኢትዮጵያ ውድ ሐብቷን አጣች›› ያለው ለምን ይመስላችኋል?
7. ከግማሽ ደርዘን የበለጡ የግጥም ስብስቦቹ ምን በሚል ርእስ ታተሙ?
8. የፀጋዬ የአብዛኛዎቹ የፈጠራ ስራዎቹ ጭብጦች ምን ምን ናቸው?

### ተግባር ሁለት

ወደቤተመጻህፍት በመሄድ ወይም በይነመረብ በመጠቀም ስለተውኔት አይነቶች (ኮሜዲ፣ ትራጄዲ፣ ድንቃይ፣ ቧልታይ) መረጃ በመሰብሰብ በአንቀጽ ካደራጃችሁ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች በንባብ አቅርቡ።

# ትምህርት አራት፤ መጻፍ

በዚህ ትምህርት እንድትጽፉ የሚመራ ተግባር ስለቀረበላችሁ ተግባሩን በትኩረት ስሩ።

## ተግባር ሦስት

1. ፀጋዬ “አባ ገዳ” በሚል ርእስ የፃፈው ግጥም በራሱ ድምፅ (በኦዲዮ) ተቀድቶ ለህዝብ ተሰራጭቷል። ይህን ግጥም ከማህበራዊ ሚዲያዎች አፈላልጋችሁ ካዳመጣችሁ በኋላ በምንባቡ ውስጥ አባ ገዳ በሚል የቀረበውን ጅምር ግጥም አጠናቃችሁ በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው።

2. የፀጋዬ የተውኔት ስራዎች በመፅሃፍ መልክ ታትመው ለህዝብ የተሰራጩ በመሆናቸው እነዚህን ስራዎች ከቤተመጻህፍት ወይም ከማህበራዊ ሚዲያዎች በማፈላለግ ከአንዱ ስራው የተወሰኑ የገፀባህርያትን ምልልሶች ጽፋችሁ ወደክፍል በማምጣት ከጓደኞቻችሁ ጋር አጥኑት። በትወና መልክም ተለማምዳችሁ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ።

3. በትምህርት ሁለት ተግባር አንድ ስር የቀረበውን ጅምር ቅንጫቢ ተውኔት በራሳችሁ መንገድ ቃለ ተውኔቱን አጠናቃችሁ ጻፉ።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ክፍል በማዳመጥና በማንበብ ትምህርቶች ከቀረቡ ጽሁፎች የወጡ አረፍተነገሮች ውስጥ ለሚገኙ ቃላት ወይም ሀረጋት አውዳዊ ፍቺ ትሰጣላችሁ።

### መልመጃ ሦስት

በሚከተሉት አረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ወይም ሀረጋት በምሳሌው መሰረት በተመሳሳይ ቃል ተኩዋቸው።

ምሳሌ፡ እኔ ለቤተሰቦቼ የበኩር ልጅ ነኝ።
እኔ ለቤተሰቦቼ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ።

1. የናቴን ጡት እንኳ ያልጣልኩ ገና እርም ታህል ልጅ ነኝ።

2. እንዳላገጥክብኝ አትቀርም እቀጣሃለሁ።

3. ከማጥፋቱ ማስተባበሉ ያበሳጫል።
4. በውስጥ ባንዳዎች ቤታቸው ተቃጠለ።
5. ፀጋዬ በአገሩ የላቀውን የብላቴን ጌትነት ደረጃ በመያዝ እውቅ ባለቅኔና ሎሬት ሆኗል።
6. ፀጋዬ ጊዜ አይሽሬ የሆኑ የምእራባውያኑን ተውኔቶች ወደ አማርኛ ተርጉሟል።
7. እሳት ወይ አበባ የተባለው የግጥም መድብል የፀጋዬ ተወዳጅ ስራው ነው።
8. ፀጋዬ በስነፅሁፍ ለኖቤል ሽልማት ሊታጭ ይገባው እንደነበረ የሚገልፁ ምሁራን ነበሩ።

# ትምህርት ስድስት: ሰዋስው

በዚህ ትምህርት የምእላድንና የቃልን አንድነትና ልዩነት የሚያብራራ ማስታወሻና ማስታወሻውን መሰረት ያደረገ መልመጃ ቀርቦላችኋል። ማስታወሻውን በጥሞና ካጠናችሁ በኋላ መልመጃውን በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

## የምእላድና ቃል አንድነትና ልዩነት

ትርጉም አልባ ድምጸች ስርአት ባለው መንገድ ተቀናጅተው ትርጉም ያለውን አሃድ ያስገኛሉ። በዚህ ሁኔታ የሚገኝ ትርጉም ያለው አሃድ ምእላድ ይባላል። ምእላድ ትርጉም አዘል የሆነ የመጨረሻ ንኡስ አሃድ ነው። ይህም ማለት ምእላድ ወደሌላ አነስተኛ ትርጉም ያለው አሃድ ሊከፈል አይችልም ማለት ነው።

ምሳሌ: በጎች = (በግ - ኦች) “በጎች” ቃል እንጂ ምእላድ አይደለም፤ ምክንያቱ ደግሞ ትርጉም ወደሚሰጡ ሁለት አሃዶች ስለተከፈለ ነው። ሁለቱ ክፋዮች ግን ምእላዶች ናቸው፤ ምክንያቱም ትርጉም ይሰጣሉ፤ እንዲሁም ወደሌላ ትርጉም ወደሚሰጥ ሌላ አሃድ መከፈል አይችሉም። ቃል ከአንድ ወይም ከአንድ በላይ ከሆኑ ምእላዶች የሚመሰረት ነው። ስለዚህ ቃል ላይ ብዙ ትርጉም አዘል አሃዶች ተቀጥለው ሊገኙ ይችላሉ ማለት ነው። ምሳሌ: በጎቻችን =(በግ - ኦች - ኣችን) በዚህ ምሳሌ “በግ”

ቃልም ምእላድም ነው። "- ኦች እና - ኦችን" ምእላድ ናቸው። በሌላ አነጋገር "በግ" ነጻ ምእላድ ነው። "- ኦች እና - ኦችን" ደግሞ ጥገኛ ምእላዶች ናቸው።

በአጠቃላይ በምእላድና በቃል መካከል አንድነትም ልዩነትም አለ። አንድነታቸውና ልዩነታቸው በአጭሩ የሚከተለውን ይመስላል።

- ሁለቱም ትርጉም አላቸው።
- ቃል ነጻ በመሆኑ ራሱን ችሎ ይቆማል። ይህም ከነጻ ምእላድ ጋር አንድ ያደርገዋል።
- ምእላድ ወደትርጉም አዘል አሃድ ሊከፋፈል አይችልም። ቃል ግን ትርጉም አዘል ወደሆኑ አሃዶች ሊከፋፈል ይችላል፡፣
- ቃል የቋንቋው ቃላት ከሚመዱባቸው የቃል ክፍሎች የአንዱ ክፍል አባል መሆን ይችላል።

ጌታሁን አማረ (2011)

## መልመጃ አራት

ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን በምሳሌው መሰረት ቃል ወይም ቃልና ምእላድ በማለት ለዩ።

1. ቤት = ቃልና ምእላድ
2. ቤቶች = ቃል
3. ቤቱ
4. ቤቴ
5. ቤቷ
6. ቤታችን
7. ልብ
8. ልባሞች
9. ልቤ
10. ልቡ
11. ልቦች

ለ. በ "ሀ" ስር የቀረቡትን ቃላት ትርጉም ወደሚሰጥ አሃድ ሊከፈሉ የሚችሉትን በምሳሌው መሰረት ከፋፍላችሁ ከዚህ በታች በቀረበው

ሰንጠረዥ ውስጥ በነጻ ምእላድና በጥገኛ ምእላድ ስር መድቧቸው።

| ቃል | ክፋዮች | ነጻ ምእላድ | ጥገኛ ምእላድ |
|---|---|---|---|
| ቤት | ----- | ቤት | ---- |
| ቤቶች | ቤት - ኦች | ቤት | - ኦች |
| ቤቱ | | | |
| ቤቴ | | | |
| ቤቷ | | | |
| ቤታችን | | | |
| ልብ | | | |
| ልባሞች | | | |

## የምእራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ተውኔትን በሚመለከት የተለያዩ ይዘቶች ቀርበዋል። ተውኔት የስነጽሁፍ ዘርፍ መሆኑን፣ በመድረክ ላይ የሚቀርብ መሆኑን፣ የማኅበረሰቡን ገጽታ በማሳየት ከሌሎች የስነ-ጽሁፍ ዘርፎች የሚጋሯቸው ኪነጥበባዊ ባህርያት ቢኖሩትም ገና ከመነሻው በተዋንያን አማካኝነት በመድረክ ላይ የሚደረስ በመሆኑ በአያሌው መለየቱን ተምራችኋል።

ተውኔት በመድረክ ላይ ስለሚቀርብ የተመልካቹን ትኩረትና ስሜት የመሳብ ከፍተኛ ኃይል ያለው መሆኑን ተመልክታችኋል። ተውኔት የሚቀርብበትን መድረክ የተሟላ ለማድረግ የተለያዩ ባለሙያዎች የሚሳተፉ መሆኑን ተምራችኋል። መቼት፣ ገጸባህርይ፣ ሴራ፣ ቃለተውኔት፣ ጭብጥ የተውኔት አላባውያን መሆናቸውን ተምራችኋል።እንዲሁም ስለእያንዳንዳቸው ተግባር በሠራችኋቸው የመልመጃ ጥያቄዎች አማካኝነት ተመልክታችኋል።

የተውኔት መልልስን ተግብራችኋል።እንዲሁም የ"ጸሀፊ ተውኔትና ባለቅኔው ሎሬት" በሚለው ምንባብ መነሻነት በርካታ ተውኔቶች ስለደረሱት ጸጋዬ ገብረመድህን ስራዎች ግንዛቤ ከመውሰድም ባሻገር ተግባራዊ የተውኔት ልምምድ አድርጋችኋል።

ለአዳዲስ ቃላት አውዳዊ ፍቺ ሰጥታችኋል።እንዲሁም ምእላድ ትርጉም የሚሰጥና ወደሌላ ትርጉም ወደሚሰጥ ሌላ አሃድ ሊከፋፈል የማይችል የመጨረሻ የቋንቋ ክፍል እንደሆነ፣ ቃል ምንም ቅጥያ ከሌለው ነጻ ምእላድ ሊባል እንደሚችልና ቅጥያዎችን ካስጠጋ ግን ቃል እንጂ ምእላድ እንዳልሆነ ተረድታችኋል።

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ተውኔት ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘርፎች የሚለይበትን መሠረታዊ ባህርይ ጻፉ።
2. ተውኔት የሚቀርብበትን መድረክ ድባብ የተሟላ ለማድረግ ከሚሳተፉት ባለሙያዎች ውስጥ ቢያንስ የሁለቱን ስምና ተግባር ግለጹ።

3. የአንድ ተውኔት ትርጉም በምን በምን ሊመዘን ይችላል።
4. ከተውኔት ዓይነቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ግለጹ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች እንደገና አንብቡ።

| | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የተውኔትን ምንነት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | የተውኔት አላባውያንን መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 3 | ተዋናይ ማለት ምን ማለት እንደሆነ መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 4 | በተውኔት ውስጥ የሚሳተፉትን ባለሙያዎችና ተግባራቸውን መዘርዘር ችያለሁ | | | |
| 5 | የተውኔት መዋቅርን ማብራራት ችያለሁ | | | |
| 6 | ተውኔት መተወን ችያለሁ | | | |
| 7 | የተውኔት ዓይነቶችን ማብራራት ችያለሁ | | | |
| 8 | የተውኔት ምልልሶችን ተውኛለሁ፤ አጠናቅቄ ጽፌአለሁ። | | | |
| 9 | የቃላትን አውዳዊ ፍቺ አብራርቻለሁ | | | |
| 10 | የቃላትንና ምእላዶችን አንድነትና ልዩነት ተገንዝቤያለሁ | | | |

# ምእራፍ ዘጠኝ

## መገናኛ ብዙኃን

### የሚጠበቁ ውጤቶች

ተማሪዎች የዚህን ምእራፍ ትምህርት ካጠናቀቃችሁ በኋላ፡-

- አዳምጣችሁ ማጠቃለያ ትሰጣላችሁ።
- በሰዎች ፊት ለፊት ንግግር ታቀርባላችሁ።
- አንብባችሁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ትሰራላችሁ።
- ጅምር ሃሳቦችን አጠቃላችሁ ትጽፋላችሁ።
- ማስታወቂያዎችን ትጽፋላችሁ።
- የቃላትን ትርጉም ከአውዱ ውስጥ ታወጣላችሁ።
- ጥገኛ አረፍተነገሮችን ይለያሉ።

## ትምህርት አንድ፡ ማዳመጥ

በዚህ ትምህርት የሚቀርብላችሁን ቃለምልልስ ከማዳመጣችሁ በፊት የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎችን፣ እያዳመጣችሁ የጊዜ ማዳመጥ ጥያቄዎችን እና ካዳመጣችሁ በኋላ የድህረማዳመጥ ጥያቄዎችን ስሩ።

## የቅድመማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመወያየት የጋራ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

1. ጋዜጠኝነት ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. ቃለምልልስ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍቺያቸውን ገምቱ።

1. ታዋቂነት
2. መረጃ
3. እፍታ
4. ኮሚቴ
5. ሊቃውንት

## የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ባዳመጣችሁት ቃለምልልስ ውስጥ ጋዜጠኛው ከየትኛው የመገናኛ ብዙኃን የመጣ ነው?
2. ቃለምልልስ ሰጪው ግለሰብ የምን ኮሚቴ አባል ናቸው?
3. የጋዜጠኛውን ጥያቄዎችና የቃለምልልስ ሰጪውን ዋና ዋና መልሶች በማስታወሻ ደብተራችሁ ያዙ።

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ አንድ

ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በትእዛዛቸው መሰረት መልሱ።

1. የቃለምልልሱ ዋና ጉዳይ ምን ነበር?
2. የቃለምልልሱ መግቢያ ላይ ምን አይነት የቋንቋ አጠቃቀም አስተዋላችሁ?
3. ወደቃለምልልሱ ዋና ጉዳይ ከመገባቱ በፊት ሁለቱ አካላት ስለምን ጉዳይ አወሩ?

4. ወደቃለምልልሱ ዋና ጉዳይ ከመዝለቃቸው በፊት ጋዜጠኛው የቃለምልልስ ሰጪውን ይሁንታ የጠየቀው በምን ጉዳይ ነበር?

5. ጋዜጠኛው ሲጠይቅ ቃለምልልስ ሰጪው የሰጣቸው መልሶች እንዲህ ባይሆን ኖሮ፣ እንዲህ ቢሆን ኖሮ የምትሉት ካለ ግለጹ።

6. የቃለምልልሱ ማጠቃለያ ላይ አስተያየት ከሰጣችሁ በኋላ የራሳችሁን ማጠቃለያ ስጡ።

### ተግባር አንድ

በሳምንቱ ከተላለፉ የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን የስፖርት ውድድር ዘገባ አንዱን ጉዳይ መርጣችሁ አዳምጡና ለክፍል ተማሪዎች የቃል ዘገባ አቅርቡ።

## ትምህርት ሁለት፡ መናገር

በዚህ ትምህርት ሃሳብን አጠቃላችሁ እንድታቀርቡና ቃለምልልስ እንድታደርጉ የሚመራ ተግባር ስለቀረበላችሁ ተግባሩን በትእዛዙ መሰረት ስሩ።

### ተግባር ሁለት

በማዳመጥ ትምህርት ክፍል የቀረበውን ቃለምልልስ በማስታወስ በጋዜጠኛውና በቃለምልልስ ሰጪው አማካኝነት የተላለፈውን መልዕክት ጠቅለል አድርጋችሁ በቃል አቅርቡ።

### ተግባር ሦስት

በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የተላለፉ ማስተወቂያዎችን ካነበባችሁ በኋላ ማስታወቂያውን ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ።

# ትምህርት ሦስት፡ ማንበብ

በዚህ ትምህርት "መገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኝነት" በሚል ርእስ የቀረበ ጽሁፍ ከማንበባችሁ በፊት የቅድመማንበብ ጥያቄዎችን፣ እያነበባችሁ የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎችን፣ ካነበባችሁ በኋላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ስሩ።

## የቅድመማንበብ ጥያቄዎች

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመወያየት የጋራ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ።

1. መገናኛ ብዙኃን ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?
2. የምታውቋቸውን የመገናኛ ብዙኃን አይነቶች ዘርዝሩ።

## መገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኝነት

መገናኛ ብዙኃን መረጃዎችን ለህብረተሰቡ በተለያዩ አማራጮች ለማድረስየሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው። እነዚህ የመረጃ ማሰራጫ መንገዶችም የህትመት ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን ሊሆኑ ይችላሉ። የህትመት መገናኛ ብዙኃን የሚበሉት ጋዜጦች፣ መፅሔቶች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ወዘተ. ሲሆኑ፣ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን የሚባሉት ደግሞ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ በይነ መረብና የመሳሰሉት ናቸው። በኤሌክትሮኒክስም ሆነ በህትመት መገናኛ ብዙኃን በየቀኑ የሚቀርቡት መረጃዎች የሁነቶች ወይም የድርጊቶች ዝርዝር ቁም ነገር ቢሆንም መረጃዎቹ የሚቀርቡበት ጊዜ እና ፍጥነት የተለያየ ነው። በተለይ ከኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን ውስጥ አንዱ የሆነው የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን በፍጥነት በርካታና የተለያዩ መረጃዎች ይተላለፉበታል። ይህ ደግሞ ከሰው ልጆች የመፍጠር ችሎታ ጋር የተገናኘ ነው።

የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ አውታሮች በተለይም በስልክና በበይነ መረብ

ረገድ ከቀን ወደ ቀን አዳዲስ ግኝቶች እና የመሻሻል ለውጦች እየተስተዋሉ ናቸው። የመሻሻሉ ፍጥነት የሚያስደምመው ደግሞ ሰዎች አንዱን ግኝት በአግባቡ አውቀውና ተጠቅመው ሳይጨርሱ ሌላ መምጣቱ ነው። በቀናት፣ በወራት፣ ምናልባትም በዓመታት በደብዳቤ አማካኝነት ናፍቆትን የሚለዋወጡበት፣ መልዕክት የሚቀባበሉበት፣ የፖስታ ቤትን ደጅ የሚጠኑበት ጊዜ በኢ-ሜይል ከተቀየረ ዓመታት ተቆጥረዋል። ከሰከንዶች ባነሰ ፍጥነት በበይነ መረብ አማካኝነት ግንኙነት የሚፈጠርበት ይህ ቴክኖሎጂ አድጎ ቲውተርን፣ ኢሞን፣ ሜሴንጀርን፣ ቫይበርን፣ ቴሌግራምን፣ ፌስቡክን፣ ወዘተ. ሊፈጥር ችሏል። ይህ ቴክኖሎጂ ናፍቆትን ከማስቀረት ባለፈ ማን፣ የትና እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚገኝ ለማወቅም ተችሏል።

ዛሬ የሰው ልጅ ብዙ ጊዜውን አብዝቶ ከሚያሳልፍባቸው ጉዳዮች ማህበራዊ ድህረገፆች ዋነኞቹ እንደሆኑ ጥናቶች ያመላክታሉ። ማህበራዊ ድህረገፆች ለፈጣን መረጃ ልውውጥና ለተለያዩ ሀገራት ህዝቦች መቀራረብ ያላቸው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው። በአንፃሩ አላስፈላጊ ያታዊ ትንኮሳ፣ ለማይጠቅሙ ምስሎችና መረጃዎች ልውውጥ፣ እንዲሁም አላስፈላጊ ለሆኑ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መልዕክቶች የተመቹ በመሆናቸው ስጋትን መፍጠራቸው አይቀርም። ያም ተባለ ይህ ማህበራዊ ድህረገፆች በርካታ ጥቅሞች እንዳላቸው ሁሉ ዘርፈብዙ ጉዳትን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በማሰብ አጠቃቀምን ማስተካከል ተገቢ ነው።

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. የኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን በመባል የሚጠሩት ምን ምን ናቸው?
2. የህትመት መገናኛ ብዙኃን የሚባሉት የትኞቹ ናቸው?
3. ደብዳቤ ለመላክ ከፖስታ ቤት ደጅ መጥናትን ያስቀረው ምንድን ነው?
4. በአሁኑ ጊዜ የሰው ልጅ ብዙ ጊዜውን የሚያሳልፈው የት ነው?

ጋዜጠኝነት ለጋዜጣ፣ ለመፅሔት፣ ለሬዲዮ፣ ለቴሌቪዥን፣ ለዜና አገልግሎትና ለተለያዩ የበይነመረብ መገናኛ አውታሮች ዜናዎችን፣ አጫጭርና ረጃጅም መጣጥፎችን፣ የሐተታ ፅሁፎችንና ርእሰአንቀጾችን፣ እንዲሁም የቴሌቪዥንመርሀግብሮችን የማቅረብ ሙያ ነው። ጋዜጠኝነት ከሙያ እይታ ተነስቶ ማቀድን፣ መረጃ መሰብሰብን፣ መጻፍንና የአርትኦት ስራ ማከናወንን ይጠይቃል። ጋዜጠኝነት የተጠናቀረ ቅርፅና ይዘት መያዝ የቻለው ዮሀን ጉተንበርግ የተባለው ጀርመናዊ እንደአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1450ዎቹ በአውሮፓ የመጀመሪያውን ማተሚያ መሳሪያ ፈልሰፎ ስራ ላይ ካዋለ በኋላ ነው። ዘግይተው የተፈለሰፉት ሬዲዮና ቴሌቪዥንም ለጋዜጠኝነት ሙያ መዳበር ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል።

ጋዜጠኞች የሚያቀርቧቸው ፅሁፎች፣ አስተያየቶችና መርሀግብሮች ሁሉ የሚተላለፉት ከተራው ሰው ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ላሉት ተደራሲያን ነው። ስለሆነም ጋዜጠኛው የሚያቀርባቸው የስራ ውጤቶች ለሁሉም ተደራሲዎች በየፈርጁ በቂ ግንዛቤ የሚሰጡና ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል።

ጋዜጠኝነት የህዝባዊ አገልግሎት ባህሪ ያለው ሙያ እንደመሆኑ መጠን እንደ እኛ ባሉ በልማት ባልገፉ ሀገሮች የማህበራዊ ኑሮ እድገትን፣ የኢኮኖሚ ልማትን፣ የባህል ትንሳኤንና መስፋፋትን፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ሁለንተናዊ የአገር ግንባታን በማፋጠን ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። የሙያው ዋና ዓላማ ህብረተሰቡን ማሳወቅ፣ ማስተማርና ማዝናናት ሲሆን፣ የማህበራዊ ኑሮን አስተሳሰብ በመለወጥም የሚያደርገው አስተዋፅኦ ልዩና ወሳኝ ነው።

ጋዜጠኝነት ታላቅ ዝናን፣ እውቅናን የሚያስገኝ ሙያ የመሆኑን ያህል ዝና እና እውቅና ለማግኘት የሚከፈለው መስዋዕትነትና አገልግሎትም እጅግ ከባድና ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአህጉራችን ህይወታቸውን ለሙያቸው ሲሉ የሠው፣ ለሃቅ በመቆማቸው ብቻ በፀረ-ሃቅ ወገኖች ጥይት

የወደቁ ጀግኖች ጋዜጠኞች ቁጥር ጥቂት አይደለም።

በሀገራችን ህብረተሰቡ ጋዜጠኛ ሁሉ በጣም የተማረ፣ በሙያው የሰለጠነ፣ ብዙ የሚያነብና የሚመራመር፣ ሁሉን ነገር የሚያውቅ፣ ለችግሩ ሁሉ መፍትሔ ያለው፣ ለእውነትና ለህዝባዊ መብት የሚታገል፣ የደረጀ እውቀትና ከፍተኛ የህይወት ልምድ ያቀናጀና ያካተተ እንደሆነ አድርጎ ይመለከታል። ነገር ግን በመንግስትም ሆነ በግል መገናኛ ብዙሃን የሚሰሩ ጋዜጠኞች ሁሉም እነኝህን መለኪያዎች ሙሉ በሙሉ በብቃት ያሟላሉ ወይ ብለን ስንጠይቅ አወንታዊ መልስ ማግኘቱ ያዳግታል።

(ምንጭ፡- ማዕረጉ በዛብህ (1995) የጋዜጠኝነት ሙያ ንደፈሃሳብና አተገባበሩ ከሚለውን ላይ ለማስተማሪያ እንዲሆን ተሻሽሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

### መልመጃ ሁለት

ሀ. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።

1. የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታ በመገናኛ ብዙኃን ለሚተላለፉ መረጃዎች ብዛትና ፍጥነት መሻሻል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው።
2. የሬዲዮና የቴሌቪዥን መፈልሰፍ ለጋዜጠኝነት ሙያ እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል።
3. የበይነመረብ መገናኛ ብዙኃን ጥቅማቸው እንጂ ጉዳታቸው የጎላ አይደለም።
4. ጋዜጠኝነት ምንም ዓይነት መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ሙያ አይደለም።

5. ጋዜጠኝነት ለሀገር ግንባታና እድገት ወሳኝ ሚና አለው።
6. ሁሉም ጋዜጠኞች የሙያ ብቃት መለኪያዎችን በሙሉ ያሟላሉ።

ለ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ በጽሁፍ ስጡ።

1. ጋዜጠኝነት የተጠናቀረ ቅርፅ እንዲይዝ የተደረገው መቼ ነው?
2. በጋዜጠኝነት ሙያ የሚከናወኑ ተግባራት ምን ምን ናቸው?
3. የሀገራችን ህዝብ ለጋዜጠኞች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?
4. የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃንን ጥቅምና ጉዳት አብራሩ።
5. በህትመትና በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ዘርዝሩ።
6. የጋዜጠኝነት ሙያ ብቃት መለኪያዎችን ዘርዝሩ።

# ትምህርት አራት፡ መጻፍ

በዚህ ትምህርት ጅምር ሃሳቦችን አጠቃላችሁ እንድትጽፉና ማስታወቂያዎችን እንድታዘጋጁ የሚመሩ ተግባራት ስለቀረቡ ተግባራቱን በትእዛዛቸው መሰረት ስሩ።

## ተግባር አራት

ከዚህ በታች ሁለት የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዙ ጅምር ጽሁፎች ቀርበዋል። እነዚህን ጅምር ሀሳብ የያዙ ጽሁፎችን አጠቃላችሁ ጻፏቸው።

1. የጋዜጠኝነት ሙያ የተለያዩ የብቃት መለኪያዎች አሉት።እነ

2. ሱም____________________________________________

________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________።

3. ማህበራዊ መገናኛዎች የየራሳቸው ጠቃሚና ጎጂ ጎኖች አሏቸው።ከጠቃሚ ጎኖች መካከል ፈጣን የመረጃ ልውውጥ ማሳለጥ እና የህዝብን የእርስበርስ መስተጋብር ማጎልበት የሚሉት ይጠቀሳሉ። በሌላ በኩል በርካታ ጎጂ ጎናቸውንም መጥቀስ ይቻላል። ለምሳሌ ____________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

____________________________________________________________

_________።

## ተግባር አምስት

በቡድን በመሆን የተለያዩ ምርትና አገለግሎቶችን ለማስተዋወቅ የሚያስችላችሁን ማስታወቂያ ጻፉ። የምትጽፉት ማስታወቂያ ምርትና አገልግሎቶችን የሚያሳዩ ፎቶዎችን ወይም ምስሎችን ያካተተ መሆን አለበት። የጻፋችሁትን ማስታወቂያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ካነበባችሁ በኋላ ማስታወቂያው ምን ያህል ውጤታማ እንደነበር ግብረመልስ እንዲሰጧችሁ አድርጉ።

# ትምህርት አምስት፡ ቃላት

በዚህ ትምህርት የቃላትን አገባባዊ ፍቺ እንድትገልጹ የሚያዝ መልመጃ ስለቀረበላችሁ በስሩ የተካተቱ ጥያቄዎችን በትኩረት መሰረት ስሩ።

## መልመጃ ሦስት

ሀ. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን አገባባዊ ፍቺ ከሰጣችሁ በኋላ የራሳችሁን አረፍተነገር መስርቱባቸው።

ምሳሌ፡ ይተላለፍበታል = ይሰራጭበታል

በሚኒ ሚዲያ በትምህርት ቤታችን የሚከናወኑ አንኳር ጉዳዮች ይተላለፍበታል።

1. ግኝቶች
2. የሚያስደምመው
3. ደጅ የሚጠኑበት
4. ፈልስፎ
5. ተደራሲዎች
6. ትንሳኤ

ለ. ከዚህ በታች በቀረቡ አረፍተነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ቃላት በምሳሌው መሰረት በተመሳሳይ ቃላት ተኩ።

ምሳሌ፡ ጉንፋን ብዙ ጊዜ ከአንዱ ወደሌላው የሚሰራጨው በትንፋሽ

አማካኝነት ነው።

ጉንፋን ብዙ ጊዜ ከአንዱ ወደሌላው የሚተላለፈው በትንፋሽ

አማካኝነት ነው።

1. ጤንነቱ ያልተጠበቀ ትውልድ ተመራማሪ፣ ችግር ፈቺና ፈጣሪ የመሆን እድሉ የመነመነ ነው።
2. ልቦለድ የእውነታው አለም ነፀብራቅ እንጅ ዘገባ አይደለም።
3. በስራዬ ላይ ያልጠበኩት አሜኬላ ገጠመኝ።
4. በህቡዕ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት ወንጀለኞች በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋሉ።

# ትምህርት ስድስት፡ ሰዋስው

በዚህ ትምህርት ስለጥገኛ አረፍተነገሮች የቀረበላችሁን ማስታወሻ መሰረት አድርጋችሁ የቀረበውን መልመጃ ስሩ።

## ጥገኛ አረፍተነገር

ጥገኛ አረፍተነገር የሚባሉት የሚገልጹትን ሀሳብ የማይቋጩና በግሶች ላይ ጥገኛ የሚያደርጋቸውን ቅጥያ የቀጠሉ ናቸው። እንደዚህ ያሉ አረፍተነገሮች ጥገኛ የተባሉበት ምክንያት በሌላ ሀረግ ውስጥ ጥገኛ ሆነው ስለሚገቡ ነው።

ምሳሌ፡ ኩመሺ መኪና እንደገዛች ሰምተናል።

ጥገኛ አረፍተነገር፡ ኩመሺ መኪና እንደገዛች

ጌታሁን አማረ (2011)

### መልመጃ አራት

ከዚህ በታች በቀረቡት አረፍተነገሮች ውስጥ ተካተው የሚገኙትን ጥገኛ አረፍተነገሮች ለይታችሁ አመልክቱ።

ምሳሌ፡ መጽሐፉን አንብቤ ጨርሼዋለሁ።

ጥገኛ አረፍተነገር፡ መጽሐፉን አንብቤ

1. ዘገባውን ያዘጋጀሁበትን ቀን አስታውሰዋለሁ።
2. ሁልጊዜ የሚያጠኑ ተማሪዎች አመርቂ ውጤት ያስመዘግባሉ።
3. በሀሳብ ሲብሰለሰል ቆየ።
4. ስኬታማ ስለሆንኩ ደስተኛ ነኝ።
5. ሀገሩን የሚወድ ትውልድ ራሱን ለማሻሻል ይጥራል።

## የምእራፉ ማጠቃለያ

ምእራፍ ዘጠኝ ጋዜጠኝነት በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆንበስሩም የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል። በማዳመጥ ክፍል ውስጥ የጋዜጠኝነትን ምንነት፣ የቃለ ምልልስን ምንነት፣ በመገኛኛ ብዙኃን ባለሙያ እና በቃለ ምልልስ ሰጪው መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በሚመለከት በቅድመማዳመጥ ክፍል ተወያይታችኋል። ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በመስራት ተለማምዳችኋል።

በክፍል ሁለት የቃለምልልስ ልምምድ አድርጋችኋል። በክፍል ሦስት ደግሞ "መገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኝነት" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የተለያዩ የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሰርታችኋል። በክፍል አራት ጅምር ሀሳብን ማጠቃለል፣ ማስታወቂያ መጻፍን የጽሁፍ ዘገባ መዘጋጀትን ተምራችኋል። በክፍል አምስት ከምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ቃላትን አገባባዊ ፍቺ መግለጽን እንዲሁም በክፍል ስድስት ጥገኛ አረፍተነገር መለየትን ተምራችኋል።

## የምእራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በትኩረት ስሩ።

1. መገናኛ ብዙሀን ማለት ምን ማለት ነው?
2. የቃለምልልስ ዋነኛ ዓላማ ምንድን ነው?
3. በሬዲዮ ወይም በጋዜጣ ወይም በቴሌቪዥን ወይም በተለያዩ ማኅበራዊ መገናኛ ብዙሀን የሚቀርቡ ማስታወቂያዎች ምን ጠቀሜታ አላቸው?
4. የማወዳወር እና የማነጻጸር ተግባር ያላቸውን ሦስት ሀረጋት ጻፉ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል። በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ። የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ይዘቶች እንደገና አንብቡ።

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የአዳምጠና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን መስራት ችያለሁ | | | |
| 2 | ጅምር ሃሳቦችን ማጠቃለል ችያለሁ | | | |
| 3 | ቃለምልልስ ማድረግ ተለማምጃለሁ | | | |
| 4 | ማስታወቂያዎችን መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 5 | ጥገኛ አረፍተነገሮችን መለየት ችያለሁ | | | |

# ሙዳየ ቃላት

| ቃል | ፍቺ |
|---|---|
| ሀሴት | ደስታ |
| ሂስ | በደካማ ጎን ላይ የሚያተኩር አስተያየትና ነቀፋ፣ በስነ ጽሁፍ ሥራ ላይ የሚሰነዘር መዛኝ አስተያየት |
| ሌጣ | ነጠላ፣ ብቸኛ፣ ምንም ያልያዘ፣ ባዶ፣ የምታጠባው የምታዝለው ወይም በሆዷ የተረገዘ ልጅ የሌላት |
| መመረቅ | መባረክ፣ መቀደስ፣ ማመስገን፣ ጭማሪ መስጠት |
| መስተጋብር | አንድ ነገር ከሌላው ጋር ያለው ግንኙነት |
| መስዋእት | ለአምልኮ የሚሰጥ፣ የሚቀርብ ስጦታ፣ ህይወቱን አሳልፎ ሰጠ |
| መብረቅ | የሰማይ ብልጭታን ተከትሎ የሚሰማ ከፍተኛ የፍንዳታ ድምጽ፣ ነጎድጓድ |
| ማእበል | ኃይለኛ ነፋስ በባህር፣ በውቅያኖስ ላይ የሚፈጥረው የውሃ መናወጥ፣ ሞገድ |
| መከላከል | ማገድ፣ ማጠር፣ መዝጋት፣ ማቆም፣ |
| መዋቢያ | ማማሪያ፣ መቆነጃጃ፣ መሸገኛ |
| መደብ | ከጭቃ፣ ከአፈር፣ የሚሰራ መኝታ፣ የህብረተሰብ ክፍፍል የሚያመለክት፣ ከቅርጫት ስጋ አንዱ ክፍል፣ ችግኝ ለማፍላት የሚዘጋጅ ቦታ፣ |
| መግነጢስ | ብረትን ወደራሱ የሚስብ ብረት (ማግኔት) |
| ማመጣጠን | እኩል ማድረግ፣ አቻ ማድረግ |
| ማስተዋል | መመልከት፣ መቃኘት፣ መመርመር፣ ልብ ማድረግ |
| ማዜም | መዝፈን፣ ማቀንቀን |
| ማደራጀት | ማዋቀር፣ ሥርዓት ማስያዝ |

| | |
|---|---|
| ማፈግፈግ | ወደኋላ መመለስ፣ መሸሽ፣ በአቋም አለመጽናት |
| ምሰሶ | አምድ፣ ረጅም እንጨት፣ መለሎነት ያለው በቤት መካከል ቆሞ ዋልታ የሚሸከም፣ የኤሌክትሪክ የስልክ ... ሽቦ የሚዘረጋበት ቀጥ ያለ ረዥምና መጠነኛ ውፍረት ያለው እንጨት |
| ምንጭ | የአንድ ነገር መገኛ፣ መነሻ፣ ምክንያት፣ መረጃ፣ ከመሬት ውስጥ እየወጣ የሚፈስ ውሃ፣ መፍለቂያ |
| ሰቀቀን | የናፍቆት፣ የሀዘን፣ የችግር፣ አግኝቶ የማጣት ስሜት |
| ሰናይ | መልካም |
| ስርጭት | መተላለፍ፣ ብዙ ቦታ መድረስ |
| ስብ | ነጭና ቅባትነት ያለው ጮማ ስጋ፣ በዕፅዋት ወይም በእንስሳት ውስጥ የሚከማችና ባስፈለገ ጊዜ ኃይል የመስጠት ጠቀሜታ ያለው፣ ለም የዳበረ መሬት፣ ወፍራም ደንዳና |
| ረቂቅ | በጣም የላመ፣ የደቀቀ፣ ጥንቃቄና ጥበብ የሚጠይቅ የጌጣጌጥ ሥራ፣ ለማንበብ የሚያስቸግር በትንንሽ ፊደል የተጻፈ፤ በዓይን የማይታይ፣ በእጅ የማይዳሰስ፣ ውበውስብስብነቱ የተነሳ በቀላሉ ለማየት የማይቻል፣ ሊጨመርበት ወይም ሊቀነስበት የሚችል የመጀመሪያ ጽሁፍ |
| ረባዳ | በተራራዎችና በአምባ ምድሮች መካከል የሚገኝ ግድጓዳ ወይም ዝቅተኛ ስፍራ |
| ረግረጋማ | ከወንዝ፣ ከሀይቅ፣ ከዝናብ በሚገኝ ውሃ የተሞላ አካባቢ |
| ቅልቅል | ድብልቅ፣ ስብጥር |

| | |
|---|---|
| ቅርስ | በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን በስነ-ጥበብ፣ በሳይንስ፣<br><br>በባህል ወይም በታሪክ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው፣ የህንጻ ወይም የመታሰቢያ ቦታ ወይም ሀውልት፣ የጥንታዊ ከተማ ፍርስራሽ፣ የመቃብር ቦታ፣ የዋሻ ስዕል፣ የድንጋይ ላይ ጽሁፍ፣ የብራና ጽሁፍ፣ የተጠራቀመ፣ የተካበተ |
| ቅይጥ | ድብልቅ፣ ቅልቅል፣ ዝንቅ፣ የልዩ ልዩ ነገሮች አንድነት ቅልቅል |
| በይነ መረጃ | የመረጃ መረግ፣ ድረ ገጽ |
| ተደራሲያን | ታዳሚዎች፣ ተመልካቾች፣ አድማጮች |
| ትልልፍ | መተላለፍ፣ አልፎ መሄድ |
| ትንኮሳ | ጠብ መጫር፣ መጀመር፣ ፍለጋ፣ ለኮፍ ማድረግ |
| ነፍሰ ጡር | የፀነሰች፣ በማህፀኗ ፅንስ የያዘች፣ የከበደች፣ ያረገዘች |
| አመክንዮ | ምክንያት |
| አምልኮ | እምነትን ለመግለጽ ሰዎች የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች |
| አራስ ነብር | ቁጡ፣ ኃይለኛ ሰው |
| አቀንቃኝ | የዜማ፣ የዘፈን ወራጅ (አቀንቃኝ ገፀ ባህርይ - አውራ፣ዋና፣ ዐብይ ገፀ ባህርይ) |
| አውታር | የድንኳን መወጠሪያ ገመድ፣ የበገና፣ የክራር ጅማት |
| እምነት | ሃይማኖት፣ አምልኮ፣ እርግጠኛነት |
| እርቃን | ያለ ልብስ ራቁት መሆን፣ መ ጋ ለ ጥ |
| እኩይ | ምግባረ ቢስ፣ በጣም የከፋ፣ ርህራሄና ምህረትየማያውቅ |
| ተንሰራፋ | ሰፊ ስፍራ እየያዘ፣እየተባዛ፣እየተዋለደ ክምችት |

| | |
|---|---|
| ክምችት | የተከማቸ፣ ስብስብ፣ ጥርቅም፣ ያልተመረተ ማዕድን |
| ክፍተት | በሁለት ነገሮች መካከል የሚገኝ ባዶ ቦታ፣ ቀዳዳነት፣ ስንጥቅነት፣ የአንድ ነገር ግንኙነት መቋረጥና ክፍት ሆኖ መገኘት |
| ወለላ | ሰፈፍ የሌለበት ንፁህ ማር፣ ፋህፋህ ደግ ሰው |
| ወጥመድ | አድፍጦ ሜዣ፣ አሽክላ፣ ከባቢ |
| ውሰት | መዋስ፣ ከሌላው መበደር፣ መውሰድ |
| እንቁ | በባህር ውስጥ የሚገኝ ከወርቅ የሚበልጥ የከበረ ድንጋይ |
| ዘዬ | ፈሊጥ፣ የአሰራር መንገድ፣ ልማድ፣ ቀበልኛ፣ የአካባቢ አነጋገር |
| የሚያስደምም | የሚያስገርም፣ የሚያስደንቅ፣ እጅን በአፍ የሚያስጭን |
| የተዛባ | የተፋለሰ፣ ቅደም ተከተላቸውን የሳቱ፣ የተሳሳቱ፤ ይተነብያሉ |
| ይፋ ሆነ | ተነገረ፣ ተወራ፣ ሽሽግነቱ ቀረ፣ ተገለጸ |
| ደለል | በወራጅ ወሃ፣ በጎርፍ ወይም በነፋስ ተሸካሚነት ተጠርጎ ወይም ተወስዶ በሌላ ቦታ የተከማቸ ለም አፈር፣ የአሸዋ ዝቅጠት |
| ደሴት | ዙሪያውን በባህር የተከበበ መሬት |
| ደጅ መጥናት | ጉዳዩን ለማስፈጸም መጉላላት፣ መመላለስ |
| ዳርቻ | ዳር፣ መሀል ያልሆነ፣ |
| ድሪቶ | ያረጀ፣ የተቀደደ፣ የተቦጫጨቀ ልብስ |
| ጋጠወጥ | ልቅነት፣ ሥርዓት አልበኝነት |
| ግብይት | የሸቀጥ ዕቃዎች ልውውጥ |
| ፈጠራ | ልቦለድ፣ አዲስ ቁስ አካላዊ እሴቶችንና መንፈሳዊ ፋይዳዎችን የመፍጠር ችሎታና እንቅስቃሴ፣ በምርመራ፣ በሙከራ የሚገኝ አዲስ ነገር፣ ውሸት፣ የፈጠራ ወሬ |

# ዋቢ ጽሁፎች


ማዕረጉ በዛብህ (1995)። የጋዜጠኝነት ሙያ ንደፈሃሳብና አተገባበሩ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

በዕውቀቱ ስዩም (1995)። ኗሪ አልባ ጎጆዎች። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት

ባየ ይማም (2000)። የአማርኛ ሰዋስው፣ የተሻሻለ ሁለተኛ እትም። አዲስ አበባ፣እሌኒ ማተሚያ ቤት።

______ (2010)። አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው (4ኛ ዕትም)። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

አቡሽ አያሌውና ሌሎች (ዓ.ም. ያልተጠቀሰ)። የኮሮናው መብረቅ። አዲስ አበባ፣ ሔሪቴጅ ኅትመትና ንግድ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር።

ኢ.ፌ.ዴ.ሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር (2008)። መሰረታዊ የስነጽሑፍ ማሰልጠኛ ሞጁዩል። አዲስ አበባ፣ ኢኒስፓየር ፕሪንቲነግ ፕረስ።

ዘሪሁን አስፋው (2005)። የስነጽሁፍ መሰረታውያን፤ (7ኛ ዕትም)። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ደበበ ሠይፉ (1992)። ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ።የብርሃን ፍቅር (ቅጽ፣2)፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

ጌታሁን አማረ (2011)። ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።